# የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርአት እና የማስረጃ ሕግ/ረቂቅ/ አጭር ማብራሪያ

## ማውጫ


የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርአት እና የማስረጃ ሕግ አጭር ማብራሪያ ..... 3

1. አጠቃላይ ..... 3

1.1. መግቢያ ..... 3

1.2. የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ ..... 7

1.3. ረቂቆችን የመከለስና ድጋሚ የማርቀቅ ሥራን የማከናወን ሂደት ..... 8

2. የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዐት ሕግ ለማርቀቅ የተለዩ ተጨማሪ ችግሮች፤ ..... 10

2.1 የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ችግሮች ..... 10

3. መግቢያና ጠቅላላ ጉዳዮች ..... 12

4. ስያሜው ..... 13

5. የተፈጻሚነት ወሰንና ቀን ..... 14

6. ትርጉም ..... 16

7. የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ መርሆዎች ..... 18

8. የሕጉ አላማ ..... 20

9. የተከላካይ ጠበቃ ጉዳይ ..... 21

10. የፍትሕ አካላት ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት ..... 22

11. የወንጀል ምርመራ ተግባራት ..... 23

12. ማስረጃ አሰባሰብ ..... 30

12.1. የዋስትና ጉዳይ ..... 38

12.2. በምርመራ መዝገብ ላይ መወሰን ..... 40

12.3. የጥፋተኛት ድርድር ..... 42

12.4. አማራጭ መፍትሔዎች ..... 45

12.5.ክስ የመመስረት ውሳኔ ..... 47

13. ዳኝነት ነክ ጉዳዮች ..... 49

13.1 የዳኝነት ሥልጣን ..... 50

13.2 ችሎትና ግልፅነት ..... 56

13.3. ከፍርድ እና ከፍትሕ ሂደት ስለመነሳት ..... 58

13.4. መጥሪያ ..... 59

13.5.የቅድመ ክስ መስማት ተግባራት ..... 61

13.6. የክርክር ሥርአቶች ... 63
13.7. ቀጠሮ፣ መቃወሚያና እምነት ክህደት ... 70
13.8. የማስረጃ ደንቦች ... 73
14.ፍርድና ቅጣት ... 79
14.1 የቅጣት ውሳኔ ... 80
15. ፍርድ እንደገና የሚታይባቸው አግባቦች ... 86
15.1 ይግባኝ ... 87
15.2 ሰበር ... 89
15.3 ፍርድን እንደገና ማየት ... 93
16. በወንጀል ጉዳይ አለም አቀፍ የወንጀል ጉዳዮች ትብብር ... 94
16.1. የዓለምአቀፍትብብርምንነት ... 96
16.2. አሳልፎ መስጠት (Extradition) ... 97
16.3 በወንጀል ጉዳዮች መረጃ መለዋወጥ እና መተባበር (Mutual legal assistance) ... 97
16.3.1.ፍርደኞችን መስጠት ወይም መቀበል (Transfer of sentenced persons) ... 98
16.3.2. የወንጀል ክስን ወደ ሌላ ሃገር ማስተላለፍ ... 98
16.3.3. ሌሎች የዓለም አቀፍ ትብብር ዓይነቶች ... 98
16.4 የዓለም አቀፍ ትብብርንና የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት ... 99
17. ኪሳራና ወጪን በተመለከተ ... 102
18. ደንብ፣ መመሪያ እና ቅፃ ቅፆችን ማውጣትእንዲሁም ሕጉን ስለማሻሻል ... 103
19. ሰንጠረዥ ... 104

# የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርአት እና የማስረጃ ሕግ አጭር ማብራሪያ

## 1. አጠቃላይ

አሁን በስራ ላይ የሚገኘውን የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአት ሕግ ለማሻሻል ከዚህ በታች በተገለጹት ምክንያቶች ከ10 አመት በላይ የፈጀ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። በዚህ ሂደት ውስጥም በርካታ ማሻሻያዎች የተደረጉባቸው የሥነ ሥርአቱ ሕጎች እየተዘጋጁ ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን ከውይይቶቹ የሚገኙ ግብአቶችን ጭምር በማካተት ይህ የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕግ የመጨረሻ ሆኖ ተዘጋጅቷል። ይህ ማብራሪያ በረቂቅ ሕጉ ውስጥ ምን እንደተካተተና ለምን እንደተካተተ በጥቅሉ የሚያመለክት ሰንደ ሆኖ ነው የተዘጋጀው። በመሆኑም በረቂቅ ሕጉ ውስጥ የተካተቱት እያንዳንዳቸው አንቀጾች የሚብራሩት በሃተታ ዘምክንያት በመሆኑ ይህ ማብራሪያ ረቂቁ የያዛቸውን ጉዳዮች ጠቅለል ካለ ምክንያት ጋር እንዲያመላክት የተዘጋጀ ማብራሪያ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን።

### 1.1. መግቢያ

የኢፊዲሪ ሕገ መንግስት በመግቢያው ላይ በግልፅ እንዳስቀመጠው በህግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ ዘላቂ ሰላምና ዘላቂ ልማት የማረጋገጥ ግብ አለው። የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት የአገሪቱ የበላይ ህግ ከመሆኑም በላይ በርካታ የወንጀል ስነ ስርአትና የማስረጀ ድንጋዎችንም ያቀፈ ነው። የስነ ስርአትና የማስረጀ ድንጋጌዎቹ አንዳንዶቹ በቀጥታ በፍትሕ አካላቱ ወደ ተግባር ሊለወጡ የሚችሉ ሲሆን ሌሎቹ ድንጋጌዎች ደግሞ ለማስፈፀሚያነት ሌሎች ዘርዘር ያሉ ድንጋጌዎችን የሚፈልጉ ናቸው። በተመሳሳይም አገራችን የአለም አቀፍ ድንጋጌዎችን በተለይም ሰበአዊ የሲቪል፣ ፖለቲካል፣ የሕጻናት፣ ሴቶችና እና ሌሎች መብቶችን የተመለከቱ አለም አቀፍና አሕጉራዊ ስምምነቶችን የተቀበለች በመሆኑ በስራ ላይ ያሉትን የስነ ስርአትና የማስረጃ ህጎቻችንና አሰራራችን ከእነዚሁ ስምምነቶች አንጻር መቃኘት ይገባል።

የህገ መንገስቱ ግቦች የሆኑት የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ እና ዘላቂ ሰላምና ልማትን ማምጣት ሊሳኩ የሚችሉት የሃገር፣ የሕዝብና የግለሰቦች ሰላምንና ደህንነት ሲጠበቅ በመሆኑ መንግስት በዚህ መልኩ የሚገለፁትንና መሠረታዊ የሆኑትን የግለሰብና የቡድን መብት እና ጥቅም የማሟላት፣ የማክበርና የማስከበር ግንባር ቀደም ኃላፊነት ተጥሎበታል። በዚህ ረገድ መንግስት ኃላፊነቱን ለመወጣት በቅድሚያ እና በዋነኛነት መከናወን ከሚገባቸው ተግባራ ውስጥ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ እ.ኢ.አ በ2003 ዓ.ም ያወጣ

ሲሆን በ1949 የወጣውን የወንጀል ሕግ የተካውን የወንጀል ሕግንም በ1997 በስራ ላይ አውሏል፡፡ ይህ የወንጀል ሕግ ስነ ስርአትና የማስረጃ ሕግም የዚሁ ጥረት አካል ተደርጎ ማውጣት ያስፈልጋል፡፡

የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዐት እና የማስረጃ ሕግ ሲደነገግ በመሰረቱ በሁለት ትላልቅ ጎራዎች ውስጥ የሚታዩ የተለያዩ ጥቅሞችንና ፍላጎቶችን በማመዛዘንና ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በአንድ በኩል የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅና ለማስጠበቅ የወንጀል ድርጊት ፈፃሚዎችን ለፍርድ አቅርቦ ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ የሚያስፈልግ ሲሆን በሌላ በኩል እውነቱን ለይቶ በማውጣት አጥፊውን በትክክል ለይቶ በማውጣት አጥፊዎቹ ብቻ ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲቀጡ ለማድረግ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህን በሁለት ጎራ ስር የሚታቀፉ ልዩ ልዩ ፍላጎቶችን አጣጥሞ የወንጀል ሕጉን ትርጉም ባለው መልኩ ለማስፈፀም የሚያስችል ውጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ሚዛናዊ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ተደራሽ እና ከፍተኛ የሕዝብ አመኔታ ያለው አሠራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡ ወንጀል ተፈፅሞ ሲገኝ ወንጀሉ በማን፣ እንዴት፣ መቼ ወዘተ እንደተፈፀመ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ማስረጃዎች የሚሰበሰቡበት፣ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡበት እንዲሁም የማስረጃዎቹ ዓይነት፣ ክብደት እና ብቃት በአግባቡ የሚመዘኑበት ውጤታማ የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ ያስፈልጋል፡፡

ኢትዮጵያ ከ1940ዎቹ ወዲህ የተለያዩ የወንጀል ሕጎችን በመደንገግ እና የተለያዩ የፍትሕ ተቋማትን በማቋቋም ዘመናዊ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርአትን እየገነባች ያለች አገር ናት፡፡ በ1940ዎቹ ከተደነገጉ ሕጎች መካከል በ1949 ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እና ይህንን ሕግ ለማስፈፀም በ1954 ዓ.ም የተደነገገው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት ሕግ በዋናነት ከሚጠቀሱት ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ እነዚህን ሕጎች ጨምሮ በሌሎች የፍሬ እና የሥነ ሥርዐት ሕጎች ውስጥ በተለያዩ ክፍሎችና ድንጋጌዎች የተካተቱ ዘመናዊ የማስረጃ ሕግ መርሆዎችና ሥርዓቶችም ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በ1949 ዓ.ም የወጣው  የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አሁን ከደረስንበት ዘመን አዳዲስ አስተሳሰቦች፣ የቴክኖሎጂ ዕድገቶችና የሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ፅንሰ ሃሳቦች ጋር የሚጣጣም ሆኖ ባለመገኘቱ በ1997ቱ የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ተሽሯል፡፡ በአንፃሩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት እና በሌሎች ሕጎቹ ውስጥ ተበታትነው የሚገኙ የማስረጃ ሕጎች እንደ  የፀረ ሙስና፣ የጉሙሩክ እና የፀረ ሽብርተኝነት ወንጀሎችን አስመልክቶ ከተደረጉ ለውጦች በስተቀር ላለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመታት መሠረታዊ ማሻሻያ ሳይደረግበት እየተሰራበት ይገኛል፡፡ በመሆኑም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነሥርአት ሕግና በተለያዩ

በታዎች ተካተው የሚገኙ የማስረጃ ድንጋጌዎች አሁን ዘመኑ ከደረሰበት አስተሳሰብ እና መርሆዎች ጋር ማጣጣም ያስፈልጋል።

አሁን ባለንበት ዘመን ወንጀሎች (በተለይም እንደ ሽብርተኝነት፣ የኢኮኖሚ ወንጀሎች፣ በተደራጁ ቡድኖች የሚፈፀሙ ወንጀሎች) አለም አቀፍ ገፅታን እየያዙ በአይነታቸው፣ በብዛታቸው እና በአፈፃፀማቸው እየተወሳሰቡና በየጊዜውም ስልታቸውን አየቀያየሩ የሚፈፀሙ ሆነዋል። ከዚህ እድገት ጋር ለማጣጣም ታልሞም የ1949ኙ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በ1997ቱ የወንጀል ሕግ የተተካ ቢሆንም የወንጀል ሕጉን አላማና ግብ በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስችል የሥነ  ሥርአት ሕግ ያልወጣ በመሆኑ የወንጀል ፍትሕ ስርአቱ የተሟላ ሊሆን አልቻለም። ይህ በመሆኑም የመንግስት ተቋማት በሚቋቋሙበት ሕግ ውስጥ እንዲሁም ስነ ስርአትና ማስረጃ ነክ ባልሆኑ የወንጀል ሕጎች ውስጥ በርካታ የስነ ስርአትና ማስረጃድንጋጌዎች እየተካተቱ እንዲወጡ ሆኗል። ይህም በመሰረቱ በፍሬ ሕግና በስነ ስርአትና ማስረጃ ህግ መካከል በከፍተኛ ደረጃ መደበላለቅን የፈጠረና የፍትህ ሥርአቱን ቅርጽ ያዛባ የህግ አወጣጥ እንዲሰፍን አድርጓል።

በሌላም በኩል በስራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ በበርካታ ጉዳዮች ላይ ግልፅነት የጎደለው፣ በዘመኑ ከሚፈጸሙት ውስብስብና የረቀቁ ወንጀሎች አንጻር እንዲሁም ዘመኑ ከደረሰበት የወንጀል ሳይንስ ጋር ሲታይ ከዘመኑ ጋር የማይሄዱ በርካታ ድንጋጌዎች የተካተቱበትና መሰረታዊ  ክፍተት ያለበት ነው። ዘመኑ በዚህ መልኩ ቀድሞ ከመሄዱም በላይ የወንጀል ጉዳይ ሕብረተሰቡ ባዳበረው የረጅም ጊዜ ልምድም አንጻር እየታየ ጎን ለጎን በባህላዊ ስርአቶች የሚፈታበት አግባብም በዛው ልክ አቅፎ የሚጓዝ ቢሆንም ይህም ስርአት ቢሆን በስነ ስርአትና ማስረጃ ህግ ውስጥ በአግባቡ የተካተተ አይደለም። ይህ በመሆኑም በሳራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ በዘመናዊም ሆነ በባህላዊ አግባብ የሚታዩ እድገቶችን እና ተግባሮችን አሟልቶ ያልያዘ ሆኖ ተገኝቷል። ስለሆነም የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉን ከሕገ መንግስቱ፣ አለም አቀፍ ድንጋጌዎች እንዲሁም አለም አቀፍ ተቀባይነት ካላቸው የዘመኑ አሰራሮች ጋር በማጣጣም ማሻሻል ይስፈልጋል።

የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉን ለማሻሻል የሚያስችለው ረቂቅ ከመዘጋጀቱ በፊት በመስኩ የሚታዩ ችግሮች ለዚሁ በተቋቋመ አጥኙ ቡድን የተለዩ ከመሆናቸውም በላይ ችግሮቹ በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው፣ በፍትሕ

አካላት የአሰራር ለውጥ ጥናት እንዲሁም በተግባር በየጊዜው የሚስተዋሉ ችግሮች ለመሆናቸው የተረጋገጡ ናቸው። በተለይ ጎልተው ከታዩት ችግሮች ውስጥም የሚከተሉት ይገኙበታል።

የመጀመሪያው ችግር የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በወንጀል ስነ ስርአትና ማስረጃ ጉዳይ ላይ የተሟላ የህግ ማዕቀፍ የሌለው መሆኑን ይመለከታል። ይህም ሕገ መንግሥቱ ከፀደቀ በኋላ በሥራ ላይ የዋለውን የወንጀል ሕግ አሟላቶ የሚያስፈጽም የተሟላ የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ ካለመኖሩ ጋር የሚያያዝ ሲሆን መፍትሔውም በዚሁ አግባብ የሚታይ ነው። ይህን ዘርፈ ብዙ ክፍተት ለመለየት ለዚሁ ተግባር የተቋቋመው አጥኚ ቡድን በቅድመ ረቂቅ ጥናቱ በግብአትነት ከተጠቀማቸው ሰነዶች መካከል የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት፣ በስራ ላይ ያለው የ1954ቱን የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዐት ሕግ፣ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ፤ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲን ለማርቀቅ ጥቅም ላይ የዋሉ ሰነዶች፣ በፌዴራል መንግሥት የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር አካላት አሰራርን ለማሻሻል የተሰራ የጥናት ሰነድ፣ በክልል ፍትሕ አካላት የወንጀል ፍትሕ ሂደቱን አስመልክቶ የተዘጋጀ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የጥናት ሰነዶች፣ ከተለያዩ ፍትሕ አካላትና የሕግ ባለሙያዎች የተሰበሰቡ የናሙና መረጃዎች፣ ለጥናቱ መዳበር አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመነባቸው ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ የተለያዩ መጣጥፎችና የፍርድ ቤት ውሳኔዎች እንዲሁም የሌሎች ሃገሮች ህጎችና ልምዶች እና ሌሎች ሰነዶች እንደመነሻ ተወስደው ህጉን ለማርቀቅ አገልግለዋል። በዚህ የቅድመ ረቂቅ ጥናት የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ ውስጥ የሚታዩ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን የተተነተኑ ሲሆን የተለዩት ችግሮችና የችግሮቹ ጥልቀት የ1954ቱን የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዐት ሕግን በመጠነኛ ማሻሻያና ጥገና ከማስቀጠል ይልቅ በመሰረቱ ሙሉ በሙሉ ሊሻሻል እንደሚገባው ድምዳሜ ላይ አድርሰዋል።

በዚህ መልክ የተለዩትን ችግሮች የሚፈታ እንዲሁም ወረድ ብሎ እንደሚመለከተው የወንጀል ማስረጃ ሕግን ያካተተ ረቂቅ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ እንዲያዘጋጅ በፍትሕ ስርአት መሻሻያ ቦርድ በተወሰነው መሰረት ወንጀልን የሚመለከቱ የማስረጃ ድንጋጌዎችን አጠቃልሎ የያዘ የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ የመጀመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቷል። በዚህ መሰረት የተዘጋጀውንና 600 አንቀጾች ያሉትን የመጀመሪያ የወንጀል ሥነ ሥርዐት ረቂቅ ሕግ በተለያዩ መድረኮች ለማስተዋወቅ የተሞከረ ሲሆን በችግር ከተለዩት ጉዳዮች ውስጥ ለረቂቁ መነሻ የሚሆን የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ ያልነበረ በመሆኑ ረቂቁ በወቅቱ የተነሱ በርካታ ፖሊሲ ነክ ጥያቄዎችን መመለስ አልቻለም። ረቂቁ ሃገር አቀፍ ተፈፃሚነትን ታሳቢ አድርጎ የተዘጋጀ ስለነበር የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግን የመውጣት ሥልጣን በክልል ሥር መሆን አለበት ወይስ

በፌዴራል የሚሉ አስተያየቶች በመኖራቸው ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል የፖሊሲ አቅጣጫ አልነበረም። የፍትሕ ሥርዐት ማሻሻያ ቦርድ ይህንን ጥያቄ ተመልክቶ የተዘጋጀው ረቂቅ ተፈፃሚነት በፌዴራል ሥልጣን ሥር እንዲሆን በማሰብ በሰጠው አቅጣጫ መሰረት ከቦርዱ የተውጣጣው የሕግ ባለሙያ ቡድን የመጀመሪያውን ረቂቅ በመከለስ በፌዴራል ስልጣን ስር የሚፈጸም 409 አንቀፆች ያለው ሁለተኛ የስነ ስርአትና ማስረጃ ረቂቅ ያዘጋጀ ቢሆንም ይህም ረቂቅ በተመሳሳይ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ በሌለበት የተዘጋጁ በመሆኑ ተመሳሳይ እና ሌሎች በአሁኑ ረቂቅ የተካተቱ የፖሊሲ ጉዳዮችን በአግባቡ ለመመለስ አልቻለም። በመሆኑም በወንጀል ስነ ስርአትና ማስረጃ ጉዳይ ላይ አገሪቱ የምትመራበት ፖሊሲ የግድ የሚያስፈልግ ለመሆኑ ሂደቶች አረጋግጠዋል።

## 1.2. የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ቀደም ብለው የተዘጋጁት ረቂቆች በመሰረቱ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር የመንግሥትን አቋምና የመፍትሔ አቅጣጫ የሚያሳይ መነሻ ሰነድን መሰረት ያደረጉ ባለመሆናቸው ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ መልስ የሚሰጡ አልነበሩም። በመሆኑም የኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ አጽድቆ በስራ ላይ ማዋል ችግሩን ሊቀርፍ የሚችል በመሆኑ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ በስራ ላይ ውሏል። የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ የታዩ አንኳር አንኳር ችግሮችን ግምት ውስጥ በማስገባት ለችግሮቹ አጠቃላይ የሆነ የመፍትሔ አቅጣጫንና የመንግሥትን አቋም አመላክቷል። ፖሊሲው ለሚወጡ የወንጀል ህጎች ተፈፃሚ የሚሆኑ አግባብ ያላቸውን መርሆዎች፣ ድንጋጌዎችና እና እሴቶችን አካቶም ይዟል። በተለይ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ችግሮችን በማለት በወንጀል ፍትሕ ስርአቱ ውስጥ አዲስ ለሚወጡ ሕጎች መሰረት የሚሆኑ አቅጣጫዎችንም ያሰቀመጠ ነው።

የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ያካተታቸውን በርካታና ዘመናዊ አስተሳሰቦች እንዲሁም በለውጥ ስራዎች የተለዩ የተሻሉ አሰራሮችን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር በስራ ላይ ያለው የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ በርካታ ርቀቶች የሚቀሩት መሆኑን ፖሊሲው በድጋሚ አመላክቷል። በነዚህ አግባቦች ከተለዩት ችግሮች ውስጥም፤

- ✓ ነባር የስነ ስርአትና ማስረጃሕጎች ግልጽ አቅጣጫ ያልያዙ መሆናቸው፤
- ✓ ሕጎችን በስራ ላይ ለማዋል የሚያግዝ አላማ እና መርህ ያልነበራቸው መሆኑ፣

- ✓ በፍትሕ አካላት መካከል የየተቋማቱን ልዩ ባህሪ ባናዘበና በመርህ ላይ የተመሰረት ግልጽ የሆነ የአሠራር፣ የግንኙነት እና የአመራር ትስስር አለመኖሩ፣
- ✓ በከፊልም ሕጎቹ ከፈጠሩት ክፍተት በመነሳት በፍትሕ አካላት ውስጥ የሚገኙ የሕግ ባለሙያዎች የእውቀት፣ ተግባራቸውን በተመለከተ የአመለካከት፣ የሥነ ምግባርና የክህሎት ማነስ ችግር ያለባቸው መሆኑ፣
- ✓ ሕብረተሰቡን በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ በበቂ ሁኔታ እንዲሳተፍ የማያደርጉ መሆናቸው፤ በዚህም መደበኛውን የፍትሕ አስተዳር ውጤታማ ከማድረግ አንጻር ከሕብረተሰቡ ተሳትፎ ሊገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ጥቅም ማግኘት ያልተቻለ መሆኑና ሕዝቡ በፍትሕ ሥርዐቱ ላይ ያለው እርካታና አመኔታ እንዲቀንስ ያደረጉ መሆናቸው፣

የሚሉት ይገኙበታል። የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው በወንጀል መከላከል፣ በወንጀል ምርመራ፣ በዐቃቤ ሕግ አገልግሎት፣ በፍርድ አሰጣጥ ሂደት፣ በውሳኔ ማስፈጸም እና በአለም ዓቀፍ ጉዳዮች ለታዩ ችግሮች መፍትሔ ያመላከተ ሲሆን ከተለዩት ችግሮችም አንጻር የአገሪቱን ፍላጎት አመላክቷል። የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ከዚህ ቀደም ያልነበረ ከመሆኑም በላይ የኢትዮጵያን የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት መልሶ ለመገንባት እና ለማቋቋም የሃገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የዘመኑን አዳዲስ ሃሳቦችንና ፍልስፍናዎችን ማካተት እንደሚገባ ዝርዝሩ ያመላክታል። ቀደም ብለው ይነሱ ለነበሩ የፖሊሲ ጥያቄዎች ምላሽ እና አቅጣጫ የሰጠ በመሆኑ ለስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በግብአትነት አገልግሏል።

ይህንን ፖሊሲ በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል ለለውጡ አስፈላጊ የሆኑ በሥራ ላይ ያሉ ሕችጎን ማሻሻልና ከፖሊሲው አቅጣጫ ጋር ማጣጣም የግድ አስፈላጊ ነው። የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው በየደረጃው መሻሻል ይገባቸዋል ካላቸው ዝርዝር የፍትሕ ችግሮች ውስጥ አብዛኛዎቹ በወንጀል ሥነ ሥርዐት እና የማስረጃ ሕጉ ውስጥ መካተት የሚገባቸው ናቸው።

## 1.3. ረቂቆችን የመከለስና ድጋሚ የማርቀቅ ሥራን የማከናወን ሂደት

የኢፌዴሪ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲን መጽደቅ ተከትሎ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ረቂቆች እንደገና መፈተሽና አስተካክሎ ማርቀቅ የግድ ነበር። ከዚህ አንፃር ፖሊሲው ቀደም ሲል ይነሱ ከነበሩ የፖሊሲ ጥያቄዎች ውስጥ ለበራካቶቹ ምላሽ የሰጠ በመሆኑና የሃገሪቱን የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ አቅጣጫ ያመለካተ በመሆኑ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲውን መሠረት ያደረገና የአፈፃፀም ወሰኑም አገር አቀፍ

ተፈፃሚነት ያለው የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዐት ማውጣትና መከለስ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህንንም ተከትሎ የፍትሕ አካላቱን መፍትሔ የሚሹ ችግሮችን ከሁሉም አቅጣጫ መመልከተ እንዲቻልም ከተለያዩ የፍትሕ አካላትና እና የሕግ ትምሕርት ቤት የተውጣጡ የሕግ ባለሙያዎችን ያካተተ አርቃቂ ቡድን የተደራጀ ሲሆን አርቃቂ ቡድኑም የቀደሙ ረቂቆቹን በመከለስ በድጋሚ የማርቀቅ ሥራውን አከናውኗል፡፡ ተግባሩንም የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እንዲከታተልና እንዲቆጣጠር ተደርጓል፡፡ አርቃቂ ቡድኑም ቀደም ብለው የተዘጋጁትን ረቂቆቹን በሙሉ ከማገናዘቡም በላይ፤

- የሕገ መንግሥቱን መሠረታዊ መብቶችና ድንጋጌዎች፣
- የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ዝርዝርና አጠቃላይ አቅጣጫ፣
- የ1996 ዓ.ም የወንጀል ሕግ፣
- በፍትሕ አካላት ለወንጀል የፍትሕ ስርአት አስተዳደር መሻሻል ይረዳሉ ተብለው የተጡኑ ተጨማሪ ትናችን እና ልዩ ልዩ ጽሁፎችን፣
- በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጣቸውን የሕግ ትርጉሞች፣

በመመልከት ረቂቁን ከማዘጋጀቱም በተጨማሪ ከዚሕ በላይ በተመለከቱት ጉዳዮች ያልተካተቱ ችግሮችን በመለየት፣ የውጪ ተሞክሮዎችን በመቀመር፣ ሕግ ሊወጣላቸው የሚገባቸውን ጉዳዮች በመዘርዘር፣ በሥነ ሥርዐት ሕጉ ወይም ሌላ ሕግ መካተት ያለባቸውን የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ ጉዳዮች በመለየት፣ ሕጉ ሃገራዊ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የክልሎችን ጉዳይ በማካተት እንዲሁም በወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ የጋራ አቋም ሊያዝባቸው የሚገባ ጭብጦችን በመለየትና ከተለያዩ መድረኮች ግብአቶችን በመሰብሰብ ሕጉ ተረቋል፡፡

ከፍ ሲል የተመለከቱትን የሃገራችን የወንጀል ፍትሕ አስተዳር ችግሮችን መቅረፍም የሚቻለው ወንጀልን የሚመለከቱ የማስረጃ ድንጋጌዎች በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዐቱ ውስጥ አካቶ በመደንገግም ጭምር በመሆኑ የማስረጃ ድንጋጌዎች ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ ከሥነ ሥርዐቱ ጋር የማዋሀድና የማደራጀት ሥራ ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው የተካተቱትንና የሕግ እና የአፈፃጸም ክፍተትን ለመለየት የሚረዱ እንደ የአለም ዓቀፍ ግንኙነት ጉዳዮች፣ አሳልፎ መስጠት ሂደት (Extradition)፣ የጋራ የሕግ ጉዳዮች ትብብር (Mutual legal assistance) እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ጥናት በማካሔድ በሕጉ እንዲካተት ሆኗል፡፡

## 2. የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዐት ሕግ ለማርቀቅ የተለዩ ተጨማሪ ችግሮች፤

በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ የተስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች፣ የችግሮቹ መንስዔዎች እና መገለጫዎች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዐት ሕግ ቅድመ ረቂቅ ጥናት በሰፊው ተመልክተዋል፡፡ ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት ጋር ተያይዘው ያሉ ችግሮች እጅግ በርካታ መሆናቸው በተመሳሳይ ተለይቷል፡፡ በዚህ መሠረት ሕጉ ውስጥ የሚስተዋሉ የሕግ እና የአሠራር ክፍተቶችን፣ የሕጉ ድንጋጌዎች ግልፅነት መጓደል፣ አገሪቱ እንዲሁም አለም አሁን ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ አንጻር ያልተጣጣመ የሥነ ሥርዐት ሕግ ይዘቶች፣ መካተት የሚገባቸው አዳዲስ አስተሳሰቦች ካለመካተታቸው ጋር ተያይዞ የተነሣ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ላይ ያስከተለው ችግር ሲሆኑ በጥናት እና በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው የተመለከቱ አጠቃላይ ችግሮችን ሲሆኑ እንደሚከተለው በጥቅሉ ተመልክተዋል፡፡

### 2.1 የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ችግሮች

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት፣ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ በመሆኑ በሕገ-መንግሥቱ እና በወንጀል ሕጉ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የሚወጣ ሕግ ነው፡፡ ሕጉ ራሱን ችሎ አዋጅ ሆኖ ቢወጣም ዓላማው እና ግቡ በሕገ-መንግሥቱ እና በወንጀል ሕጉ ውስጥ የተቀመጡትን ዓላማዎች እና ግቦች ለማስፈጸም የሚወጣ ነው፡፡ ለግማሽ ምዕተ ዓመት ሲያገለግል የነበረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በ1997 ዓ.ም የተሻረ ቢሆንም የተሻረውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ተከትሎ የወጣው የ1954 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ግን ሕገ መንግስቱም ሆነ የወንጀል ሕጉ ከደረሰበት ደረጃ እንዲሁም አለም ከደረሰበት ደረጃ ጋር በሚጣጣም መልኩ ሳይሻሻል ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በሕግ መሰረት ውጤታማና ፍትሃዊ የፍትሕ አገልግሎት ለመስጠት የሚደረግ ጥረት ላይ ቀላል የማይባሉ ችግሮችን አስከትሏል፡፡ ከዚህም አንጻር በተለይም የወንጀል ፍትሕ አስተዳደሩ ያጋጠሙት ችግሮች ሲጠቃለሉ፤

- ✓ የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ ሕገ-መንግሥቱን እና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ተቋማዊ በሆነው አግባብ ማገልገል አለመቻሉ፣በፌዴራልም ሆነ በክልል እየተሰሩ ላሉት የመሰረታዊ ለውጥ ስራዎች በቂ የህግ ማእቀፍ ሆኖ በማገልገል የለውጡን ውጤታማነት ቀጣይነት ለማረጋገጥ በሚያስችል ደረጃ ላይ አለመገኘቱ፣
- ✓ የሕዝብ ጥቅሞች እና ፍላጎቶች በበቂ ሁኔታ የሚረጋገጡበትና የሚከበሩበት የሕግ ማዕቀፍ ሆኖ ለማገልገል አለመቻሉ፣

- ✓ በአሁኑ ሰአት እየተወሳሰቡ የመጡትን ወንጀሎችና አፈፃጸማቸውን ለመከታተልም ሆነ ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ መርምሮ እውነቱን ለማውጣት የሚያስችል የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ አለመሆኑ፣
- ✓ ከወንጀል ፍትሕ ሂደቱ የሚገኙ ውጤቶች የሕብረተሰቡን ሰላም እና ደህንነት በበቂ ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚያስችል የሕግ ሥርዓት ለመፍጠር አለመቻሉ፣
- ✓ የሚፈጸሙ የተለያዩ ወንጀሎችን አስመልክቶ በማስረጃ በማረጋገጥ እውነቱን አንጥሮ ለማውጣት የሚያስችል የወንጀል ፍትህ ስርአት ከመገንባት አንጻር የስነስርአት ህጉ ያለው ሚና ከሚጠበቅበት በታች መሆኑ፣
- ✓ የሕብረተሰቡን ተሳትፎ በተገቢው ሁኔታ የሚያረጋግጥ አለመሆኑ፣
- ✓ የወንጀል ተጎጂዎችን በፍትሕ ሂደቱ የሚሳተፉበትን አግባብ በአግባቡ የሚያስችል አለመሆኑ፣
- ✓ አገሪቱ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ዘርፍ ከዓለም አቀፍ ሕግጋት እና የአሠራር ሥርዓት አንጻር ያሏትን መብቶች ለማስከበርና የተጣሉባትን ግዴታዎች ለመወጣት የሚያስችል የህግ ማእቀፍ አለመሆኑ፣
- ✓ የሰዎችን ሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች በተሟላ መልኩ ለማክበር እና ለማስከበር የሚያስችል የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ከመፍጠር አንጻር የወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕጉ መጫወት ያለበትን ሚና በሚፈለገው ደረጃ አለመወጣቱ
- ✓ አለማቀፍ ትብብርን በተመለከተ እንደሀገር የምንመራበት ስርአት አለመኖሩ፣
- ✓ አማራጭ የመፍትሄ እርምጃዎች፣ ባህላዊ ስርአቶችና ሌሎች መፍትሄዎችን አስመልክቶ ስርአት ያለተበጀ በመሆኑ የብሄሮች ብሄሮችና ህዝቦችን ባህላዊ ስርአቶች ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉ የሚሉት እና ሌሎች መሰል ጉዳዮች

ዋና ዋና ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው። እነዚህን እና ተያያዥ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ የሚያሰፈልግ በመሆኑ በስራ ላይ ያለውን የስነ ስርአትሕግ በሚከተለው መልኩ ያሻሻለና የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ያካተተ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ተዘጋጅቷል።

## 3. መግቢያና ጠቅላላ ጉዳዮች

የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ **በአስር መጽሃፎች የተከፋፈለ ሆኖ 444 አንቀጾችን** ያካተተ ነው። ሕጉ የተደራጀው ሁሉንም የፍትሕ አካላት በወልና በጋራ ከሚመለከቱ ጉዳዮች አንስቶ የወንጀል ፍትሕ ሒደቱን የሥራ ፍሰት ተከትሎ ነው። ሕጉ አዳዲስ ጉዳዮችን ያካተተ ከመሆኑም በላይ አጠቃላይ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደሩ የሚመራበትንና ሕጉ የሚተረጎምበትን መንገድ በማመልከት ነው የሚጀምረው። ይህም በስራ ላይ በነበረው ሕግ ውስጥ ያልነበረ ሲሆን የአሁኑ ረቂቅ የሕጉ አካል በሆነው በመግቢያው ክፍል የሕጉን አላማ በግልጽ አስቀምጧል።

የቀድሞው የሥነ ስርአት ሕግ መግቢያ ያልነበረው በመሆኑ ሕጉን ለመተርጎም አጋዥ ሊሆን የሚችል ትልቅ መሳሪያ ጎድሎት ቆይቷል። የፍትህ አካላት በወንጀል ገዳይ ላይ በምን መስመር ህጎቹን መተርጎም እንዳለባቸው ለተለያዩ አላማዎች ከተጻፉ የተለያዩ መጣጥፎች ለመረዳት ከመሞከራቸው በስተቀር የስነ ስርአት ሕጉን አላማ በግልጽ ሳይረዱ ሲሰሩ ቆይተዋል። በመሆኑም ነባሩ የስነ ስርአት ሕግ የነበረበትን ክፍተት እና የግልጸኝት ችግር በመቅረፍ በሕግ አወጣጥ ስርአታችን በበርካታ ሕጎቻችን ውስጥ እንደምናገኘው ይህ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ግልጽ የሆነ መግቢያን እንዲያካትት ሆኗል። ይህ መግቢያ በዋነኛነት ሕጉ ለምን፣ በማንና በምን ስልጣን እንደወጣ የተመለከተበት ነው። ሕጉን ለማውጣት አስፈላጊ ከሆኑት ምክንያቶች ውስጥም ከፍ ሲል የተዘረዘሩት የፍትሕ አስተዳደር ችግሮችን በመቅረፍ በሕገ መንግስቱ የተመለከቱትን የሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶችን አሟልቶ ተግባራዊ ለማድረግ በስራ ላይ ያለው ስነ ስርአትህግ ያልቻለና የማይችል መሆኑ፣ አገራችን ያፀደቀቻቸውን፣ የገባችባቸውንና የምትገባባቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶች (እንዲሁም የሁለትዮሽ እና ባለ ብዙ ሃገራት ስምምነቶች) እና መርሆዎች በተሟላ ሁኔታ መተግበር የሚገባ በመሆኑ፣ በዚህ ረገድ በግንኙነቱ አለም አቀፍ ግዴታን በአግባቡ ለመወጣትና በዚህ ረገድ የሚኖሩ ጥቅሞችንና መብቶችን በአግባቡ ማግኘትና ማስከበር በማስፈለጉ፣ እየበዙና እየተወሳሰቡ የመጡትን ወንጀሎች ውጤታማ ባለው ሁኔታ በመመርመር እውነቱ ላይ መድረስ የሚያስፈልግ በመሆኑ፣ ሕብረተሰቡን በወንጀል ፍትሕ ስርአቱ ውስጥ ማሳተፍ የሚያስፈልግ በመሆኑ እንዲሁም ተበታትነው የሚገኙ ልዩ ልዩ የስነ ስርአትና ማስረጃ ህጎችን አጠቃሎ በመፅሃፍ መልክ በማውጣት ለአጠቃቀም የተመቸና ይበልጥ ግልፅ የሆነ ሕግ እንዲሆን ለማድረግ በማለም የወጣ እንደሆነ መግቢያው በግልጽ ያመለክታል። የወንጀል ሂደቱን ውጤታማነት እና ፍትሓዊነት ማረጋገጥ በተለይ በእለት ተእለት የፍትሕ አካላት ሊተገበሩ የሚገባቸው እሴቶች ናቸው። መግቢያው በሕጉ አላማ ውስጥ

አጠር ብሎ የተቀመጠ ቢሆንም ሕጉን በቀጥታ ለመፈፀምም ሆነ ተርጉሞ ለመፈፀም አይነተኛ የአፈፃፀምና የትርጉም መሳሪያ በመሆን ያገግላል ተብሎ ይታሰባል።

የሕጉ መግቢያ የሕጉ አላማ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደሩን ውጤታማት ማረጋገጥ ነው ሲል ውጤታማነት የተደራሽነት፣ ቅልጥፍና፣ ግልጽነት፣ ነጻነት እና ተጠያቂነት ድምር ውጤት መሆኑን በመውሰድ ነው። በተመሳሳይም የፍትሓዊነት አላማ በፍትሕ ሂደት ውስጥ የሚያልፉ ተከራካሪ ወገኖች እኩል፣ ለአንዱ ወገን ብቻ ያላደላ በፍትህ ሂደት ውስጥ የሚያልፉ ወገኖች ሁሉ በህግ ላይ የተመሰረተ ትክክለኛና ሚዛናዊ እድል ማግኘት ያለባቸው መሆኑን የሚያሰምር እሴት ነው።

የሥነ ስርአት ሕጉን የፌዴራል መንግስቱ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 55(5) መሰረት የወንጀል ህግን ለማውጣት በተሰጠው ስልጣን መሰረት፣ በሕገ መንግሰቱ አንቀፅ 55(1) ስር የተመለከቱትን የኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ፣ ንግድ፣ ፀጥታ፣ አለም አቀፍ ወዘተ ጉዳዮችን ለማስፈፀም የሚያስችል ሕግ ለማውጣት እንዲችል እንዲሁም የፌዴራል መንግስቱ ያወጣውን ሕግ የማስፈጸም ኃላፊነት የፌዴራል መንግስቱ ከመሆኑ የተነሳ ለፌዴራል መንግሰቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የወጣ መሆኑም በመግቢያው ላይ ተመልክቷል።

## 4. ስያሜው

የህጉ ስያሜ የስነ ስርአትጉዳይንና የማስረጃ ጉዳይን ማካተቱን በሚያመላክት አግባብ የተቀረጹ ሁለት ሀረጎች ያሉት ነው። ስያሜው በወንጀል ስነ ስርአትና ማስረጃ ጉዳይ ላይ የማይታለፉ ሁለት ጉልህ ጉዳዮች በህጉ ውስጥ መካተታቸውን በቀጥታ እና በግልጽ ያመለክታል። ሕጉ አንድ ወንጀል ተፈፀመ ከተባለበት ጊዜ አንስቶ ወንጀል አድራጊው በምርመራ የሚለይበት፣ ለፍትሕ ሂደት የሚቀርብበት እና አጥፊው በአግባቡ ታርሞ ሕብረተሰቡ ጋር የሚቀላቀልባቸውን ሂደቶች እና ስርአቶች አሟልቶ የያዘ በመሆኑ እና በስራ ላይ ያሉትን የወንጀል ህጎች ለማስፈፀም የሚያገለግል በመሆኑ የወንጀል  ህግ ስነ ስርአትና ማስረጃ የሚል ስያሜን አካቷል። በሌላ መልኩ በወንጀል ፍትህ አስተዳር ስነ-ስርአት ውስጥ ከምርመራ እስከ ውሳኔ አሰጣጥ ያለው ሂደት  ያለ ማስረጃ ሊከናወን የሚችል አይደለም። በሒደቱ ሁሉ ማስረጃ ምን እንደሆነ፣ ማን ሊሰበስበው እንደሚችልና እንደሚገባ፣ በየደረጃው የሚፈለገው የማስረጃ አይነትና መጠን ምን መምሰል እንዳበት ካልተመለከተ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ የተሟላ ሊሆን አይችልም። የማሰረጃ ደንቦቹ የስነ ስርአትሕጉ አካል ሆነው መውጣታቸው የወንጀል ጉዳዮች ከወንጀል ሕጎች ጋር በቀላሉ እንዲዋሃዱ ስለሚያደርግ፣ በወንጀል ጉዳይ ላይ በተቻለ መጠን የወንጀልን ጉዳይ ያጠቃለለ መፅሐፍ እንዲኖር

ስለሚያስችል፣ ሕጎቹን በወጥነት ለመፈፀም ወይም ለመተርጎም ስለሚያግዝ  የሌሎች ሃገራትን ልምድም በመመልከት ከስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ጋር ተጠቃሎ የወጣ በመሆኑ ስያሜውም ማሟላት ይገባዋል። በዚህ መሰረት ዋናው ርእስ የሕጉን አውጪ፣ የሚፈፀምበትን ወሰን እንዲሁም የሕጉን ይዘት ሊያመለክት በሚችል መልክ የተቀረፀ ሲሆን "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዐት እና የማስረጃ ሕግ" የሚል ሆኗል።

ይህ የሕጉ ዋና ስያሜና የሁልጊዜ መጠሪያው ነው። ይሁን እንጂ ስያሜው ረጅም ከመሆኑ የተነሳ የፍትሕ አካላት በየእለቱ በእያንዳንዱ ደቂቃ ለሚያከናውኑት ተደጋጋሚ ሥራ ለየተግባራቱ ሁሉ ሁል ጊዜ ይህንን ርእስ መጠቀም ያስቸግራቸዋል። በመሆኑም ህጉ ለእለት ከእለት ስራ መጠሪ የሚሆነው አጭር ርእስ ያስፈልገዋ። የህጉ አጭር ርእስ የፍትሕ አካላት በእለት ከእለት ተግባራቸው ረጅሙን ርእስ ለመጠቀም የሚቸገሩ በመሆኑ ከላይ የተመለከተውን አላማ ማሳየቱን እንደተጠበቀ ሆኖ ለአጠቃቀም እንዲመች ተብሎ ያጠረ ስያሜ ነው። አጭሩን ርእስ የፍትሕ አካላት በእለት ተእለት ስራቸው የሚጠቀሙበት ይሆናል። ስለሆነም ሕጉ አጭር ርእስ ተሰጥቶታል። በዚህ አግባብም አጭሩ ርእስ "የ፳፻፬ ዓ.ም የወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ"  የሚል ሆኗል።

## 5. የተፈጻሚነት ወሰንና ቀን

የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በማናቸውም የወንጀል ስነ ስርአትና ማስረጃ ጉዳዮች ላይ ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ በሚኖሩ የስነ ስርአትና ማስረጃ ጉዳዮች ላይ ሁሉ በወንጀል ጉዳዮች ላይ የመመርመር፣ የመክሰስ፣ የመዳኘት፣ አግባብ ያለውን መፍትሔ የመስጠት እና አጥፊን አርሞ የመቀላቀል ስልጣን በተሰጣቸው አካላት ሁሉ ተፈፃሚ የሚሆን ነው። ሕጉ የሚፈጸመው በወንጀል ጉዳዮች ላይ ሁሉ ነው። የወንጀል ጉዳዮች የሚባሉት በ1996 በወጣው የወንጀል ሕግ ውስጥ የተካተቱትን ጨምሮ በሌሎች ልዩ  ሕጎችና  ደንቦች ላይ የተመለከቱ የወንጀል ሕጎችን ሁሉ ያካትታል። የወንጀል ሕግ ሲባል በ1996 የወጣውን የወንጀል ሕግ ብቻ የሚመለከት አድርጎ የመረዳት አዝማሚያ ሰፊ በመሆኑ ሌሎች የወንጀል ጉዳዮችም በዚህ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ እንደሚመሩ ሕጉ ሰፋ ያለ ትርጉም ይዟል።

ሕጉ በመጽሐፍ መልክ የወጣ በመሆኑ በወንጀል ጉዳይ ላይ የወጡ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጎችን በሙሉ ማጠቃለል ይገባዋል። የወንጀል ፍትሕ አካላት በተለያዩ አካላት ስር ይተዳደሩ በነበረት ጊዜ የፍትህ አካላቱ ከሥነ ሥርአቱ ሕግ ጋር በሚጋጩ በርካታ ልዩ የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕጎች በተለያዩ ሕጎች ሲመሩ የቆዩ

ናቸው። ሕጎቹም በተለይ ለወጡላቸው ጉዳዮች ብቻ የሚፈጸሙ በመሆናቸው የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ጉዳይ ላይ ወጥ ወይም በመርህ ደረጃ የተቀራረበ አረዳድ ያልነበራቸው ድንጋጌዎች በርካቶች ናቸው። ይህንን በመርህ ላይ ተመስርቶ ማመሳሰልና ሰዎች ሁሉ በእኩል የሚዳኙበትን እድል መፍጠር ያስፈልጋል። ተለይቶ የሚታይ ጉዳይ ቢኖር እንኳን ልዩነቱን መፍጠር ያስፈለገበትን ምክንያት በግልጽ በሚያሳምን አግባብ በዚሁ ስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ውስጥ መደንገግ ይቻላል። በመሆኑም በወንጀል ጉዳይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ሕጎችን በዚሁ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ በማካተት በዚሁ ሕግ ውስጥ ተካተው እንዲወጡ ተደርጓል።

በመሆኑም ሕጉ የተሻሩትንና ሕጉ በሸፈናቸው የወንጀል ስነ ስርአትና ማስረጃ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ የማይሆኑትን ሕጎች ለይቶ አሰቀምጧል። ለምሳሌ የፀረ ሽብር ሕግ እና የፀረ ሙስና ሕግ እና መሰል ሕጎች የያዟቸው የሥነ ሥርአትና እና የማስረጃ ድንጋጌዎች በዚህ ሕግ የተሸፈኑ በመሆናቸው በልዩ ሕጎቹ ውስጥ የተካተቱት ድንጋዎች ተፈጻሚ አይሆኑም። ይሁን እንጂ ከሥነ ሥርአትና የማስረጃ ውጪ ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከተቱ ት የልዩ ሕጎች ድንጋጌዎች አፈፃፀም በዛው በልዩ ሕጎቹ መሰረት ይቀጥላል ማለት ነው።

ሕጉ በመፅሀፍ መልክ የወጣ በመሆኑ ከሕጉ ጋር የሚጋጩ ሌሎች የወንጀል ሕግ ምርመራ፣ ማስረጃንና በዚህ ሕግ የተመለከቱ ጉዳዮችን የተመለከቱ ሕጎችን በዝርዝር ለይቶ ሽሯል። ሕጉ ከሕገ መንግስት በታች ስለሆነ በዚህ አግባብ “ሕግ” የተባለው ሕገ መንግስትን እንደማይመለከት ሕገ መንግስትን እንደማይሽር ግልፅ ነው። በሌላ በኩልም ልማዳዊ ሕጎች በተለየ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆኑ በሕጉ የተፈቀደ በመሆኑ ተፈፃሚ የማይሆኑት በዋነኛነት ከሕገ መንግሰቱ ጋር የሚጋጩት ሲሆኑ እንዲሁም እንዳግባቡ በጠቅላይ አቃቤ ሕግ መመሪያ ወይም ጉዳዩን በያዘው ፍርድ ቤት እይታ ከሕግና ከሞራል ጋር የሚጋጩ ሆነው ከተገኙ ነው። ስለሆንም ባህላዊ ሥርአቶች በሕጉ በተፈቀዱ ጉዳዮች ላይ ከሥነ ሥርአቱ በተለይ አካሄድና በተለየ መፍትሔ ተፈጻሚ ስለሚሆኑ በድፍኑ ይህንን ሕግ የሚቃረን ልማዳዊ አሰራር ሁሉ ተፈጻሚ አይሆኑም የሚለውን የተለመደውን አደነጋግ ይህ ሕግ አልመረጠም።

ሕጉ በሁሉም የወንጀል ሥነ ሥርአታዊ ጉዳዮች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ የሚሆን ነው። ይህ በሕጉ መግቢያ ላይ በግልጽ ተመልክቷል። በመሰረቱ ሕጉ የሚፈፀመው በህግ አውጪው ፀድቆ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ከታተመበት ቀን አንስቶ ነው። ይሁን እንጂ ሕጉ በርካታ አዳዲስ ሀሳቦችን ያካተተ በመሆኑ ለፍትሕ አካላት በሙሉ በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ስልጠና ሳይሰጥ መፈፀም ያሰቸግራል። ሕጉ ተሟልቶ

የሚፈፀመውም ልዩ ልዩ ደንቦችና መመሪዎች ወጥተው ነው። በሌላ በኩል ሕጉን በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ ተቋማትን (ለምሳሌ አማራጭ ቅጣቶችን የሚያስፈፅም ተቋም፣ የተከላካይ ጠበቃ ፅሕፈት ቤት፣ እውቅና የሚሰጣቸው ባሕላዊ ተቋማት፣ አማራጭ ቅጣት የሚፈጸምበትን ስርአት መዘርጋትና ተቋም መገንባት) ማቋቋም ያስፈልጋል።

በሌላም በኩል በነባሩ ሕግ የተጀመሩ ጉዳዮችም አዲስ ከወጡት ጋር ለማጣጣም የሚያስቸግርበት ሁኔታም ሊያጋጥም ይችላል። የይርጋ ጊዜ እስካላገደው ድረስ ማናቸውም የወንጀል ጉዳዮች ለምርመራ እና ለፍርድ መቅረባቸው አይቀርም። በልምድ እንደሚታየውም ያለፉ ጉዳዮች ለረዥም ጊዜ ከአዲስ ጉዳዮች ጋር አብረው መታየታቸው ይቀጥላል። ነባሩ ሕግ ለነባር ጉዳዮች እየተፈጸመ ይቆይ ቢባል ይህ ሂደት በማያቋርጥ ሁኔታ ይቀጥላል። የወንጀል ፍትሕ ስርአቱ ላይ ትርምስ ይፈጥራል። የእኩልነት እና መሰል የህገ መንግስት ጥያቄም ያስነሳል። ስለሆነም ተመራጭ የሚሆነው ይህ ሕግ መፈጸም ከሚጀምርበት ጊዜ አንስቶ ለሁሉም ጉዳዮች ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግና ምናልባት ነባሩ ሕግ ለነባር ጉዳዮች የሚጠቅም ከሆነ በወንጀል ሕግ መርህ መሰረት ጉዳዩ በልዩ ሁኔታ በነባሩ ሕግ እንዲታይ ማድረግ ነው።

ስለሆነም በእነዚህ እና መሰል ጉዳዮችን ተጨማሪ ችግር እንዳይሆኑ አስቀድመው የሚደረጉ ዝግጅቶች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሕጉ በሕግ አውጪው አካል ከፀደቀበት ጊዜ አንስቶ ሊያሰሩ የሚችሉ ተጨማሪ ዝግጅቶች ከተደረጉ በኃላ ስድስት ወር ቆይቶ በሁሉም ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ መሆን እንደሚገባው ተደንግጓል።

## 6. ትርጉም

የሕጉን አፈጻጸም እና አተረጓጎም ምቹና ቀላል ከማድረግ አንጻር የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ከዚህ ቀደም ትርጉም ላልተሰጣቸው ቃላት ወይም ሐረጎች እንዲሁም በሕጉ ለተካተቱት አዳዲስ ሃሳቦች ትርጉም ሠጥቷል። በዋነኛነትም ትርጉም የተሰጣቸው አገሪቷ ከምትከተለው ስርአት በመነሳትም ሆነ አለም ከደረሰበት እውቀት አንፃር ለፍትህ ስርአቱ አዲስ ለሆኑ ወይም በሕጉ ውስጥ ተደጋግመው ጥቅም ላይ ለዋሉ ወይንም ግልፅ ላልሆኑ ሃሳቦች፣ ቃላቶችና ሀረጎች ነው። ይህ ትርጉምም የፌዴራል እና የክልል ተቋማትን እንዲያካትት ሆኖ የተቀረጸ ነው። ለአብነትም በሚከተሉት ላይ ሕጉ ትርጉም ይሰጣል።

አገሪቷ ከምትከተለው የፌዴራል ስርአት አንጻር ፍርድ ቤት፣ አቃቤ ሕግ፣ ፖሊስ፣ መርማሪ እና ማረሚያ ቤት የተባሉት አካላት እና ተቋማት ትርጉም ያስፈልጋቸዋል። ለምሳሌ በወንጀል ጉዳይ ላይ የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ውሱን ስለሆኑ (መሆንም ስላለባቸው) ፍርድ ቤት በፌዴራል እና በክልል የተቋቋሙትን መደበኛ ፍርድ ቤቶችን እና ወታደራዊ ፍርድ ቤትን ብቻ እንዲያመላክት ተደርጎ ትርጉም ተሰጥቶታል። በሌላ በኩልም በወንጀል የተጠረጠረ ሰው በምርመራ፣ በክርክር እና በቅጣት ዘመን በእስር የሚቆዩ ከሆነ የመቆያ ቦታው የተለየ ሊሆን ይገባዋል። ወንጀል የፈፀመ ሰው ታርሞ ከሕብረተሰቡ ጋር በተሳካ ሁኔታ ሊዋሃድ የሚችለው በየደረጃው ያለው አያያዙ ጉዳዩ ያለበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ እንደሆነም ጭምር ነው። በመሆኑም ተጠርጣሪ መያዝ/መታሰር ካለበት በምርመራ ወቅት ፖሊስ በሚያዘጋጀው ማቆያ ቦት፣ በክርክር እና በቅጣት ዘመን ደግሞ እንደ ቅደም ተከተሉ ማረሚያ ቤት ለያይቶ በሚያደራጃቸው የማረፊያ እና የማረሚያ ቦታዎች መያዝ ይገባዋል። በመሆኑም ሕጉ ለ "ማቆያ፣ ማረፊያ እና ማረሚያ" ቦታዎችም ትርጉም ይሰጣል።

የወንጀል ጉዳዮች ከምርመራ አንስቶ እስከ ማረም ድረስ በተለያየ መንገድ መመራት ያለባቸው ናቸው። ጉዳዮች ተለይተው የማይመሩ በመሆናቸው ቀላሉም ሆነ ከባዱ ጉዳይ በአንድ መስመር እያለፉ በአኩል ሲጓተቱ መሰተዋላቸው የተለመደ ነው። በመሆኑም ጉዳዮችን በደረሱበት ደረጃ ሁሉ እንደ ክብደታቸው መስተናገድ እንዲችሉ ደረጃቸው በቀላል፣ መካከለኛ እና ከባድ ወንጀሎች ተከፍለዋል። ለአጠቃቀም ያመች ዘንድም ትርጉም የተሰጣቸው የወንጀል አይነቶች ድልድል በሰንጠረዥ ተለይተው ተቀምጠዋል። የዚህ ትርጉምም በተመሰሳይ ተመልክቷል።

የሥነ-ሰርአት ሕጉ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይንና ትእዛዝ የሚሉትን ቃላት በተደጋጋሚ ከሕጉ መጀመሪ እስከ መጨረሻው ድረስ ይጠቀምባቸዋል። በየትኛውም የፍትህ አካላት የእልት ከእለት ስራ ውስጥ በተደጋጋሚ ሳይጠሩ ስራ ሊሰራ አይችልም። ቃላቶቹ ጽንሰ ሃሳብን ያቀፉ ቃላት ከመሆናቸውም በላይ ተደጋግመው መገኘታቸው ትርጉም እንዲሰጣቸው ግድ ይላል። ይሁን እንጂ ቃላቶቹ ግልጽ ትርጉም ሳይሰጣቸው ቀርቷል። እስካሁን እየተሰራበት ያለው የስነ ስርአትሕግም ቢሆን ብይን የሚለውን ቃል የማይጠቀም ቢሆንም ፍርድ፣ ውሳኔ፣ እና ትእዛዝ ለሚሉት ቃላት ግልፅ ትርጉም ያልሰጠ በመሆኑ የቃላቱ አጠቃቀም ጽንሰ ሃሳብ የራቀው እና ወጥነት የጎደለው ሆኗል። በየትኛው ደረጃ ትእዛዝ ተሰጠ ሲባልም ተግባሩ በእርግጥ ትእዛዝ ለመሆኑ ከስያሜው ሳይሆን ከተግባሩ ይዘት ብቻ ለመረዳት ግድ ሲል ቆይቷል። ይህ በመሆኑም በፍርድ ቤት በተሰጠው ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትእዛዝ ላይ ይግባኝ የሚባልበት ለመሆኑ

ወይም ላለመሆኑ ለመረዳት የተግባሩን ይዘት እንጂ ስያሜው እምብዛም የማይረዳ ሆኖ ቆይቷል። በመሆኑም በተግባር የገጠመውን ሰፊ ችግር ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ የትርጉም ክፍሉ "ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን እና ትእዛዝ" ለሚሉት ቃላት ግልፅ ትርጉም አሰቀምጧል።

የትርጉም ክፍሉ የያዛቸው ትርጉሞች በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ለተመለከቱት ጉዳዮች ሁሉ የሚያገለግሉ ናቸው። ይሁን እንጂ ከስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ ለተወሰነ ክፍል ብቻ የሚያገለግሉ ትርጉሞች ባጋጠሙ ጊዜ ወይም ለአንድ ወይም ለተወሰነ አንቀፆች ብቻ የሚያገለግሉ ትርጉሞች ባጋጠሙ ጊዜ ትርጉሙ በሚፈለግበት በተለየው ክፍል ውስጥ ብቻ እንዲቀመጥ ሆኗል ይህም ከህግ አረቃቀቅ መርህ አንፃር ተገቢ ነው።

በሕጉ የሚታወቁት ፍርድ ቤቶች የመደበኛው እና ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች በመሆናቸው ለመደበኛው አሰራር የተቀመጡት ትርጉሞች በሙሉ እንዳግባቡ ለወታደራዊ ፍትሕ አካላትም (ወታደራዊ ፍርድ ቤት፣ ወታደራዊ አቃቤ ሕግ፣ ወታደራዊ ፖሊስ እና ወታደራዊ ተከላካይ ጠበቃ) የሚያገለግሉ ናቸው። የማረም ጉዳይ ድንጋጌዎችም በተመሳሳይ የሚፈጸሙ ናቸው።

## 7. የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ መርሆዎች

ምንም ያህል የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉን አፈጻጸም ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ጥረት ቢደረግም ትርጉም የሚፈልጉ ጉዳዮች ማጋጠማቸውን ማሰቀረት አይቻልም። ሕግን በመተርጎም መፈፀም የግድ አስፈላጊ ነው። ተገቢው ነገር ሕጉ በዘፈቀደ እንዳይፈጸም እንዲሁም እንዳይተረጎም ማድረግ ነው። ፍርድ ቤቶች ሕጉን መተረጎም የሚያስፈልጋቸው በሚሆንበት ወቅት በመሰላቸው ወይም አግባብ ነው ብለው በተረዱት መንገድ ሁሉ መተርጎም የማይገባቸው በመሆኑ ወጥ ወይም ተቀራራቢ ትርጉም ሊያመጡ የሚችሉበትን መስመር ማመልከት የተገባ ነው። ይህንን አፈጻጸምና ትርጉም ወጥ አቅጣጫ ከሚያስዙት ውስጥ አንዱ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ የሚመራባቸውን አጠቃላይ መርሆዎችን እና አላማዎችን በሕጉ ውስጥ በግልጽ ማሰቀመጥ ነው።

እነዚህ መርሆዎች በህገ መንግሰቱ፣ በወንጀል ሕጉ ወይም አገራችን ባጸደቀቻቸው አለም አቀፍ ሰነዶች ውስጥ ተካተው የሚገኙ ቢሆንም በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ መካተታቸው የራሱ ጠቀሜታ አለው። በመርህ ስር ከተካተቱት ድንጋጌዎች ውስጥም እንደ ጥፋተኛ አለመቆጠር፣ በአንድ ወንጀል

በድጋሚ አለመከሰስ/አለመቀጣት፣ በሕግ ፊት እኩል መሆን፣ ያለ በቂ ምክንያት አለመያዝ፣ ኢሰብአዊ አያያዝ ስለመከልከሉ፣ በጠበቃ ስለመወከል፣ ቀልጣፋ ውሳኔ በግልጽ ችሎት ስለማግኘት፣ እውነትን ስለማውጣት፣ ስለእኩልነት፣ ስለጠበቃ ውክልና፣ ሕጋዊነት እና የወንጀል ሕግ የመንግስት መሆኑን ናቸው። መርሆዎቹ ሥነ ሥርአታዊ በመሆናቸውም አለመከበራቸው በሰብአዊ መብት ላይ የራሱን አፍራሽ ውጤት የሚያስከትል ነው። መርሆዎቹ መደንገጋቸው በራሱ ውጤት ላያመጣ የሚችልበትን እድልንም ለመቀነስ መርሆዎቹ በሌሎች ህጎች በተቀመጡበት አግባብ ደግሞ የማስቀመጡ ፋይዳ በስነ ስርአትና ማስረጃ ጉዳይ ላይ እምብዛም እንዳይሆን በፍትሕ ሒደቱ ባይከበሩ ሊከተል ስለሚገባው ውጤትም በሕጉ በተመሳሳይ ተመልክቷል። ለምሳሌ **የተከላካይ ጠበቃ አስፈላጊ በሆነበት ጉዳይ ያለጠበቃ የተደረገ ክርክር እንዳልተካሔደ እንዲቆጠር የሚያደርግ ግልፅ ድንጋጌን** ሕጉ ይዟል። አብዛኛዎቹ በሕገ መንግስት ውስጥ የተመለከቱ በመሆናቸው ዝርዝር ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው አይደሉም።

መርሆዎቹ መካተታቸው ካለው ጥቅም ውስጥ ለአብነትም የሕገ መንግሰቱ ድንጋጌዎችን በወንጀል ጉዳይ ላይ በቀጥታ ተፈጻሚ ማድረግ፣ መርሆዎቹን ሥነ ሥርታዊ በማድረግ ሕጉ የሚተረጎምበትን አግባብ ማመላከት፣ ሕገ መንግሰቱ ውስጥ የተመለከቱትን የሰብአዊ መብቶች የማክበርና የማሰከበር ግዴታን በቀጥታ ለመወጣት እንዲቻል እና የሕገ መንግስቱን ድንጋጌዎች አፈጻጸም ከእለት ከእለት ሥራ ጋር ለማስተሳሰር እንዲቻል መሆኑ ተጠቃሽ ናቸው።

መርሆዎቹ በሕጉ ውስጥ መካተታቸው በተወሰነ መልኩም ቢሆን በሕገ መንግሰቱ የተቀመጡትን አነስተኛ ግዴታዎች ከፍ በማድረግ መብቶች የተሻለ ጥበቃ እንዲያገኙ የማድረግ እድልን ይፈጥራል። ለአብነትም የትርጉም አገልግሎት የማግኘት እና በጠበቃ የመወከልን ፍልጎት በፍርድ ሂደት ላይ ብቻ የሚያስፈልግ ሳይሆን ከፍርድ ሂደቱ በፊት ባሉ ስርአቶችም የሚያስፈልግና አለመሟላቱ የሰብአዊ መብት ጥሰትን ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ በጠበቃ የመወከል መብት በወንጀል የፍትሕ ሂደቱ ሁሉ ሊሟላ የሚገባው እንደሆነ ሕግ ይደነግጋል። በማረሚያ ቤት ያለ ፍርደኛም ከአያያዙ አንስቶ ለይግባኝ፣ ሰበር፣ አመክሮ ወዘተ ጉዳዮች ሰብአዊ መብቱን ባከበር አግባብ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ በዚህ መብት ሊጠቀም ይችላል። በተወሰኑ ጉዳዮች ደግሞ (ለምሳሌ በወጣት ጥፋተኞች ጉዳይ) በጠበቃ መወከል ግዴታ እንዲሆን ያስችላል።

ሕጉ ከያዛቸው መርሆዎች ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀምን የሚመለከተው መርህ ይገኝበታል። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግስቱ መሰረት በአማርኛ ቋንቋ የሚሰሩ ሲሆን የክልል ፍርድ ቤቶችም በየክልሉ የስራ ቋንቋ ይሰራሉ። ሆኖም በክልል አስተዳደሮች ውስጥ የዞን ወይም የወረዳ አስተዳደሮች የሚሰሩበት የተለየ የአስተዳደር ቋንቋ ካላቸው ይኸው ቋንቋ የስራ ቋንቋቸው ይሆናል ማለት ነው። ለምሳሌ በአማራ ክልል የአዊ ዞን አስተዳደር በአገውኛ ሊሰራ ይችላል ማለት ነው።

የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ የሚመራበትን መሰረታዊ መርሆዎች በአንድ ክፍል ውስጥ የተቀመጡ ናቸው። ይሁንና በተለየ ክፍል ለተለየ አላማ ብቻ ሊፈጸም የሚችል ወይም የሚገባው ተጨማሪ (ልዩ) መርህ ሲኖር በሕጉ በተለየ ክፍል ውስጥ እንዲካተት ሆኗል። በዚህ አግባብ በሕጉ ልዩ ክፍል ውስጥ ከተቀመጡት መርሆዎች ውስጥ በወንጀል ውስጥ ገብቶ የተገኘ ወጣት ጉዳይ አመራር መርህ፣ የወንጀል የምርመራ እና የክስ ሂደት የትብብር መርህ፣ የሰበር ጉዳይ መርህ፣ የአማራጭ መንገዶችና አማራጭ ቅጣት መርህ፣ የክስ መመስረት መርህ፣ የቅጣት መርህ ወዘተ ይገኙበታል። እነዚህ መርሆዎች ከአጠቃላዩ የሕጉ መርህ ጋር ተዳምረው በተቀመጡበት ልዩ ክፍል ውስጥ ብቻ የሚፈጸሙ መርሆዎች ናቸው።

ሕጉ መርህን በጠቅላላ እና በልዩ ክፍሉ ውስጥ ያካተተ ቢሆንም በወንጀል ጉዳይ ሌሎች አግባብ ያላቸው የሕገ መንግሰቱም፤ የልዩ ሕጎች ወይም የሌሎች ሕጎች መርሆዎች እንዳግባቡ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉን ለመተርጎም ተፈጻሚ አይሆኑም ማለት ግን አይደለም።

## 8. የሕጉ አላማ

የስነ ስርአትና  የማስረጃ ሕጉን አላማም በተመለከተ ነባሩ የስነ ስርአትሕግ የሚመራበት ግልፅ አላማ ያልነበረው መሆኑ ይታወቃል። ይህ በመሆኑም ከወንጀል መከላከል አንስቶ እስከ ማረምና መልሶ መቀላቀል ድረስ ያለው ተግባር ምን አላማን ለማሳካት እንደሚፈጸም የተለያዩ ጫፎችን የያዙ የተለያየ አመለካከቶች እና ተግባራት እንደነበሩ ይታወቃል። የነበረው ሰፊ ክፍተትና ልዩነት በወንጀል ሕጉ አረዳድ እና አተረጓጎም ላይም ሰፊ አረዳድ እና የትግበራ ልዩነትን ሲያስከትል የቆየ ሲሆን መነሻ ምክንያታቸው ለሁሉም ፈጻሚና ተርጓሚ በእኩል ደረጃ ግልጽ ያልሆኑ የውጪ ልምዶችንና ፅሁፎችን ጭምር ለሕጉ አፈጻጸም እና ትርጉም መጠቀምን ሲያስገድድ ቆይቷል። ይህንን ችግር ለመቅረፍም የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕጉን አላማ በግልጽ ማስቀመጥ የሚያሰፈልግ በመሆኑ የሕጉን አላማ የሚያሳይ ግልጽ ድንጋጌ በሕጉ ውስጥ ተካቷል።

በመሆኑም የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ አላማ ሶስት መሰረታዊ ቁም ነገሮችን ማረጋገጥ እንደሆነ ተመልክቷል። በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጡትን ሰብአዊ መብቶች ማክበርና ማስከበር፣ የወንጀል ፍትሕ ሂደቱ ፍትሓዊነት እና ውጤታማነት (ውጤታማነት ማለት ቅልጥፍና፣ ግልጽነት፣ ተደራሽነት፣ ተጠያቂነት፣ ነጻነትን ያካትታል) በማረጋገጥ እውነትን ማውጣት እና የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ ናቸው። እያንዳንዱ የፍትሕ አካል ኃላፊነቱን ይህንን አላማ በሚያሳካ መልኩ እንዲወጣ ይጠበቃል።

## 9. የተከላካይ ጠበቃ ጉዳይ

በሕገ መንግስቱ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የተከሰሱ ሰዎች ጠበቃ ለማቆም የሚያስችል የገንዘብ አቅም የሌላቸው ከሆነና ፍትሕ ይዛባል ተብሎ ከታመነ በመንግስት ወጪ በጠበቃ የመወከል መብት አላቸው። አሁን ባለው አሰራር በፍርድ ቤቶች መዋቅር ውስጥ የሚገኘው የተከላካይ ጠበቆች ጽ/ቤት ይህንን ኃላፊነት ከሞላ ጎደል እየተወጣ ይገኛል። ይሁን እንጂ የተከላካይ ጠበቆች ጽሕፈት ቤት በፍርድ ቤት ውስጥ የሚገኝ ከመሆኑ የተነሳ በተከሳሾች ዘንድ ነጻ አገልግሎት ይሰጠናል የሚል እምነት ያላቸው ለመሆኑ በእጅጉ ያጠራጥራል። ጽ/ቤቱም የተለያዩ የሎጂሰቲክ ችግሮች ያሉበት በመሆኑም በሚፈለገው ደረጃ አገልግሎቱን ሊሰጥ አልቻለም። ጽ/ቤቱ ሊሰጠው የሚገባው አገልግሎት በሕገ መንግስቱ ለተከሰሱ ሰዎች ካላቸው የመከላከል ሕገ መንግስታዊ መብት አንጻር በሕጉ በተሰጠው ቦታ ልክ መሆን ይገባዋል። ይህ በመሆኑም የተከላካይ ጠበቃ አገልግሎትን በተመለከተ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው የተለየ ትኩረት ሰጥቶት አቅጣጫ አስቀምጧል።

በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የተከላካይ ጠበቃ አገልግሎት የሚያስፈልገው የወንጀል ፍትሕ ሂደቱ በማናቸውም ደረጃ (4.7.1) በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ ነው። በሌላ በኩልም ተከላካይ ጠበቃ የሚያስፈላጋቸው በወንጀል ጉዳይ ለሚከራከሩት ብቻ ሳይሆን በፍትሐብሔርም ጉዳይ ያላቸው እንደሆኑ ፖሊሲው ያመለክታል። በመሆኑም በከባድ ወንጀል ድርጊት ወይም በሰብአዊ መብት መጣስ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ካሳ ለማግኘት በፍርድ ቤት በሚያደርጉት ክርክር ጠበቃ ወክለው ለመከራከር አቅም የሌላቸው ከሆነና በዚህም ፍትሕ ይዛባል በሚል ከታመነ በመንግስት ወጪ ጠበቃ ይመደብላቸዋል።

እነዚህን ከባድ ኃላፊነትን የሚጠይቁ ዝርዝር ተግባራት አሁን ባለው የጠበቃ ጽሕፈት ቤት አደረጃጀት እና አሰራር ማሳካት የማይቻል በመሆኑ የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕጉ ነፃና ገለልተኛ የሆነ የተከላካይ ጠበቃ ጽሕፈት ቤት እንደሚቋቋም ታሳቢ አድርጓል፡፡

## 10. የፍትሕ አካላት ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት

ወንጀልን ከመመርመር አንስቶ ታራሚን በአግባቡ አርሞ ከሕብረተሰቡ ጋር እስከመቀላቀል ባለው ሂደት ውስጥ በቀጥታ ተሳታፊ የሚሆኑ የፍትሕ አካላት ማለትም ፖሊስ፣ አቃቤ ሕግ፣ ፍርድ ቤት፣ ማረሚያ ቤት እና  የተከላካይ ጠበቃ ተቋም በጋራ፣ በወል እንዲሁም በተናጠል ስለሚያከናውኑት ተገባር በሕጉ ውስጥ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ በጋራ የሚከናወኑት ተጋባራት የየተቋማቱ ነጻነት እንደተጠበቀ ሆኖ ሁሉንም የፍትህ አካላት በሚያገናኛቸው ጉዳይ ላይ ምን ሊሰራ እንደሚገባ የሚያመለክት ነው፡፡ ለምሳሌም ሁሉም የፍትሕ አካላት በተናጠል (የወል ኃላፊነት) በወንጀል ጉዳይ ጥናትና ምርምር የማድረግ፣ ዘመናዊ አሠራሮችን የመዘርጋት ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት ይህንኑ የጥናትና ምርምር ተግባር ሁሉም ተቋማት በአንድነት ሊያከናውኑት ይችላሉ ማለት ነው፡፡

ሕጉ የፍትሕ አካላትን የተናጠል፣ የጋራ ወይም የወል ኃላፊነቶችን ያመለከተ ቢሆንም ተግባርና ኃላፊነታቸው በዚህ ዝርዝር ላይ የተመለከተው ብቻ ነው ማለት ግን አይደለም፡፡ ሕጉ ውስጥ የተመለከቱት ተግባራ በሥነ ሥርአትና በማስረጃ ሕጉ  ላይ በተመለከቱት የፍትሕ አካላቱ ኃላፊነቶች ጋር የታያያዙትና ሊቀሩ/ሊቀነሱ የማይችሉት አነስተኛ ተግባራት ብቻ ናቸው፡፡ ለምሳሌ መመርመር፣ መፍረድ፣ ታራሚን መልሶ መቀላቀል ተግባራት እንደቅደም ተከተላቸው በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ ሊቀሩ የማይችሉ የፖሊስ፣ የፍርድ ቤት እና የማረሚያ ቤት ተግባራት ስለሆኑ በዚህ ሕግ ውስጥ እንዲካተቱ ሆነዋል፡፡

በመሆኑም በሕጉ ውስጥ በዚህ መልኩ የተመለከቱት ተግባራት/ኃላፊነቶች እያንዳንዱ ተቋም በተቋቋመበት ሕግ ወይም በሚቋቋምበት ሕግ የተመለከቱትን/የሚመለከቱትን ተግባራትና ኃላፊነቶች የማይተኩና እና የማይቀንሱ ናቸው፡፡ በሥነ ሥርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ የተመለከቱት ተግባራት ከሥነ ሥርአትና ማስረጃ ሕጉ ወሰን ጋር የተያያዙት ብቻ በመሆናቸው ተግባራቱ በዚሁ ልክ መዘርዘራቸው በሌላ ሕግ ወይም ለሌላ ተግባር ለተቋማት የሚሰጡ ተግባራትን አያስቀርም፡፡ እያንዳንዱ ተቋም በተቋቋመበት ወይም በሌላ ሕግ የተሰጠውን ተጨማሪ ተግባር (ለምሳሌ ለፖሊስ አግባብ ባለው ሕግ የተሰጠውን ዝርዝር የወንጀል መከላከል ተግባራትን) እና የየተቋማቱን ነጻነት አይነካም፣ አይተካም፡፡ ሌሎች የተናጠል

ተግባራት የወልና የጋራ ተግባራትን ተከትለው ተዘርዝረው ተቀምጠዋል፡፡ በያንዳንዱ የፍትህ አካል በተናጠል ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባራት (ለምሳሌ ፖሊስን በተመለከተ የወንጀል ክትትል ማድረግ፣ መጥሪያ የማድረስ፣ ብርበራና ፍተሻ የማካሔድ ወዘተ) በተለየ ዝርዝር ለብቻው እንዲቀመጥ ሆኗል፡፡ ይህ የወል እና የተናጠል ተግባራት ዝርዝር በወንጀል ምርመራ፣ ክርክርና ውሳኔ አሰጣጥ ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ሌሎች ተግባራት አይተካም፡፡

እነዚህ ተግባራትም በሁሉም የፍትሕ አካላት ሊከናወኑ የሚገባቸው ወይም በአንድ የተለየ የፍትሕ አካል ብቻ የሚከናወኑ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የፍትህ አካላቱ እንዳግባቡ ተቋማዊ ወይም/እና የሙያ ነጻነት ያላቸው ከመሆኑ አንጻር የተግባራቱ መዘርዘር በጋራ ሊያከናውኗቸው የሚችሏቸውን ተግባራት በግልጽ እንዳሰፈላጊነቱም በጋራ እቅድ ለይተው እንዲያሰቀምጡ ያግዛቸዋል፡፡ በመሆኑም በሁሉም የፍትሕ አካላት ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባራት የወል ተግባራት ተብለው ተዘርዝረዋል፡፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥም እንደ ዘመናዊ እንዲሁም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ አሰራር መዘርጋትና መተግበር፣ የወንጀል መረጃና ስታትስቲክስን  መያዝ ማደራጀት መተንተን እና መጋራት፣ ምቹ የተገልጋይ መስተንግዶን ማመቻቸት፣ በጋራ ጉዳዮች ላይ በጋራና በትብብር መንፈስ መስራት፣ የወንጀል ቅጣት አላማውን ስለማሳካቱ ማረጋገጥና የመሳሰሉት ተመልክተዋል፡፡

በፍትሕ ሂደቱ ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት ከላይ ከተመለከቱት አካላት በተጨማሪ በፍትህ አሰጣጥ ሒደት የተያዙ ሰዎች፣ የተከሰሱ ሰዎች፣ የወንጀል ተጎጂዎች፣ ምስክሮች፣ አስተርጓሚዎች ወዘተ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ አካላት በሒደቱ እንዲያከናውኑ የሚጠበቅባቸው ተግባራት ያሉ ከመሆኑም በላይ የየራሳቸው መብትና ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ መብትና ኃላፊነታቸው በሕጉ ውስጥ በግልፅ ሊደነገግ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ተግባራት፣ መብትና ኃላፊነቶች የፍትሕ አካላት እንዲያከናውኑ በሚጠበቅባቸው ተግባራት፣ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በሚመራባቸው መርሆዎች እና አላማዎች ውስጥ በሌላ አገላለጽ የተቀመጡ በመሆኑ ለብቻቸው መደንገግ አላስፈለገም፡፡

## 11. የወንጀል ምርመራ ተግባራት

የወንጀል ምርመራ የሚጀምረው በጥቆማ፣ በአቤቱታ፣ በፖሊስ ምልከታ፣ ክትትል ወይም በጥናት ነው፡፡ የወንጀል ምርመራ ስራ በዐቃ ህግ የሚመራ ቢሆንም በዋነኛነት በፖሊስ አማካኝነት የሚከናወን ነው፡፡ ጥቆማው ለፖሊስ ወይም ለአቃቤ ሕግ ሊቀርብ ይችላል፡፡ የወንጀል አቤቱታውን የተቀበለው አካል

ወንጀልን የማጣራት ኃላፊነት በሕግ ያልተሰጠው ከሆነ ጥቆማውን/አቤቱታውን ለሚመለከተው አካል ማስተላለፍ ይጠበቅበታል። በተመሳሳይም አቃቤ ህግ የደረሰውን ጥቆማ ወንጀል ለመፈፀሙ አመላካች የሆነ በቂ መረጃ ያለው ለመሆኑ ከተገነዘበ የወንጀል ምርመራ እንዲጀመር ጉዳዩን ለፖሊስ ያስተላልፈዋል። ይሁን እንጂ ፖሊስ ማንኛውንም የተጀመረ ምርመራ ምርመራው እንደተጀመረ ለአቃቤ ህጉ ከማስታወቅ አንስቶ ምርመራው በየጊዜው የደረሰበትን ደረጃ እና ስለተወሰዱ (ስለሚወሰዱ) እርምጃዎች ለአቃቤ ሕጉ ተገቢ በሆነው መንገድ ማሰታወቅ ይኖርበታል። አቤቱታ ሲቀርብም ፖሊስ ወዲያውኑ ምርመራ የሚጀምር እንደሆነና ዝርዝሩን ግን ወዲያውኑ ለአቃቤ ሕግ ማስታወቅ እንደሚገባው የሚያስገነዝቡ ድንጋጌዎች ተካተዋል። በመሆኑም የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕጉ አቃቤ ሕግ በወንጀል ምርመራ ሂደት ከመጀመሪያው ጀምሮ በቀጥታ እውቀት የሚሳተፍበት፣ ምርመራውን የሚከታተልበት ከሕግ አንፃር የሚመራት ሥርዐት እንዲዘረጋ ያደርጋል። መርማሪው በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የምርመራ ሥራ እየሠራ በየደረጃው ከዐቃቤ ሕጉ ጋር እየተገናኘ እና ከሕግ አንጻር የዓቃቤ ሕግን ምክር እያገኘ የምርመራ ስራው ሁሉ ሕጋዊነትን የተከተለ እንዲሆን የሚያስችሉ ድንጋጌዎች ተካተዋል። ይህም በስራው ላይ በቅብብል የተነሳ ሊደርስ የሚችለውን ምልልስና በዚህም የሚባክነውን ጊዜ የሚያሳጥር ከመሆኑም በላይ የምርመራ ስራው በተሻለ ጥራት እንዲመራና ህጋዊነቱንም ያልሳተ ለመሆኑ የተረጋገጠ እንዲሆን ያግዘዋል። ይህ አሰራር በወንጀል ፍትህ ፖሊሲው አቅጣጫ ከተሰጠባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው።

የወንጀል ምርመራን ለመጀመር ማንኛውም ሰው ወንጀልን በአቅራቢያው ለሚገኝ ፖሊስ ወይም ስልጣን ያለው የህግ አስከባሪ አካል የመጠቆም መብት ያለው ለመሆኑ በሥነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ ተመልክቷል። በሌላ በኩል ወንጀልን የማስተዋቅ ግዴታ በስነ ስርአትና የማስረጀ ሕጉ ውስጥ ማካተት አስፈላጊ ባለመሆኑ ቀደም ሲል የነበረው ድንጋጌ ቀሪ ሆኗል። ይህ ማለት ግን ወንጀልን የማስታወቅ ግዴታ በአጠቃላይ ይቀራል ማለት ሳይሆን ይህንን ግዴታ መኖር የሚፈልጉ ሕጎች በወጡ ቁጥር በዛው ፍሬ ህግ ላይ የሚደነገግ በመሆኑ ብቻ የታለፈ ነው። አሁን በስራ ላይ ያሉትም ሕጎች በተመሳሳይ ይህንን ግዴታ መጣላቸው የሚታወቅ ነው።

ስለሆነው ጉዳዩ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ጉዳይ ከሚሆን በፍሬ ሕጎች ውስጥ የሚካተት በመሆኑ ከስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ ውጪ ሆኗል።

በሥራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት የተለያዩ የወንጀል ጉዳዮች አላስፈላጊ በሆነ ሁኔታ በወንጀል ፍትሕ ሂደቱ እንዳይገቡ መከላከል በሚያስችል እና ከገቡ በኋላም ሥርዓት ባለው ሁኔታ መፍትሔ እንዲያገኙ በሚያስችል አኳኋን ብቃት ባለው መልኩ የተደራጀ አይደለም። የሕጉ አንቀጽ (22) እንደሚደነግገው ለፖሊስ የሚደርሱ የወንጀል አቤቱታዎች ወይም ክሶች ሁሉ በማጣራት/በምርመራ ሂደት ውስጥ እስከመጨረሻው ማለፍ እንዳለባቸው የሚያስገድድ ሲሆን በማንኛውም ሁኔታ ከምርመራ ውጪ ወይም የምርመራ ሂደት ሳይጠናቀቅና ውጤቱ ሳይታወቅ ከሂደቱ ውጪ መፍትሔ የሚያገኙበትን ሁኔታ አልተመለከተም። በተጨማሪም አቤቱታ ወይም ክስ የቀረበበት ጉዳይ የወንጀል ጉዳይ ቢሆንም እንኳን ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች በሕጉ ተለይተው ስላልተቀመጡ የሕዝብ ጥቅም በከፍተና ደረጃ ከሚጎዳባቸው ጉዳዮች ይልቅ ቀላል የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግና የምርመራ ሥራ መጀመር ያጋጥማል። ከዚህም በተጨማሪ አቤቱታ ወይም ክስ ከቀረበባቸው ጉዳዮች መካከል አብዛኞዎቹ የወንጀል መዛግብት የምርመራ ሂደትን አልፈው ለዓቃቤ ሕግ ውሳኔ ይቀርባሉ። ለዓቃቤ ሕግ ለውሳኔ ከሚቀርቡ የምርመራ መዝገቦች ውስጥ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት የወንጀል ድርጊት አይደለም የሚባልባቸው፣ ከምርመራ በፊት በእርቅ ቢያልቁ ተመራጭ የሚሆኑ፣ ማስረጃ የተሟላ ባለመሆኑ የማያስከስሱ፣ በሕግ ተቀባይነት የሌላቸው ማስረጃዎች የሚቀርቡባቸው እና የመሳሰሉ ጉድለቶች ያሉባቸው ሁሉ ይገኙባቸዋል።

ከላይ የተጠቀሰው ችግር እንዲከሰት ከሚያደርጉ ሁኔታዎች መካከል አንዱ የምርመራ ሥራ በሕግ ምክር አለመደገፉ ነው። ሥራዎች በጋራ በማይሰሩበት ሁኔታ አብዛኛው የወንጀል ምርመራ ተግባራት ያለ ሕግ ምክር እና ያለ ዓቃቤ ሕግ ተሳትፎ የሚከናወኑ በመሆኑ የምርመራ ሥራ የመርማሪው ኃላፊነት ብቻ ተደርጎ ይታሰባል። ከዚህም የተነሳ የወንጀል ምርመራ ሥራ ያለዓቃቤ ሕግ ተሣትፎ በመርማሪ ፖሊስ ብቻ ተከናውኖ ስለሚጠናቀቅ በምርመራ ደረጃ ወዲያውኑ ሊቋረጡ የሚችሉ ጉዳዮች አላስፈላጊ ጉልበት፣ ወጪ እና ጊዜ ከወጣባቸው እና የተጠርጣሪዎች መብቶችና ነጻነቶች ከተጣሱ በኋላ በጅምላ ወደ ዓቃቤ ሕግ እንዲቀርቡ ይደረጋሉ። ዓቃቤ ሕግ ዘንድ ቢቀርቡ አዋጭ ናቸው የሚባሉት እና የወንጀል ድርጊትን የሚያቋቋሙ ጉዳዮችም ቢሆኑ ብዙውን ጊዜ በቂ የሆነ ማስረጃ ሳይሰበሰብባቸውና ሙያዊ ምክር ሳይሰጥባቸው ለአቃቤ ሕግ ስለሚቀርቡ፣ በዓቃቤ ሕግና በመርማሪ አካላት መካከል ተደጋጋሚ መፃፃፍ እንዲኖር በዚህም ምክንያት አላስፈላጊ የሆነ የጊዜ ቀጠሮ እንዲጠየቅባቸው ሲደረግ በተግባር ይታያል። በሥራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት ከምርመራ በፊትም ሆነ በምርመራ ወቅት

እንዲሁም ከምርመራ በኋላ የማያዋጡና የመንግሥትን እና የሕዝቡን ሀብት እና ጊዜ የሚያባክኑ እንደዚሁም የዜጎችን መብቶች እና ነጻነቶች ሊጥሱ የሚችሉ ጉዳዮች ሲያስተናግድ ቆይቷል፡፡

የኢፌዴሪ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ ከወንጀል ምርመራ ጋር ተያይዘው ያሉና ከላይ የተብራሩትን አጠቃላይ ችግሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት የወንጀል ምርመራ ዓላማና መርህ፣ በወንጀል ምርመራ ሂደት በሕግ ሊደነገጉና ሊተገበሩ ስለሚገባቸው አዳዲስ አሠራሮች፣ በወንጀል ምርመራ ሂደት በፍትሕ አካላት ዘንድ ስለሚኖር ትብብር እና ሚና ግልጽ የሆነ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡ የወንጀል ምርመራ ዓላማና መርህ በሚያብራራው የፖሊሲው ክፍል የወንጀል ምርመራ ዓላማ በአጠቃላይ ወንጀልን የማወቅ፣ ወንጀል እንዳይፈጸም የማስቆም፣ ወንጀሉ ከተፈጸመ ጉዳቶችን የመቀነስ፣ የወንጀል ኢላማ የሆኑ ሰዎች፣ ንብረቶች ወይም ጥቅሞችን የመከላከል፣ ወንጀል ፈጻሚዎችን ለሕግ የማቅረብ ወይም የወንጀል ተጎጂዎችን መብቶችና ጥቅሞችን የማስከበር እንደሆነ፤ በተለይም በወንጀል ጉዳይ ላይ መረጃ/ ማስረጃ መፈለግን፣ ማግኘትን፣ መተንተንን፣ ማደራጀትን፣ ማኖርንና ለሚፈለገው አላማ ዝግጁ ማድረግን የሚያጠቃልል እንደሆነ አሰቀምጧል፡፡

በዚህ ረገድ ፖሊሲው በወንጀል ምርመራ ሂደት ውስጥ የሚስተዋሉትን መሠረታዊ የሆኑ የአፈፃፀም፣ የብቃትና የሕጋዊነት ችግሮች በማስወገድ ውጤታማ የወንጀል ምርመራን ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ የተሟላ የአሠራርና የሕግ መሠረት መጣል የሚያስችሉ ቁልፍ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል፡፡ አነዚህ አላማዎች በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ በግልፅና በዝርዝር እንዲካተቱ ይጠበቃል፡፡

በዚህም መሠረት ከወንጀሎቹ የተለየ ባህርይና የአፈፃፀም ውስብስብነት የተነሳ የመንግሥትንና የሕዝቡን ደኅንነትና መሠረታዊ ጥቅሞች ለአደጋ የሚያጋልጡ ወንጀሎችን ከተቻለ ከመፈፀማቸው በፊት አስቀድሞ ለመቆጣጠር፣ በመፈፀም ላይ የሚገኙትንም አስከፊ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ለማስቆም እና ተፈፅመው በተገኙም ጊዜ ፈፃሚዎችን በበቂ ማስረጃ አስደግፎ ለማውጣት የሚያስችሉ ዘመናዊ የአሠራር ዘዴዎች መከተል እንደሚገባ ፖሊሲው ያመላክታል፡፡ ከአሠራር ዘዴዎቹም ጋር በተያያዘ በወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎች ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉትን የመብት ጥሰቶች ከወዲሁ ለመቆጣጠር የሚረዱ የአሠራር ሥርዓቶች መዘርጋት እንደሚያስፈልግ በፖሊሲው ተመልክቷል፡፡

ከዚህ አንፃር የወንጀል የምርመራ ሥራ ውጤታማ እንዲሆን ማስረጃ መር የምርመራ ዘዴን መከተል እንደሚገባ ሕጉ በግልጽ ደንግጓል፡፡ እጅግ የተለዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የምርመራ ስራም በህጉ

መጽሐፍ ሁለት በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሰረት መፈጸም ያለበት መሆኑ ምርመራን ማስረጃ መር እንዲሆን ያደርገዋል። ከዚህ በተጨማሪም ምርመራ ውጤታማ እና ፍትሓዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ሥራው በመርማሪና በዐቃቤ ሕግ  በጋራ መከናወን ያለበት መሆኑ፤ የምርመራ ሥራውን የመምራት እና የመከታተል ኃላፊነት የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ስለመሆኑ፤ ዐቃቤ ሕግ ለሚመለከተው መርማሪ አግባብ ያለው ትእዛዝና ምክር የመስጠት የምርመራ ሂደት ሕጋዊነት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ፤ መርማሪም ከዐቃቤ ሕግ የሚሰጡ ትዕዛዞችና ምክሮችን ተቀብሎ የመፈጸምና የማስፈጸም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፤ በወንጀል በተጠረጠሩ ሰዎች ላይ ሕግን በተከተለ መንገድ ክትትል ማድረግ እና ማስረጃ ለመሰብሰብ ሲባል በመካከላቸው ሰርጎ መግባት የሚቻል ስለመሆኑ፣ ሊፈፀም የተቃረበ፣ በመፈፀም ላይ የሚገኝን ወይም የተፈፀመ ወንጀልን ለማውጣት እና በጉዳዩ ላይ ማስረጃ ለማሰባሰብ ሲባል አግባብነት ያላቸውን ሕጐች ተከትሎ የተጠርጣሪዎቹን የግል መገናኛ ዘዴዎች መጥለፍ ስለመቻሉ፣ ከባድና ውስብስብ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን የሚሰጡ የወንጀል ተጠርጣሪዎችን በግልፅ በሰፈሩ የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ሊቀርብባቸው ከሚችል ክስ ነፃ እንዲሆኑ፣ በወንጀል ጉዳይ ላይ ምስክርነት የሚሰጡ ሰዎች ሊደርሱባቸው ከሚችሉ የተለያዩ ጥቃቶች ለመከላከል ሲባል እንደሁኔታው አስፈላጊ የሆነ ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገባ ስለመሆኑ፣ እንደሽብርተኝነት፣ ሙስና፣ በሕገመንግሥቱና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ የሚፈፀም፣ በተደራጁ ቡድኖች የሚፈፀም፣ በሴቶችና ሕፃናት የመነገድ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ጋር በተገናኘ  ለወንጀሉ መፈፀሚያነት ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም ከወንጀሉ ተግባር የተገኙ ገንዘቦችንና ንብረቶችን በሕግ አግባብ ማገድ የሚቻል መሆኑን ወዘተ በምርመራ ተግባራት የሚከናወኑ እንደሆነ ፖሊሲው ያስገነዝባል። የስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ይህንን አቅጣጫ በመከተል ዝርዝር ድንጋጌዎችን ያካተተ ከመሆኑም በላይ የነባሩ ሕግ ከምርመራ ስራ ጋር በተያያዘ ያለበትን ችግር ለመቅረፍ ጥረት አድርጓል።

ከፍ ሲል በዝርዝር በተመለከተው አግባብ ከወንጀል ምርመራ ጋር ተያይዞ በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ እንዲካተቱ ከተደረጉ አብይ ጉዳዮች አንዱ የወንጀል ምርመራ ስለሚመራበት ሁኔታና በዐቃቤ ሕግና በፖሊስ መካከል የወንጀል ምርመራን አስመልክቶ የሚኖረውንግንኙነት የሚመለከተው ድንጋጌ አንዱ ነው።

በነባሩ ሕግ አንድ  ክስ ወይም  የክስ  አቤቱታ  ለፖሊስ ከቀረበ  በኋላ  ፖሊስ  ምርመራውን አጠናቅቄያለሁ  ብሎ  ሲያምን የተጠናቀቀ  የምርመራ  መዝገብ  ለዐቃቤ  ሕጉ  የሚያቀርብ በመሆኑ

ዐቃቤ ሕግ በምርመራ ሥራ ላይ ያለው ተሳትፎ አነስተኛ እንደሆነ የተስተዋለ መሆኑን ከፍ ሲል ተገልጿል። ነገር ግን ይህ አሠራር ላላስፈላጊ የመዝገብ ምልልስ፣ የጊዜ እና ሃብት ብክነት የሚዳርግ በመሆኑ ውጤታማነት እና የተፋጠነ ፍትሕ አሰጣጥ ላይ ችግር ሲፈጥር ቆይቷል። አሰራሩም የሁለቱንም አካላት እንቅስቃሴ ለመከታተል እና ለመገምገም በሚያስችል አግባብ ተቀርጾ የተሟላ ግልጽነት እና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ማድረግ ያስፈልጋል። ችግሩን ለመቅረፍም የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው በቁጥር 3.3 ላይ በግልፅ ባስቀመጠው መልኩ በወንጀል ምርመራ ተግባር ላይ ፖሊስ እና አቃቤ ሕግ በጋራ መሳተፍ ይገባቸዋል። የጋራ ስራ ወንጀል ፈፃሚን ለይቶ ለሕግ ማቅረብ፣ መረጃን ወይም ማስረጃን ማፈላለገ፣ ማገኘትን፣ መተንትን፣ ማደራጀት፣ ለክስ ወይም ለሌላ አላማ መጠቀምንና አግባብ ላላቸው አካላት (ለምሳሌ ለአሰታራቂ) ማስረከብ ሂደቶች ሊያካትት ይችላል። በዚህ መሰረት የስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ምርመራ የሚደረግባቸውን ጉዳዮች፣ አላማውን፣ በምርመራ የሚሳተፉ አካላትን ሚና፣ ተፈፃሚ የሚሆኑ መርሆዎች እና ተዛማጅ ጉዳዮችን አካቷል።

ይህ ማለት ግን አቃቤ ሕግ በሁሉም የምርመራ ስራዎች ውስጥ ይሳተፋል ማለት ሳይሆን ተሳትፎው የወንጀል ምርመራ ስራን በመምራትና በመከታተል ብቻ የሚገለጽ ነው የሚሆነው። የወንጀል ስራን መምራትና መከታተል ተቋምን እስከ ማዋሃድ የሚደርስ የተሳሳተ ትርጉም ሲሰጠው የሚስተዋል በመሆኑ ይህንን ግልጽ ለማድረግ ሕጉ ግልጽ ድንጋጌን ይዟል። በመሆኑም የወንጀል ምርመራ ስራ የሚጀምረውም ሆነ የሚመራው በፖሊስ ሲሆን አቃቤ ሕግ የምርመራውን ስራ በተመለከተ የመምራትና እና የመከታተል ተግባራትን ያከናውናል።

በመሆኑም አቃቤ ሕግም በምርመራ ሂደት ውስጥ የሚኖርበት ሃላፊነት ለምርመራው የሚያስፈልጉ የሕግ ምክርና አስተያየት ለመርማሪው በመስጠት ምርመራ በሕግ መሰረት መከናወኑን ማረጋገጥ፣ ምርመራውን የመከታተል፣ ለመርማሪው አግባብ ያለውን ትእዛዝ ምክርና ድጋፍ የመስጠት፣ ምርመራው በአግባቡ መከናወኑን የመምራትና ሕጋዊነቱን የማረጋገጥ እንዲሆን የሚያስችሉ ድንጋጌዎች ተካትተዋል። መርማሪም ከምርመራው ጋር በተያያዘ ከዐቃቤ ሕጉ የሚሰጥ ማንኛውንም ምክርና ትዕዛዝ የመፈጸምና የማስፈጸም ግዴታ እንዳለበት በግልጽ በሚደነግግ መልኩ በረቂቁ የተካተተ ሲሆን ምናልባት መርማሪ በዚህ ዙሪያ ቅሬታ ቢኖረው ለቅሬታውን ሚመለከተው የዓቃቢ ሕግ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ የሚችልበት መንገድም ተደንግጓል።

በምርመራ ክፍል ሌላው የተመለከተው ጉዳይ የምርመራ ጊዜን የሚመለከተው ድንጋጌ ነው። የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው የምርመራ ተግባራት የሚጠናቀቁበት ጊዜ ሊቀመጥ እንደሚገባው ባሰቀመጠው አቅጣጫ መሰረትም የወንጀል ጉዳዮች እንደክብደታቸው ደረጃ የሚጠናቀቁበት የጊዜ ገደብም ተቀምጧል። ለዚህም አጋዥ የሚሆን የምርመራ ተግባርን ፍትሐዊነት፣ ግልፅነትና ቀልጣፋነት እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጡ የጉዳይ አሰተዳደር ስርአት በፖሊስም ሆነ በጠቅላይ አቃቤ ህግ እንደሚወጡ ይጠበቃል።

የወንጀል ምርመራ የሚጀምርበት ሌላው መንገድ ጥቆማ ነው። ጥቆማን በተመለከት የወንጀል ጥቆማ በሁለት አይነት መንገዶች ሊቀርብ እንደሚችል ተቀምጧል። አንደኛ አይነት **ጥቆማ ከወንጀል ፍሬ የሚገኝን** ጥቅም ለመካፈል በማሰብ የሚቀርብ ጥቆማ ነው። ይህ ጥቆማ በማናቸውም ሰው ሊቀርብ የሚችል ሲሆን ጠቋሚው ሊያገኝ ስለሚችለው የተለየ የጥቅም አይነት እና መጠን በሌላ ፍሬ ህግ ወይንም የጠቅላይ አቃቤ ሕግ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሚፈጸም ነው። ሌላው ጥቆማ ከዚህ ውጪ በራስ ተነሳሺነት የአገሪቷ የወንጀል ሕግ ተከብሮ ከማየት ፍልጎትና መብት በመነሳት ወይም ህግ በጣለው ግዴታ የተነሳ የሚቀርብ ጥቆማ ሊሆን ይችላል።

በሂደቱም በማናቸውም መልክ የቀረበን ጥቆማ ጥቆማው የቀረበለት አካል ጥቆማውን አልቀበልም ለማለት የማይቻል ለመሆኑና ጥቆማዎች ወይም አቤቱታዎች ሁሉ መመዝገብ የሚገባቸው ለመሆኑ፣ አቤቱታውን የተቀበለው ተቋም በወንጀል ጉዳይ ስልጣን የሌለው ቢሆንም እንኳን ጥቆማውን ለሚመለከተው ፖሊስ ተቋም ማሰተላለፍ የሚገባው ለመሆኑ፣ ፖሊስም ጥቆማው/አቤቱታው እንደደረሰው ወዲያውኑ የመጀመሪያ ማጣራት ማድረግና ሂደቱ መጀመሩን ለአቃቤ ሕግ ወዲያውኑ ማሳወቅ ይገባዋል። የወንጀልን ጥቆማ የተቀበለ መርማሪም ምንጊዜም ቢሆን የመጀመሪያ ማጣራት ማድረግ የሚገባው ለመሆኑ፣ በዚህ ማጣራት ሂደትም ጉዳዩ በእርግጥ ወንጀል ለመሆኑ፣ ጉዳዩ ወንጀል ከሆነና በጉዳዩ ላይም ስልጣን ያለው ከሆነም ጉዳዩ የሚመራበትን መንገድ (የእጅ ከፍንጅ፣ ደንብ መተላለፍ፣ ከባድ ጉዳይ…) እንዲለይ ሕጉ ግድ ይላል።

በወንጀል ህጉ ውስጥ በግል አቤቱታ ብቻ የሚያስቀጡ ወንጀሎች የተደነገጉ መሆናቸው ይታወቃል። እነዚህ ወንጀሎችን በተመለከተም ምርመራውን ለማከናወን አቤቱታው እንዴት፣ በማንና ለማን ሊቀርብ እንደሚችል በሥነ ሥርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ መደንገግ የሚያስፈልግ ነው። ይህንኑ ጉዳይ የሚመሩ

ድንጋጌዎች በሕጉ ውስጥ የተካተቱ ሲሆን ወንጀሎቹ በግል ተበዳይ የግል ፍላጎት ላይ ተመስርተው የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ከመደበኛው ወንጀሎች በልዩ ሁኔታ ስለሚታዩ ስርአታቸውም በዛው ልክ ጠበብ ብሎ ተቀምጧል፡፡ ለምሳሌም በስልክ የቀረበ የግል አቤቱታ በአስር ቀናት ውስጥ በግንባር በፅሁፍ ሊቀርብ እንደሚገባው እንዲሁም አቤቱታውን በማናቸውም ጊዜ ማንሳት የሚቻል ቢሆንም በዚህ መልኩ የተነሳ አቤቱታ በድጋሚ ሊነቀሳቀስ የማይገባው ለመሆኑ ተደነግጓል፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረታዊ መነሻ ጉዳዮቹ የግል ስለሆኑ የሚንቀሳቀሱትም ሆነ የሚቀጥሉት በግል ተበዳይ ውሳኔ በመሆናቸው በሂደቱ የሚፈጠሩ ክፍተቶች ሂደቱን ባለመቀጠል ጉዳዩን በግል ለመያዝ ወይም ለመጨረስ መመረጡን ያመለክታሉ በሚል እሳቤ የተካተቱ ናቸው፡፡ ከሌሎች ጉዳዮች በተለየ የግል አቤቱታ ጉዳይ የሚመራው የሕብረተሰቡ አጠቃላይ ፍልጎትን በተለይ ለማስጠበቅ ሳይሆን የተጎጂን የግል ፍላጎት ለማስጠበቅ ነው፡፡ በመሆኑም የግል አቤቱታ አቃራቢ ጉዳዩን ባልተከታተለው መጠን ጉዳዩን በአማራጭ መንገዶችና መፍትሔዎች ለመጨረስ እንዳሰበ የሚገመት መሆኑን ታሳቢ ያደረጉ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡

በምርመራ ስራ ውስጥ ሊያጋጥሙ ከሚችሉት ጉዳዮች ውስጥ ሌላው የሃይል አጠቃቀምን የሚመለከተው ጉዳይ ነው፡፡ የምርመራ ስራ ሳይንስን እንዲከተል የሚጠበቅ ቢሆንም በተወሰኑ ሁኔታዎች ኃይልን መጠቀምን ግድ የሚሉ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ ኃይል መጠቀምን የሚመለከቱ ጉዳዮች በርካታ በመሆናቸው ዝርዝራቸው በሌላ ሕግ በዝርዝር የሚመለከት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በምርመራ ወቅት ሊያገጥም የሚችልን ሁኔታ ለመቆጣጠር በሚያስችል መልክ በዚህ ክፍል ውስጥ ኃይልን መቼ እና እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት ከወንጀል ምርመራ ጋር በተያያዘ ኃይልን መጠቀም የሚችለው መርማሪ ሆኖ በምርመራ ወቅት ተመጣጣኝ ኃይል ተጠርጣሪን ለመያዝ ፣ለብርበራ እና በልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴ ብቻ ሆኖ የሚጠቀመውም ኃይል ለሌላ አላማ ሳይሆን የምርመራ ተግባሩን ለማከናወን ብቻ የሆነ፣ ከገጠመው ተቃውሞ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ፣ የምርመራ ተግባርን በሌላ መንገድ ማከናወን የማይችል በመሆኑ ይህንኑ ኃይል መጠቀም የግድ አስፈላጊ ሲሆንና ሌላ አማራጭ መንገድ የሌለ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

## 12. ማስረጃ አሰባሰብ

የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ፖሊስ በወንጀል ጉዳይ ምርመራ ሂደት ውስጥ በዋነኛነት ማሰረጃን ከተከሳሽ ውጪ በሆነ አግባብ በመሰብሰብ እውነቱ ላይ እንዲደርስ ይጠብቃል፡፡ ስለዚህም ወንጀል ተፈፀመ በተባለ

ቁጥር አስቀድሞ ተጠርጣሪን በመያዝ ምርመራ መጀመር ተቀዳሚ እና ተመራጭ የማስረጃ ማሰባሰቢያ መንግድ ባለመሆኑ ማስረጃ በተቻለ መጠን ከተጠርጣሪ ውጪ ለሚሰበሰብበት መንገድ ሕጉ ቅድሚያ ይሰጣል። ፖሊስ ተጠርጣሪን ከመያዙ በፊት አስቀድሞ ማስረጃ ማሰባሰብ ያለበት ሲሆን በማስረጃ ማሰባሰብ ሂደት ውስጥም የምስክርን ቃል ስለሚቀበልበት ሁኔታ፣ ብርበራና ፍተሻ ስለሚደረግበት ሁኔታ፣ ከተጠርጣሪ ውጪ በሌላ ሰው ወይም በመንግሰት የሚገኝን ማስረጃ ስለሚቀበልበት ሁኔታ፣ በልዩ ሁኔታ ማስረጃ ስለሚሰበሰብበት እና በመጨረሻም ከተከሳሽ ማስረጃ ስለሚቀበልበት ሁኔታም በዚሁ ቅደም ተከተል ተደንግጓል። እጅግ የተለየ ሁኔታ ካገጠመ በስተቀር የወንጀል ምርመራ ስራው ሊመራ የሚገባውም በሕጉ ላይ በተቀመጠው (ከዚህ በታች በተቀመጠው) ቅደም ተከተል ብቻ ነው። ቅደም ተከተሉም የምስክርን ቃል መቀበል፣ ብርበራና ተያያዥ ጉዳዮችን፣ የምርማሪ ምልከታ፣ ከሶስተኛ ወገን የሚገኝን ማስረጃ፣ የልዩ አዋቂ ቃል መቀበልን፣ ናሙናና ተያያዥ ጉዳዮችን፣ የልዩ ምርመራ መንገዶችንና ከተጠርጣሪው ቃል መቀበልን የሚመለከቱትን ያካትታል።

በምርመራ ስራው መጀመሪያ ከሚከናወኑት ተግባራት ውስጥ የምስክር ቃልን መቀበል ይገኝበታል። ምስክርነትን በተመለከተ በመሰረቱም ሁሉም ሰው ምስክር ለመሆን ብቃት እንዳለው ሕጉ ይገምታል። ሁሉም ሰው ለመመስከር ብቃት እንዳለው ብቻ ሳይሆን የመመስከር ግዴታም ያለበት ለመሆኑም የህጉ መነሻ ነው። ከፍትሐብሔር ጉዳይ በተለየ መልኩ በልዩ ሁኔታ እስካልተመለከተ ድረስ በወንጀል ጉዳይ ምስክርነት ግዴታ ነው። ስለሆነም በመርህ ደረጃ የግዴታ ምስክርነት ሊገደብ አይችልም። ይሁን እንጂ በልዩ ሁኔታ ምስክር የመሆን ብቃት በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም በሕግ ሊገደብ እንደሚችልና ምስክር መሆን የማይችሉና የማይገደዱትን ሕጉ ለይቶ አስቀምጧል። ለምሳሌም አንድ ሰው በተያዘው ጉዳይ ላይ ለጊዜው ወይም በጉዳዩ ላይ በአጠቃላይ የመመስከር ብቃት እንደሌለው ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል። በሕግም የመመስከር ችሎታቸው የተገደቡ ሰዎች ካሉ (ለምሳሌ የሙያ ምስክር) ምስክር ላይሆኑ ይችለሉ። በሌላ በኩልም የተወሰኑ ሰዎች (ለምሳሌ በመንግስት ሚስጥር የተባለን ማስረጃ የያዙ፣ ጥበቃ በተደረገለት የተለየ ግንኙነት (ትዳር፣ እምነት፣ ጥብቅና...) በተነሳ የተገኘን ማስረጃ የሚያውቅ ሰው ለምስክርነት አይገደድም። ከዚህ ውጪ ያሉ ሌሎች ምስክሮችን ግን በፖሊስ ተጠርተው እንዲመሰክሩ ሊገደዱ ይችላሉ። የምስክር ቃልንም በመሰረቱ በምርመራ ቦታ መቀበል የተገባ ቢሆንም በልዩ ሁኔታ ለምስክር በተለየ የምርመራ ቦታ ወይም በቂ ምክንያት ሲኖር (ለምሳሌ የጤና ችግር) ለምስክሩ በሚመች ቦታ የምስክርን ቃል መቀበል ይቻላል።

የምርመራ አካል የሆነው ሌላው የፖሊስ ተግባር ብርበራ ነው። ብርበራ የሚከናወነው በሰው አካል፤ መኖሪያ ቤት ወይም ማስረጃ ይገኝበታል ተብሎ በሚታሰብ ማናቸውም ቦታ (ተሽከርካሪ፣ መጋዘን፣ መንግሰት መስሪያ ቤት፣ አውሮፕላን…) እንዲሁም በሰው ላይ ሁሉ ነው። ብርበራ በመሰረቱ በተለየ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር በፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚከናወን ሲሆን በብርበራ ሊያዝ የሚችለው ንብረትም በመሰረቱ ለምርመራው የሚፈለገው እቃ ብቻ ነው። ለምርመራ የሚፈለገውን ንብረትንም መርማሪው በእማኝ አረጋግጦ ፖሊስ ምርመራ ቦታ ሊወስደው ይችላል። ብርበራ በፍርድ ቤት ብቻ የሚከናወን ቢሆንም በተወሰኑና በጠባቡ ሊረጎሙ የሚገባቸው ጉዳዮች የገጠሙም እንደሆነ በተለዩት ምክንያቶች (ለምሳሌ የእጅ ከፍንጅ ወንጀል) ያለ ፍርድ ቤት ትዘእዛዝ ብርበራ ለማድረግ የሚቻልበት ሁኔታም ተመልክቷል።

በማስረጃነት የሚፈለገው እቃ መንቀሳቀስ የማይችል፤ በቀላሉ ማሰረጃው የማይገኝበት፣ ማስረጃውን የማግኘት ሂደት ነዋሪውን ወይም ሕብረተሰቡን የእለት ተእለት እንቅስቃሴ የሚያውክ እንደሆነ እቃውን በማሸግ ወይም ባለበት ሁኔታ በመውሰድ የሚፈለገውን እቃ መውሰድ እንደሚቻል ተደንግጓል። የተያዘው ንብረት በማናቸውም መንገድ በግለሰብ እጅ ሊያዝ የማይችል (ምሳሌ ቅርስ፣ የሐይማኖት ተቋም ልዩ ንብረት…) ሲሆን ናሙናን በማሰቀረት ንብረቱን ገቢ ማድረግ እንዲቻል እንዲሁም  ንብረቱን ለመያዝም ልዩ ፍቃድ የሚያስፈልግ ሲሆን (ምሳሌ የጦር መሳሪያ፣ የውጪ ገንዘብ…) ፈቃድ አለኝ የሚል ሰው የሚያቀርበው አግባብ ያለው የሙብት ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ ናሙና በመውሰድ ንብረቱን ገቢ ማድረግ ይቻላል። ሌሎች ንብረቶችን በተመለከተም (ምሳሌ እንስሳት፣ በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ንብረቶች፤ ባለቤታቸው አጠራጣሪ የሆኑ ንብረቶች…) አስተዳደራቸው/አያያዛቸው በተግባር አሰቸጋሪ ስለሚሆን እነዚህ ንብረቶች ላይ የበለጠ ጉዳት ሳይደርስ ፖሊስ ሊያሰተዳድራቸው ስለሚችልበት አግባብም ሥነ ስርአት ሕጉ ደንግጓል። ይህም በዚህ ዘርፍ በተግባር የሚያገጥሙ በርካታ ችግሮችን ይቀርፋል ተብሎ ታሰቧል።

በሌላ ሰው ወይም በመንግስት እጅ የሚገኝን ማስረጃ ፖሊስ ለምርመራ ተግባር ተቀብሎ ምርመራ ሊያከናውን የሚችልበት አግባብ ሕጉ የደነገገ ሲሆን ማሰረጃውን የያዘው አካል ማስረጃውን ለመስጠት የማይችለው በመንግስት ሚስጥር የተባለ ማስረጃ እንደሆነ ብቻ ለመሆኑም ተደንግጓል። ለምርመራው የሚስፈልገው ማስረጃ የባንክ ሂሳብንና እንቅስቃሴውን የሚመለከት ከሆነም ፖሊስ ማስረጃውን በፍርድ ቤታ አማካይነት ማስረጃውን ከባንክ ጠይቆ በማግኘት ምርመራውን ማከናወን ይችላል። ከተጎጂም ሆነ ከተጠርጣሪ ላይ ናሙና (አሻራ፣ የእጅ ጽሑፍ፣ የሽንት፣ የደም፣ የጸጉር ናሙና…) በመውሰድ ምርመራን

ማከናውንም ይችላል። ተጠርጣሪው ናሙናዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ከተጠርጣሪው ሰውነት በቀጥታ የማይወሰዱትን እንደ አሻራ፣ የእጅ ጽሑፍ የመሰሉትን ምርማሪው ተመጣጣኝ ኃይል በመጠቀም መውሰድ የሚችል ሲሆን በሌሎች የናሙና ጉዳዮች ግን ተጠርጣው ናሙና ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆን የተባለው ነገር መኖሩ እንደተረጋገጠ ግምት እንዲወሰድ የሚያስችሉ ድንጋጌዎች ተካተዋል። ተጠርጣሪው በዚህ መልኩ የሚወሰዱ ግምቶችን በማናቸውም ማስረጃ ማስተባበል ወይንም ማፍረስ ይችላል።

በምርመራ ስራ ውስጥ የግድ መከናወን የሚገባቸው ነገር ግን በነባሩ ስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ውስጥ ያልተካተቱ ጉዳዮችም በሥነ ስርአት ሕጉ እንዲካተቱ ሆኗል። በዚህ መሰረት ለምርመራ የሚስፈልግ ንብረት የማገድና የማሸግ ተግባራት በምርመራ ሂደት ሊከናወኑ የሚችሉበት አግባብ በህጉ ውስጥ ተካቷል። የሚታገደው ንብረት ከወንጀሉ ጋር ግንኙነት ያለው፣ በንብረት ወይም በገንዘብ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀልን ለመከላከል የሚያስችል፣ ወንጀል ለመፈፀም በጥቅም ላይ የዋለ ወይም የወንጀል ፍሬ የሆነ አለበለዚያም የሚጠረጠሩ የሂሳብ ሰነዶችን ሊያካትት ይችላል። በዚህ መልኩ የሚገኝ ንብረት የተቀየረ፣ ዋጋው የተለወጠ፣ የተቀላቀለ፣ ወዘተ ከሆነም የማገዱም ተግባር ይህንን ንብረት ይመለከታል። በተወሰኑ ወንጀሎች ላይ ግን (እንደ በሕገ መንግስት እና ሕገ ምንግስታዊ ስርአት፣ ሽብር፣ የአገር ክህደት፣ የአገር ደህንነት እና የመሳሰሉ ወንጀሎችን የሚመለከቱ ወንጀሎች ከሆኑ) ማናቸውም የተጠርጣሪው የግል ንብረት ሁሉ ሊታገድ ይችላል።

በዚህ መልኩ ውጤታማ ክስ ለማቅረብ ንብረት እንዲታገድ በወንጀል ህጉ በተመለከቱ ምክንያቶች ፖሊስ ወይም አቃቤ ህግ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላሉ። የንብረት ይታገድልኝ ጥያቄ የወንጀል ክስ ከመመስረቱ በፊት፣ በምርመራ ጊዜ ወይም ከክስ በኃላ በክርክር ወቅት ሊቀርብ ይችላል። አላማውም የሚወረሱንብረቶች እንዳይበላሹ፣ እንዳይጠፉ፣ እንዳይባክኑ ማድረግና የገንዘብ ቅጣት የሚፈጸምበት ንብረት መኖሩን ማረጋገጥ እንዲሁም በወንጀሉ ጉዳይ ተጎጂ የሆኑ ሰዎች ካሳ የሚያገኙ ቢሆን ንብረት እንዳይጠፋ ለማድረግ ነው። በመሆኑም አሰፈላጊ ለሆነው ጊዜ ያህል ተመጣጣኝ የሆነ ንብረት እንዳይሸጥ፣ እንዳይለወጥ ወይም በማናቸውም መንገድ ወደ ሶስተኛ ወገን ስመ ንብረቱ ሳይዞር እንዲቆይ ሊታዘዝ ይችላል። የንብረት መታገድ የተሰጠ ቢሆንም የንብረቱ ባለቤት በንብረቱ መደበኛ አጠቃቀም ከመስራት እና ኑሮውን ከመምራት ወይም ተጨማሪ ሀብት ከማፍራት አይከለከልም። በተጨማሪም ለተጠርጣሪው እና ለቤተሰቡ ኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ንብረቶችም የእግድ ትእዛዝ አይሰጥባቸውም።

ንብረት በሚታገድብት ጊዜ ተጠርጣሪው ንብረቱን ሆነ ብሎ እያበላሸው ለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ንብረቱ ከይዞታው ወጥቶ በሌላ ሰው እጅ እንዲጠበቅ እንዲሁም እንዲተዳደር ለማድረግ የንብረት አስተዳዳሪ ሊሾም ይችላል። የንብረት አስተዳዳሪ በፍርድ ቤት የሚሾም ሲሆን በህጉ ከተመለከተው ሃላፊነቱና ግዱታዎቹ በተጨማሪ በፍርድ ቤትም ተጨማሪ ሃላፊነት ሊሰጠው ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ጠባቂው እንደ አንድ መልካም የንብረት አስተዳዳሪ መስራት የሚገባው ሆኖ ለአገልግሎቱ ተገቢው ክፍያ በፍርድ ቤቱ ይወሰንለታል። በየጊዜው ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ ያለበት ከመሆኑም በላይ አንድ ንብረት አስተዳዳሪ የሚኖረው ኃላፊነትና ስልጣንም ይኖረዋል።

ለተመሳሳይ አለማም የንብረትን ማሸግ አስፈላጊነት ፍርድ ቤቱ የተረዳው እንደሆነ ንብረት እንዲታሸግ ሊታዘዝ የሚችል ሲሆን በንብረት ላይ ሊኖሩ የሚችሉ ለውጦችን ለመቆጣጠርም የንብረት ዝርዝር ከማዘጋጀት አንስቶ ተገቢው ጥንቃቄ ሁሉ እንዲደረግ የማዘዝ ስልጣን ለፍርድ ቤት ተሰጥቷል። የማይታገዱት ንብረቶች የማይታሸጉ ከመሆናቸውም በላይ በመታሸጋቸው ምክንያት የሚበላሹ ወይም ዋጋቸው የሚቀንሱ ንብረቶች የማይታሸጉ ለመሆናቸው ሕጉ ግልፅ ድንጋጌን ይዟል።

የምርመራ ተግባር ሌላው አካል ቀዳሚ ምርመራ ነው። ይህ ተግባር በነባሩ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ውስጥ የነበረ መሆኑ ይታወቃል። ይሁን እንጂ የነባሩን ህግ አፈጻጸም ይበልጥ ሰፋ በሚያደርግ እና ሂደቱንም ፍትሓዊ ለማድረግ በሚያስችል መልክ በአዲስ መልክ ተደንግጓል። በዚህ መሰረት የቀዳሚ ምርመራ አላማ በወንጀል ጉዳይ የተሰበሰቡ ጠቃሚ እና የማስረዳት ዋጋቸው ከፍ ያሉ ማስረጃዎች በአግባቡ ተጠብቀው እንዲያዙ፣ እንዲደራጁ እና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ መሆኑ ተመልክቷል። በቀዳሚ ምርመራ የሚያልፉ ወንጀሎች በከፍተኛ ፍርድ ቤት ስር የሚወድቁ ሆነው ቀዳሚ ምርመራ የሚደረገውም በቅርብ በሚገኝ በማናቸውም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው። ቀዳሚ ምርመራ የሚደረግባቸውም ወንጀሎች እንደ ከዚህ ቀደሙ በግድያ እና በውንብድና ወንጀሎች ላይ ብቻ የተወሰኑ ሳይሆን በከባድ ወንጀሎች ላይ ሁሉ የሚደረግ ነው። በሂደቱም አቃቤ ህግ ይጠበቁልኝ የሚላቸውን ማሰረጃዎች ሁሉ በማስረጃ አሰማም ስርአት ለፍርድ ቤቱ አቅርቦ የማስጠበቅ መብት ያለው ሲሆን ተጠርጣሪውም በተመሳሳይ ይጠበቁልኝ የሚላቸውን ማሰረጃዎች አቅርቦ ማሰጠበቅ ይችላል። ማስረጃው የሰው ምስክር በሚሆንበት ወቅትም የተሰሙ ምስክሮችም በተፈለጉ ጊዜ የተፈለጉበት ፍርድ ቤት ለመቅረብ ዋሰ እንዲጠሩ ከማድረግ ባሻገር አስሮ ማቆየት የማያስፈልግ በመሆኑ በዚህ ረገድም የቀድሞው ስርአት ተሻሽሏል። ጉዳዩ የሚቀርብበት ፍርድ ቤት ላይታወቅ የሚችል በመሆኑም የተጠበቀውን

ማስረጃም የሚመለከተው አካል አስገልብጦ የሚወስድ ከሚሆን በስተቀር ማስረጃውን የሰማው ፍርድ ቤት ማስረጃውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አስቀድሞ እንዲልክ ይጠበቅበት የነበረው ግዴታም ቀሪ ሆኗል። የቀዳሚ ምርመራ መዝገብ የሚይዛቸው ጉዳዮች ላይ ከነበረው ሕግ እምብዛም ለውጥ አልተደረገም።

ከፍ ሲል ከተመለከቱት የማስረጃ ማሰባሰቢያ መንገዶች በተጨማሪ ፖሊስ እንዳስፈላጊነቱ ወንጀል በተፈጸመበት ቦታ በመገኘት ማስረጃ ማሰባሰብ (የክራይም ሲን ኢንቨስቲጌሽን)፣ ማስረጃ እንዳይባክን የማድረግ እንዲሁም የፎረንሲክ እና ቴክኒክ ማስረጃ እንዳይባክን የሚያስችለውን ምርመራ ለማድረግ የሚያስችለው ግልጽ ድንጋጌ ተካቷል። የዚህ ምርመራ ዘዴ ማስረጃን ለመሰብሰብ እጅግ ጠቃሚ ሲሆን የማስረጃ ትንተና ስራንም ሊያካትት ይችላል። በቦታው የሚሰበሰበው ማስረጃ ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር እየተገናዘበ መተንተን ያለበት ሲሆን አለዚያም ማስረጃውን ምርመራ ቦታ መውሰድ ማስረጃው ላይ ብክለት/ብክነት የሚያስከትል ከሆነ ምርመራው ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ሊደረግ ይችላል። በተመሳሳይም የቤተ ሙከራ እና የሞተ ሰው አካልን ምርመራ ለማድረግ የሚያስችለው ድንጋጌ ተካቷል።

በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ አዲስ የገባው ሌላ ድንጋጌ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት የምርመራ መንገዶች ውጪ መርማሪ በልዩ ሁኔታ ማስረጃ ማሰባሰብን የሚፈቅዱ ድንጋጌዎች ናቸው። ድንጋጌዎቹ ከባድ፣ ውስብስብ እና አለም አቀፋዊ ባህሪ ያላቸውን ወንጀሎች (የሽብር ወንጀል፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት  ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት  ወንጀል፣ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል፣ የኮምፒዩተር ወንጀል፣ የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል እና የሙስና ወንጀል) በበቂ ማስረጃ አስደግፎ ለማውጣት የልዩ ምርመራ እና ዘመናዊ ዘዴዎችን በሕጉ ውስጥ ማካተትና አሰራሩን በሕግ አግባብ በጥንቃቄ መምራት የሚያስችሉ ድንጋጌዎች ናቸው። በዚህ መልኩ ማስረጃ መሰብስብ የተፈቀደበት ዋናው ምክንያት በአሁኑ ሰአት በአገራችን ብቻ ሳይሆን በመላው አለም የወንጀል አፈጻጸሞች እጅግ ውስብስብና ድንበር ተሻጋሪ ከመሆናቸውም በላይ (እንደ የኢኮኖሚ፣ ሙስና፣ በተደራጁ እና በታጠቁ ቡድኖች የሚፈፀሙ ወንጀሎች) እስካሁን በተለመዱት መንገዶች ብቻ ማስረጃ በማሰባሰብ እውነት ላይ በመድረስ የሕጉን፣ የሕዝቡን ፍላጎት እንዲሁም የሕገ መንግስቱን አላማዎች ለማሳካት የማይቻል በመሆኑ ነው። የልዩ ምርመራ መንገዶቹ በተመሳሳይ ምክንያት በሌሎች አገራትም የሚሰራባቸው ናቸው።

ልዩ የወንጀል ምርመራ መንገዶች ተግባራዊ የሚሆነው ሌሎች የምርመራ መንገዶች ተግባራዊ መሆን ያልቻሉ እንደሆነ ብቻ ነው። የሚተረጎሙትም በጠባቡ ነው። በዚህ መሰረትም ማስረጃ በልዩ ዘዴ ማሰባሰቢ መንገዶች ተብለው በሕጉ ውስጥ እውቅና የተሰጣቸው የተጠርጣሪን ግንኙነት በልዩ የድምጽ ወይም የምስል መቅረጫ መሳሪያ መከታተል፣ ሰርጎ በመጋባት እና ልዩ ክትትል ማድረግ፣ የተጠርጣሪን ልዩ ልዩ (የግል መገናኛ ዘዴዎችን መጥለፍ) ግንኙነቶችን መጥለፍና የይምሰል ግንኙነቶችን መፍጠር ናቸው። ልዩ የምርመራ መንገዶችን ለመጠቀም መደበኛ የሆኑት የማስረጃ ማሰባሰቢያ መንገዶች (ከላይ የተገለጹት ናቸው) ውጤት ያላመጡ ወይም የማያመጡና መደበኛው የምርመራ መንገድ መጠቀም አስቸጋሪ መሆኑ ወይም ውጤት እንደማያመጣ አስቀድሞ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

በልዩ ዘዴ የማስረጃ ማሰባሰቢያ መንገድ ትግበራ ላይ ከሚነሱት ጥያቄዎች ዋነኛው የሰብአዊ መብትን ሊያጣብቡ ይችላሉ የሚለው ስጋት ነው። ሕጉ ለዚህ ጉዳይ አግባብ ያለውን ጥንቃቄ አድርጓል። የልዩ ምርመራ ዘዴ ከሰብአዊ መብት ጋር ያለውን ግንኙነት በአግባቡ መቆጣጠር ይቻል ዘንድም በርካታ ገደቦችና የቁጥጥር ሥርአቶችን ሕጉ ዘርግቷል። ከመነሻው በልዩ ምርመራ ዘዴ ማስረጃ የሚሰበሰብባቸው የወንጀል አይነቶች ሁሉም አይነት የወንጀል አይነቶች ሳይሆኑ በህጉ ከባድ ተብለው የተመደቡት የተወሰኑ የወንጀል አይነቶች ብቻ ናቸው። የማስረጃ ማሰባሰቢያ መንገዱን ለመጠቀምም ጥያቄው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቅረብ መፈቀድ ይኖርበታል። ምርመራው ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ሲሆን በትእዛዙ መሰረት ስለመፈጸሙም ፈቃዱን ለሰጠው ፍርድ ቤቱ ቀርቦም መረጋገጥ ያለበት ነው። የተፈቀደው የተለየው የምርመራ መንገዱና የሚቆይበት ጊዜም በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ላይ በግልጽ መመልከት ያለበት ሲሆን ሕገ መንግስቱን በተለይም የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን በመጣስ ወይም ከተፈቀደው የምርመራ መንገድ ውጪ የሚገኝ ማናቸውም ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም። በሌላ በኩልም በዚህ ምርመራ ውስጥ የሚሳተፍ መርማሪ በሕገ መንግሰቱ የተረጋገጡትን ሰብኣዊ መብት ጥሰቶች እንዲሁም ከባድ ወንጀሎችን መፈጸም የማይችል ሲሆን በጉዳዩ ላይ ምስክርም መሆን አይችልም።

የልዩ ምርመራ ዘዴ በፌዴራል ከፍተኛ (ወይም ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት) አስቀድሞ በሚሰጥ ትእዛዝ መሰረት የሚፈፀም ቢሆንም እንደ ሽብርተኝነት፣ ሙስና ወይም በሰው ህይወትና ንብረት ላይ ከባድ ጉዳት የሚያስከትሉ ወንጀሎች ለማጋጠማቸው በቂ ጥርጣሬ ሲኖርና አስቸኳይ ሁኔታ መኖሩ ሲረጋገጥ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ በጠቅላይ አቃቤ ህግ ትእዛዝ ልዩ ምርመራው ሊከናወን ይችላል። ይሁን እንጂ ይህ ትእዛዝ

በ72 ሰአት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍድ ቤት ቤቱ ቀርቦ መፅደቅ ይገባዋል፡፡ በተለዩ ወንጀሎች ላይ ብቻ ሊተገበር የሚችለው የልዩ ምርመራ አይነት እና ልኩ በሕጉ ላይ ተለይቶ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

በምርመራ ሂደት በመጨረሻ የሚከናወነው ማስረጃን ከተከሳሹ የማግኘቱ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ በመርህ ደረጃ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ተጠርጣሪን በመያዝ ወይም በልዩ ሁኔታ ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ (ለምሳሌ የእጅ ከፍንጅ ወንጀል) ተጠርጣሪን በመያዝ የሚከናወን ነው፡፡ የቀድሞው ሥነ ሥርአት ሕግ በመርህ ደረጃ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ቢሆንም ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ተጠርጣሪዎች ሊያዙ የሚችሉበትን መንገድ ያሰፋው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ በቀድሞው ሕግ በመርህ ደረጃ ከተቀመጠው ጋር የሚጋጭና የሰዎች ሙብት ላይ ያልተገባ የሙብት ጥሰት ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ መርሁና ልዩ ሁኔታው በልኩ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ ይህ በመሆኑም በልዩ ሁኔታ ተጠርጣሪዎች ሊያዙ የሚችሉበት አግባብ በግልጽ ዝርዝር ብቻ ተመልከቷል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠርጣሪ ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ሊያዝ የሚችለው ተጠርጣሪው ሊጠፋ የሚችል ሲሆን ወይም ከሶስት ወር በላይ የሚያስቀጣ የእጅ ከፍንጅ ወንጀል ሲፈፀም የተያዘ እንደሆነ ነው፡፡

ማንኛውም የተያዘ ሰው ቃሉን የመስጠት ሙብት አለው፡፡ በፖሊስ በተጠየቀ ጊዜም ዝም የማለት ሙብቱ የተጠበቀ ሲሆን ቃሉን መስጠት ከመረጠም በምልክትም ሆነ በቃል ቃሉን መስጠት ይችላል፡፡ በማናቸውም መንገድ ቢሆን ተከሳሹ የሰጠው ቃል በሀይል የተሰጠ ነው የሚል ክርክር የቀረበ እንደሆነ ቃሉ የተሰጠው ከሃይል እርምጃ ውጪ ለመሆኑ መርማሪው የማስረዳት ሃላፊነት አለበት፡፡ ለዚህም ፖሊስ የተጠርጣሪን ቃል ሲቀበል የደረጃ ምስክርን ጨምሮ ሌሎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በቃል መቀበል ሂደት ውስጥ እንዲጠቀም ይጠበቅበታል፡፡

በአጠቃላይ የወንጀሉ ባህሪና የምርመራ ሳይንስን መከተሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የወንጀል ምርመራ ተግባራት ከላይ በተቀመጡት መንገዶች ብቻ ሳይሆን እንደቅደም ተከተላቸውም እንዲተገበሩ ይጠበቃል፡፡ በማናቸውም መንገድ ምርመራ ሲከናወንም ሆነ ሲጠናቀቅ ስለምርመራው ፖሊስ ለአቃቤ ህግ የማሳታወቅ ግዴታ አለበት፡፡ አቃቤ ሕጉም ከምርመራ ጋር በተያያዘው ኃላፊነቱ የሚሰጣቸውን ትእዛዞች ፖሊስ የመፈጸም ሃላፊነት አለበት፡፡

## 12.1. የዋስትና ጉዳይ

አንድ ተጠርጣሪ በቁጥጥር ስር ከዋለበት ሰአት አንስቶ ከሚነሱት ጥያቄዎች መካከል የዋስትና ጉዳይ ዋናው ነው። በመርህ ደረጃ በወንጀል ጉዳይ ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው በዋስትና የመለቀቅ መብት አለው። ይሁን እንጂ ዋስትና ሊከለከል እንደሚችል በህገ መንግስቱም ጭምር በተደነገገው መሰረት ዋስትና የሚከለከልባቸው ጉዳዮችን ሕጉ ዘርዝሮ የያዘ ሲሆን ከዚህ በፊት በተግባር ይስተዋሉ የነበሩ ክፍተቶችንም ለመሙላት ጥረት አድርጓል። የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 19(6) ስር የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። ይሁን እንጂ ይህ መብት ፍጹም ባለመሆኑ በፍርድ ቤት ሊገደብ እንደሚችል ድንጋጌው በተመሳሳይ ያስገነዝባል። ፍርድ ቤትም ቢሆን የዋስትና መብትን ሊገድብ የሚችለው በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች መሰረት ነው። ስለሆነም የስነ ስርአትና የማስረጃ ህጉ ከዚህ ቀደም በሕግ ዋስትና ይከለከል የነበረበትኑ ሁኔታ አስቀርቶ ዋስትና ሊከለከል የሚችለው በሥነ ሥርአቱ ውስጥ በተመለከቱ ልዩ ሁኔታዎች ብቻ እንደሆነ ግልጽ ድንጋጌ ይዟል።

ዋስትና በፍርድ ቤት በዚህ መልኩ ሊከለከሉ የሚችሉትንም በተመለከት የቀድሞው ድንጋጌ ውስጥ ሌላ ወንጀል ይፈጽማል ተብሎ ሲታሰብ ሊከለከል እንደሚችል የተደነገገው አሁን ከተጠረጠረበት ወንጀል ጋር የማይያያዝ ወንጀል በመሆኑ ቀሪ ሆኖ ሌሎች መመዘኛዎች ለአፈጻጸም በሚመች መልኩ ዘርዘር ብለው ተቀምጠዋል። በመሆኑም ዋስትና በፍርድ ቤት ሊከለከል የሚችለው ተጠርጣሪው በተፈለገ ጊዜና ቦታ ሊቀርብ አይችልም ተብሎ ሲታመን ወይም ተጠርጣሪው ምስክርን ያስፈራራል ወይም ማስረጃን ያጠፋል ተብሎ በበቂ ምክንያት ሲታመን ብቻ እንደሆነ ሕጉ ግልጽ አድርጓል። በቁጥጥር ስር መዋል የተለየ ሁኔታ በመሆኑ ዋስትና ሊከለከል የሚገባው በእነዚህ ልዩ ሁኔታዎች ላይ ሆኖ ከዚህ ውጪ ያሉ ጉዳዮች ከህግ አንፃር የዋስትና መብት የሚያስከለክሉ አይደሉም።

በዚህ መሰረት የዋስትና ጉዳይ የተፈቀደ እንደሆነ ሌላው አስፈላጊው ጉዳይ ትክክለኛውን የዋስትና መጠን መወሰን ነው። ዋስትና ጉዳይ ሲታይ የወንጀሉ ክብደት፣ የተጠርጣሪው ያለፍ ሪከርድ፣ የሕዝብ ጥቅም እንዲሁም ተጠርጣሪው በተፈለገበት ቦታ ሊቀርብ እንደሚችል በሚያረጋግጥ መልኩ መከናወን ይገባዋል። የተያዘው ሰው የሚጠራው ዋስትና በተፈለገ ጊዜ በተፈለገበት ቦት እንዲቀርብ የሚያስገድደው መሆን የሚገባው ከመሆኑ አንጻር አጅግም ያነሰ መጠን መሆን የሌለበት ሲሆን በዋሰ ከመውጣት እንዳይከለክለውም እጅግም የበዛ መሆን አይገባውም። ይህንን ትክክለኛ መጠን የመወሰን ሃላፊነት ዝርዝር ጉዳዩን እየተመለከተው ያለው ፍርድ ቤት ኃላፊነት ቢሆንም ከዚህ ቀደም በነበረው ሁኔታ ትክክለኛ

መጠን ባለመወሰኑ ይፈጠሩ የነበሩ ችግሮችን መቀነስ የሚያሰችል አመላካች መመዘኛዎች በህጉ ውስጥ እንዲካተቱ ሆኗል፡፡ በሌላም በኩል የገንዘብ ዋስትና ማቅረባ ያልቻለ ተጠርጣሪ የዋስትናው ገንዘብ መጠን ሊሻሻልለት ስለሚችልበት ሁኔታም ተመልክቷል፡፡ ይህም ማንኛውም ሰው አቅም እያለው በእስር ለመቆየት ይፈልጋል ተብሎ ስላማይታሰብ ፍርድ ቤት ሁኔታውን መርምሮ የዋስትና ገንዘቡን የሚለውጥበት፣ የሚያሻሽልበትን እድል ዝግ ላለማድረግ በማለም የገባ ነው፡፡

ዋስትና በሚፈቀድበት ማናቸውም ሁኔታ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሹ በተፈለገ ጊዜ እንዲቀርብ የሚያስገድደውን የራስ ዋስተና የመፈረም ግዴታ ያለበት ለመሆኑ በቀድሞው ህግ የተቀመጠው ግዴታ አስፈላጊ በመሆኑ የቀጠለ ሲሆን በዋሰ የሚለቀቀውን ሰውና የተጠረጠረበትን ወይም የተከሰሰበትን ወንጀል ግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ ገደቦች ሊጣሉበት ይችላሉ፡፡ እነዚህ ተጨማሪ ገደቦች የሚንቀሳቀስባቸውን በታዎች፣ የሚያገኛቸውን ሰዎች፣ ሊከተለው ስለሚገባው ባህርይ፣ ከመንግስት አካላት ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት ወይም ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው የሚለው ሌላ ገደብ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች በፍሬ ሕጎች (በወንጀል ሕግ) ላይም የሚመለከቱ ናቸው፡፡

አሁን ባለው አሰራር ተጠርጣሪ በየቦታው (ቢያንስ በምርመራ ጊዜና በፍርድ ሒደት) ዋስትና የሚጠራ በመሆኑ ትርጉም የሌለውን ድግግሞሽም ማሰቀረት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት በምርመራ ጊዜ የተሰጠ ዋስትና በተለየ ሁኔታ ፍርድ ቤት ሌላ ዋስትና እንዲጠራ ካላደረገው በስተቀር በፍርድ ሂደትም ሊያገለገግል ይገባዋልና ሕጉ ይህንን የሚመራ ድንጋጌን አካቷል፡፡ በዚህ አግባብም በቀላል አስራት ሊቀጡ የሚችሉትን ተጠርጣሪዎች መርማሪ ዋስትና መልቀቅ እንዲችል ህጉ ስልጣን ይሰጣል፡፡

ዋስትና በመርህ ደረጃ የተፈቀደ በመሆኑ በዋስትና ለመለቀቅ ጥያቄውን ከታሳሪው ሌላ የቅርብ ሰዎችም ማቅረብ እንዲችሉ እድሉ ሰፋ ብሎ ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት ከታሳሪው በተጨማሪ ወኪሉ ወይም የታሳሪው ቤተሰብ የዋስትና ጥያቄውን ለማናቸውም ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ቤት እየታየ ከሆነም ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ፡፡ በማናቸውም ጊዜ የዋስትና ጉዳይ በቅድሚያ በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት ሊሰጠው ይገባል፡፡

የዋስትና ጉዳይ ካለው ህገ መንግስታዊ እንድምታ አንጻር በጉዳዩ ላይ በሚሰጥ ውሳኔ (በዋስትና መጠን ላይ የሚኖርን ቅሬታ ጨምሮ) ለበላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይቻላል፡፡

ዋስታና መሰረታዊ መብት ቢሆንም መከበሩ እንዲሁም አለመከበሩ ውጤት ሊኖረው ይገባል። በተለይ በቂ ባልሆነ ምክንያት የማይከበር በሚሆንበት ጊዜ የዋስትናው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ስለሚሆንበት ሁኔታ፣ በርካታ ሰዎች ለአንድ ሰው በነጠላና በተናጠል ዋስ ሊሆኑ ስለሚችሉበት ሁኔታና ውጤቱ፣ እንዲሁም ዋስትና ባለመከበሩ የተነሳ ተጠርጣሪው የተወሰነ ጊዜ በእስር ቢያሳልፍ በዚህ ምክንያት የታሰረበት ጊዜ ምናለባት በስተመጨረሻ በእስራት ቢቀጣ የማይታሰብለት ስለመሆኑ የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተካተዋል።

የመያዣ ትእዛዝ ላይ ዋስትና ሊመለከትና ተጠርጣሪው በዚህ ወረቀት ላይ የተመለከተውን ግዴታ ከፈጸመ በዋስ ሊለቀቅ እንደሚችል፣ አዲስ ፍሬ ነገር ወይንም በማሳሳት የተሰጠ ዋስትና ከተገኘም ትእዛዝ እንደገና ሊታይ መቻሉ፣ ዋስትና ባይከበር ሊከተሉ ስለሚገባቸው ውጤቶችና ስርአቶች እና ቀሪ የዋስትና ጉዳዮች ከነባሩ ህግ እምብዛም ለውጥ አልተደረገባቸውም። የዋስትና ጥያቄ በተቻለው ፍጥነት እና በወዲያውኑ ስሜት ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚያስችሉ ድንጋጌዎችም በተመሳሳይ ተካተዋል።

## 12.2. በምርመራ መዝገብ ላይ መወሰን

በወንጀል መዝገብ ላይ የመወሰንን ጉዳይ በተመለከተ ወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ያሰቀመጠውን አቅጣጫ፣ የአገራን ልምድና በተግባር የሚገጥሙ ችግሮችን መሰረት በማድረግ በርካት ለውጦች በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ እንዲካተቱ ሆኗል። ምርመራው የተጠናቀቀ የወንጀል መዝገብ በርካታ ውሳዎች ሊተላለፉበት ይገባል። በዚህ መልኩ የሚወሰኑ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን የዐቃቤ ሕግ ነው። ከነባሩ የሥነ ሥርአት ሕግ በተለየ ሁኔታም የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ለአቃቤ ሕግ ሰፊ የመወሰን ስልጣንን ይሰጣል። በነባሩ ሕግ አቃቤ ሕግ ለመክሰስ የሚያበቃው በቂ ማስረጃ ካለ ክስ የመመስረት ግዴታ ያለበት መሆኑ የሚታወስ ሲሆን ይህ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ግን ይህንን ስልጣን ያሰፋዋል። በመሆኑም በቂ ማስረጃ ያለበት ጉዳይ ሁሉ የግዴታ ክስ የማይመሰረትበት ሲሆን ከመክሰስ ባሻገር የሕጉን አላማ በተሻለ አማራጭ ማሳካትና የሕዝብ ጥቅም በሌላ አግባብ ማሳካት የሚቻል መሆኑን ሲያረጋግጥ በፍርድ ቤት ክስ ላይመሰረት ይችላል። በአጠቃላይ አቃቤ ሕግ የወንጀል ምርመራ መጠናቀቁን ተከትሉ የሚወስናቸው ውሳኔዎች፤

- የምርመራ መዝገብን የመዝጋት (በሞት፣ በእድሜ…ምክንያቶች)፣
- የበላይ ኃላፊን ትእዛዝ የመጠየቅ፣
- ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ ሲያጋጥም የክስ አይመሰረትም ውሳኔ የመስጠት

- ✓ ጉዳዩ ወንጀል ካልሆነ/በቂ ማስረጃ ባመኖሩ፣
- ✓ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል፣
- ✓ ተጠርጣሪ ባለመኖሩ ምክንያት ክሱ በሌለበት የማየታይ በመሆኑ፣
- ✓ ያለመከሰስ ልዩ መብት ያለው ተጠርጣሪ የሆነ እንደሆነ፣
- ✓ ተከሳሽ ለመከሰስ በሚያስችል እድሜ ውስጥ ካልሆነ፣
- ✓ ጉዳዩ ወንጀል ካልሆነ፣
- ✓ ጉዳዩ በይርጋ፣ ይቅርታ፣ በምሕረት፣ በእርቅ፣ በቀደመ ፍርድ የተቋጨ ከሆነ፣

- መሪ ትእዛዝ የመስጠት፣
- የጥፋተኛነት ድርድር የማድረግ፣
- ጉዳዩ ከመደበኛው ፍርድ ቤት ውጪ በአማራጭ እንዲታይ የመወሰን፣
- አማራጭ የመፍትሔ እርምጃ የመውሰድ፣
- ጉዳዩን በእርቅ የመጨረስ፣

ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

ዓቃቤ ሕግ መዝገብ ከሚዘጋባቸው ምክንያቾ ውስጥ አንዱ ጉዳዩ ወንጀል ካልሆነ የሚለው ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ከወንጀል ሕግ ቁጥር 23 ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ዓቃቢ ሕግ የቀረበለትን ጉዳይ ወንጀል የሚያደርግ ሕግ ከሌለ ወይም ክስ ለመመስረት የሚያስችለው በቂ ማስረጃ ከሌለው ወይም የተጠርጣሪውን ሃሳብ/ቸልተኝነት የሚያሳይ ማስረጃ ከሌለው ክስ አይመሰርትም ማለት ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በነባሩ ሕግ አንቀጽ 42(1)(ሀ) ስር የተመለከተውን መመዘኛ ግልጽ እና ሰፋ ያደረገ ነው፡፡

አቃቤ ሕግ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ውሳኔዎች የሚያሳልፈው በሕግ መሰረት መሆን ስለሚገባው በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ ለእያንዳንዱ ውሳኔ መስፈርት ሊሆኑ የሚችሉ ዝርዝር መመዘኛዎች ተቀምጠዋል፡፡ ለምሳሌ አቃቤ ሕግ በቂ ማስረጃ የለም ብሎ ክስ የማይመሰርተው በሕጉ ውስጥ በተመለከቱት የማስረጃ ደንቦች መመዘኛነት ነው፡፡ ለዚህም የማሰረጃዎችን አግባብነት፣ ተቀባይነት፣ አሳማኝነት መመርመር ያለበት ሲሆን ማሰረጃው ግልጽና የሚታመን መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል

ማለት ነው። ለሕዝብ ጥቅም ብሎ ከስ የማይመሰርትባቸው ጉዳዮችም በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ላይ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ጉዳዩ በባህላዊ ስርአት ቢታይ የተሻለ ውጤት የሚያስገኝ ሲሆን፣ ክስ መመስረቱ ያልታሰብ የጎንዮሽ ጉዳት የሚያስከትል ሲሆንና የመሳሰሉት በሕጉ ላይ የተዘረዘሩ ምክንያቶች መኖራቸው ሲረጋገጥ ነው። ለህዝብ ጥቅም ሲባል ክስ አይመሰርትም ማለት ግን ሌላ አማራጭ አይወስድም ማለት አይደለም። ለምሳሌ ውሳኔውን ለበላይ አቃቤ ሕግ የማሳወቅ፣ የግል አቤቱታ ያቀረበ ሰው በግሉ ክስ እንዲመሰርት በጽሁፍ የመፍቀድ፣ ጉዳዩ በባህላዊ ስርአት እንዲታይ ማድረግ እና ሌሎች በሕጉ የተመለከቱ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ።

በተመሳሳይም አቃቤ ሕግ እያንዳንዱን ጉዳይ የሚወስንበት ከፍተኛው የጊዜ ገደብ በሕጉ ውስጥ ተካቷል። ይህ የጊዜ ገደብ አሁን በስራ ላይ ያለውን ልምድ፣ አፈጻጸም፣ የጉዳዮችን ውስብስብነት እንዲሁም እንደ ከዚህ ቀደሙ ሳይሆን አቃቤ ህግ እያንዳንዱን ጉዳይ ከምርመራ ጀምሮ በቅርብ እና በተሟላ ሁኔታ የሚያውቀው መሆኑን ግምት ውስጥ ያስገቡ ጊዜያት ናቸው። የጊዜ ገደቦቹም የሚያመለክቱት እያንዳንዱ ተግባር ተከናውኖ የመጨረሻው ውጤት ለፍርድ ቤት የሚቀርብበተን ጊዜ ነው። ይህ ጊዜ ለምሳሌ ድርድር አልቆ ስምምነቱ ለፍርድ ቤት የማጸደቅ ውጤት የሚቀርብበትን፣ ክስ ተዘጋጅቶ ለፍርድ ቤት የሚቀርብበተን ጊዜ ነው ማለት ነው። ጊዜው ባይጠበቅ የሚኖረው ውጤት በፍርድ ቤት ተግባራት ውስጥ ለሌሎች ጊዜያት አለመከበር የተመለከተው ውጤት ነው።

## 12.3. የጥፋተኛት ድርድር

የጥፋተኛነት ድርድር በፍትህ ስርአታችን ውስጥ አዲስ ከመሆኑም በላይ አፈጻጸሙ ዝርዝር ድንጋጌዎችን የሚፈልግ በመሆኑ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ዘርዘር ያሉ ድንጋጌዎችን አካቷል። የዚህ አይነት ድርድር በስርአቱ በሕጉ የተካተተ ከመሆኑም በላይ የጥፋተኝነት ድርደር አፈጻጸም ሥር ከሰደደበት የኮመን ሎው የሕግ ሥርዐት በሲቪል ሎው የሕግ ሥርዐትም እየተተገበረ የሚገኝ ነው። በአሁኑ ጊዜ እንደ ፈረንሣይ፣ ስፔይን፣ ጀርመን፣ ጣሊያንና ፖርቹጋል ያሉ ሃገራት ሥርዐቱን በሕጋቸው ውስጥ አካትተው ይገኛሉ። የጥፋተኛት ድርድር ከነቀፋ የፀዳ ባለመሆኑ ነቀፋዎቹን ያገናዘቡ ድንጋጌዎች በሕጉ ውስጥ እንዲካተቱ ሆነዋል።

የጥፋተኛነት ድርድር በዋነኛነት አላማው ጥፋትን ማመንን ተከትሎ ጉዳይን በአጭር ጊዜ በመቋጨት የፍትሕ ስርአቱን ቅልጥፍና ማረጋገጥ ነው። ድርድር ተከሳሹ በመፀፀት ጭምር ጥፋቱን የሚያምንበትን

እድል የሚጨምር በመሆኑ ወጪንና ጊዜን ይቆጥባል። በተመሳሳይም በመደበኛው ስርአት በማለፋቸው በተጎጂዎች፣ ተከሳሾችና ምስክሮች ላይ ሊደርስ የሚችልን የስነ ልቦና ጫናን ይቀንሳል። ድርድር በጉዳዩ ፍሬ ነገር ላይ፣ በክስ አይነት፣ ብዛት፣ በቅጣት አይነት፣ እና መጠን ላይ የሚደረግ ነው። ሥለሆነም የጥፋተኛነት ድርድር በክስ ላይና በቅጣት ላይ ሊደረግ ይችላል ማለት ነው። የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በክስ ላይ የሚደረግ ድርድርን አስመልክቶ ዝርዝር መመሪያ የማውጣት ስልጣን ያለው ሲሆን በቅጣት ላይ የሚደረግን ድርድር በተመለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የማውጣት ስልጣን ተሰጥቶታል። የቅጣት አወሳሰን መመሪያውም ተደራዳሪው በሕጉና በሌሎች ቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች ተገናዝበው ሊጣልበት ከሚችለው ቅጣት ላይ እስከ አንድ አራተኛ ተቀንሶ ሊጠቀም የሚችልበትን መመሪያ ነው  ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲያወጣ የሚጠበቀው። ለምሳሌ የቅጣ ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቾች ሁሉ ተገናዝበው ተጠርጣሪው/ተከሰሹ በሃያ አመት ፅኑ እስራት ሊቀጣ ቢችል በጥፋተኛነት ድርድር በማለፉ ቅጣቱ በተጨማሪ እስከ አስራ አምስት አመት ዝቅ ሊልለት ይችላል ማለት ነው። ለመመሪያዎቹ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች አመላካች መመዘኛዎችም በሕጉ ውስጥ ተመላክተዋል።

የጥፋተኛነት ድርድር ከሚነቀፍባቸው ምክንያቶች ውስጥ ተከሣሹ ወንጀሉን አለመፈጸሙን ቢያውቅም ላለመታሰር ወይም የእስር ጊዜውን ለመቀነስ ሲል ጥፋቱን ሊያምን ይችላል፣ ከድርድሩ የሚገኘው ውጤት ተከሣሹ ወይም የተከሣሹ ጠበቃ ባለው የመደራደር ብቃትና ዕውቀት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ተመሣሣይ ወንጀል የተፈጸመ ነገር ግን የላቀ የድርድር ዕውቀት ያለውን ጠበቃ መቅጠር የሚችል ተከሳሽ ከድርድሩ የተሻለ ጥቅም ሊያገኝ ይችላል፣ የጥፋተኝነት ድርድር ተከሣሹ በራሱ ላይ እንዲመሰክር የተስፋ ቃል መስጠት (የእሥራት ቅናሽ) በመሆኑ ከተከሣሹ በራሱ ላይ ላለመመስከር ያለውን ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚጋፋ ይሆናል፤ የሕግ አስፈፃሚ አካላት ሕገ መንግሥቱን በመጣስ በተከሣሹ የሚፈጽሟቸው ተግባራት በመርሁ ተግባራዊነት ሳቢያ ገሀድ ሳይወጣ የሚቀርበት አጋጣሚ ይኖራል፣ መርሁ ዐቃቤ ሕግ የሕዝብ ደህንነትን አሳልፎ እንዲሰጥ አጋጣሚን የሚፈጥርና በወጤቱም የወንጀል ሕግ ዓላማን የሚጥስ ይሆናል፤ ድርድሩን  የተቀበለ ተከሣሽ ያነሰ ቅጣት እንዲቀጣ፤ ድርድሩን ያልተቀበለ ተከሣሽ ሕገ መንግሥታዊ መብቱን በመጠቀሙ የበለጠ ቅጣት እንዲቀጣ የሚያደርግ  ይሆናል፣ የግል ተበዳዩን ፍትሕ የማግኘት መብት ያላገናዘበና ግልጽነት የጐደለው ነው የሚሉ እና የመሳሰሉት ይገኙበታል።

እነዚህን ትችቶች በአብዛኛው ከቁጥጥር ማነስ ይነሳሉ በሚል እምነት የሚነሱ በመሆኑ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ የተለያዩ የቁጥጥር ስርአቶችን ዘርግቷል። ከተዘረጉት የቁጥጥር ስርአቶች ውስጥም

በመጀመሪያ ደረጃ የጥፋተኛነት ድርድር የሚካሔደው በማናቸውም ወንጀሎች ላይ በአቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ አነሳሺነት ቢሆንም ድርድሩን ለማድረግ ተከሳሹን ለማስቀጣት የሚያስችል በቂ ማስረጃ መኖር ያለበት መሆኑ፣ ዐቃቤ ሕግ ያዘጋጅውን ክስ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ያለበትና በተከሳሽ ላይ ክስ ለመመስረትና ለማስቀጣት የሚያስችል በቂ ማስረጃ ያለው መሆኑን ማሳየት (ፕራይማ ፋሺያ ኬዝ ያለው መሆኑን)፣ ተከሳሹ በድርድሩ ለመሳተፍ ሙሉ እና ነጻ ፍቃዱል የሰጠ መሆኑን፣ ድርድሩ ያለጠበቃ መካሔድ የማይችል መሆኑ፣ ስለሂደቱም ሆነ ስለውጤቱ ተከሳሹ በአቃቤ ህግም ሆነ በጠበቃው በሚገባ ተገልጾለት የተረዳው መሆኑን ያለበት መሆኑ፣ በድርድሩ ሂደት ሁሉ በአካል የመገኘትና የአሰተርጓሚም ሆነ የጠበቃው ያለተቆራረጠ ድጋፍ መኖራቸው ሊረጋገጥ ይገባዋል። የሚቻል እስከሆነ ድረስም የወንጀል ተጎጂው በድርድሩ እንዲገኝ መደረግ ይኖርበታል።

በሌላ በኩልም ድርድር የሚደረገው ከክስ በፊት ባለ ጉዳይ ላይ ቢሆንም ክስ እና የክስ መግለጫው ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይገባዋል። ይህም አቃቤ ሕግ በቂ ማስረጃ ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያግዝ ከመሆኑም በላይ ድርድሩ ባይሳካ ክርክሩን ወዲያውኑ ለመቀጠል ያግዛል። ጥፋትን ማመን የክስ ወይም የቅጣት ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑ እስካሁን ባለው መደበኛው ስርአትም የሚሰራበት ከመሆኑ አንፃር የሚነሱት ቅሬታዎች ምን ያህል ሚዛናዊ ናቸው የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ሌሎች በተግባር ይገጥማሉ የሚባሉት ችግሮች እንዳያጋጥሙም የአቃቤ ሕግ፣ የጠበቃ፣ የተከሳሽ እንዲሁም የፍርድ ቤትን ኃላፊነት ግልፅ፣ ዝርዝርና ጥብቅ እንዲሆን አድርጓል። ክስን ከመቀበል አንስቶ ድርድሩን እስከ ማጽደቅ ድረስ ፍርድ ቤትም ጠበቅ ያለ ቁጥጥር የሚያደርግበትን ስርአት ሕጉ ዘርግቷል።

የድርድር ስርአት ቁጥጥር ከሚደረግባቸው መንገዶች ውስጥ ሌላው የሚጠቀሰው የተወሰኑ ድርጊቶች (ለምሳሌ መደለል፣ ያልተገባ ቃል መግባት፣ መዋሸት፣ ማጋነን...) በድርድር ጊዜ የተከለከሉ መሆናቸው ነው። ደርድር ለተቀመጠለት አለማ እንጂ ለሌላ አላማ ለምሳሌ ማስረጃን ከተቃራኒው ወገን ለማግኘት፣ የሚያዋጣውን የክርክር መድረክ ለመምረጥ ወዘተ መዋል አይገባውም። ለዚህም ለምሳሌ ድርድርን ምክንያት በማድረግም ማስረጃ በማናቸውም ወገኖች የማግኘትን ያልተገባ ድርጊት ለመቆጣጠርም በድርድር ሂደት የተገኘ ማስረጃ በፍርድ ሂደት በማስረጃነት ሊቀርብ እንደማይችልም ተደንግጓል። ድርድር ተፈጻሚ የሚሆነው ከህጉም ሆን ከሞራል ጋር የማይጋጭ ስምምነት ተደርሷል ብሎ ጉዳዩን የሚመለከተው ፍርድ ቤት ሲያጸድቀው ሲሆን ፍርድ ቤቱ ድርድሩን የማያጸድቀው ከሆነም ድርድሩን

እንደገና የማድረግ ወይም የተለዩትን ችግሮች ማሰተካከልን ጨምሮ ጉዳዩን በይግባኝ ማሳየትም ተፈቅዷል፡፡

በአንድ ጉዳይ ላይ ከሁለት በላይ ተከሳሾች ሲኖሩ ከፊሉ ተከሳሾች በድርድር ለመሳተፍ ከፊሉ ደግሞ ክርክሩን በመደበኛው ስርአት ለመጨረስ የተለያየ ፍልጎት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ምንም እንኳዋን በጠበበ እድል ቢሆንም በድርድር ስርአት ያለፈው በአነስተኛ ቅጣት ሲቀጣ በመደበኛው ስርአት ያለፈው ማስረጃ በመጥፋቱ፣ በመባከኑ ወይም በመሳሰሉት ምክንያቶች በነፃ ሊሰናበት ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ወቅት የፍትሕ ስርአቱን ለመርዳት በድርድር ያለፈው በተለየ ሁኔታ ሊጎዳ የሚገባው አይሆንም፡፡ ፍትሐዊነት የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ አላማ ከመሆኑም በላይ በፍርድ ቤት ጥፋተኛነቱን ያመነ ግለሰብ እንኳን ጥፋተኛነቱ ተነስቶለት ማስረጃ ተሰምቶ ውሳኔ የሚሰጥበት አጋጣሚን ሕጉ ዝግ አላደረገውም፡፡ በተመሳሳይም ይግባኝ ባይሉም ይግባኝ ባሉ ፍርድኞች ላይ በተሰጠ ፍርድ ይግባኝ ያላሉ ሰዎችም ሊጠቀሙ እንደሚችሉ የቀድሞውም ሕግ ድንጋጌን አካቷል፡፡ እነዚህን ሁሉ ምክንያች ስንመለከታቸው በድርድር ያለፈ ሰው በመደበኛው ስርአት ቢያለፍ የሚቀርብበት ማስረጃ አንድ አይነት እና ተመሳሳይ ቢሆንና በድርድር ባያልፍ ኖሮ በመደበኛው ስርአት እንዳለፉት በነፃ ይሰናበት ነበር የሚል መደምደሚያ ላይ ፍርድ ቤቱ ከደረሰ በተደራዳሪው ጥያቄ የድረድሩ ውጤት ተነስቶ በሌሎች አብረው በተከሰሱት ሰዎች ላይ የተሰጠው ውሳኔ ተደራዳሪው ሊጠቀም የሚችልበትንም እድል ሕጉ ደንግጓል፡፡ ይህ አማራጭ የድርድር እድልን የሚያሰፋ ሲሆን ለነቀፌታዎችም ሚዛናዊ ምላሽ ይሰጣል፡፡

## 12.4. አማራጭ መፍትሔዎች

አቃቤ ሕግ ሊወስናቸው ከሚችላቸው ውሳኔዎች ውስጥ በቂ እውቀት ያለውን ባለሙያ ምክር፣ የተጎጂውን ፈቃድ እና የሚመለከታቸውን አካላት ምክር በመቀበል ጉዳዩ በመደበኛው የክርክር መስመር ከሚቋጭ ይልቅ በሌሎች አማራጭ መንገዶች እንዲታዩ ማድረግ ይገኝበታል፡፡ የአማራጭ እርምጃ የሚወሰደው ከመደበኛው የፍርድ ሂደት በአማራጩ መንገድ በተሻለ መልኩ ለበዳይ፣ ተበዳይ እና አካባቢው ማሕበረሰብ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ይጠቅማል፣ የፍትሕ አካላትን ጊዜ መቆጠብ ይቻላል፣ በዚህም የፍትህ አካላቱ የበለጡ ከባድ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ይበልጥ ውጤታማ ይሆናሉ፣ ተያይዞም በስተመጨረሻ በማናቸውም አግባብ የሕዝብን ጥቅም ማስጠበቅ የሚቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ እነዚህ መንገዶች የእርቅ ስርአትን፣ ባህላዊ ስርአትን እና የጥፋተኛት ድርድርን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በማናቸውም ደረጃ ያለን ጉዳይ በአማራጭ ስርአት በተከራካሪ ወገኖች አመልካችነት (በፍርድ ቤት አነሳሽነትም) ማየት

ይቻላል፡፡ የእርቅ ስርአት ተፈጻሚ የሚሆኑባቸው ጉዳዮች በግል አቤቱታ የሚያስቀጡና በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ሲሆኑ ማናቸውም ጉዳዮች በባህላዊ ስርአት ታይተው እልባት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ማናቸውም ስርአት መሰረታዊ መብቶችን የማይጥስ ለመሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ ለዚሁ ስርአት በዳይና ተበዳይ ግልሰቦች በማይሆኑበት ጊዜም ስርአቶቹን ተጋባራዊ ማድረግ የሚቻል አይደለም፡፡ በሌላም በኩል እንዚህ መንገዶች በደጋጋሚ ወንጀለኛ፣ በቅርብ በተቀጣ ወይም በአማራጭ መፍትሔ ውስጥ ባለፈ ሰው ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡ በእርቅና በባህላዊ ስርአት ያለፉ ጉዳዮች ከእነዚህ መመዘኛዎች በተጨማሪ ለሕግና ለሞራለ የማይቃረን አካሄድ ተከትለው በተመሳሰይ መለኪያ ውጤት ላይ የደረሱ መሆናቸው ሲረጋገጥ በፍርድ ቤት ቀርበው የሚጸድቁ ሲሆን በዚህ መልኩ የጸደቁ መፍትሔዎችም ይግባኝ የማይባልባቸው ከመሆናቸው በቀር በአንድ የወንጀል ፍርድ ቤት የተሰጡ ውሳኔዎች ያላቸው ውጤት ይከተላቸዋል፡፡

ከአማራጭ መንገዶች ጋር ተያይዞ ሌላው መታየት ያለበት ጉዳይ የሌሎች መፍትሔዎች ጉዳይ ነው፡፡ በወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎች በእድሜያቸው፣ በአካል ወይንም በአእምሮ ጤንነታቸው ወይም ለተለዩ ሱሶች የተጋለጡ ከመሆናቸው የተነሳ የወንጀል ፍትሕ ሂደቱን (አማራጭ መንገዶችን ጨምሮ) በሚገባ መከታተል የማይችሉ ከመሆናቸውም በላይ በስተመጨረሻ የሚደረስበት መደምደሚያም ለተለየ ሁኔታቸው ተስማሚ ላይሆን ይችላል፡፡ የአእምሮ ህሙማንን በየትኛውም ስርአት ማሳለፉ የወንጀል ሕግን አላማ ከማሳካት አንጻር ለውጥ አያመጣም፡፡ እንደዚህ አይነት ሰዎች በወንጀል ጉዳይ ላይ ጥፋተኛ ቢባሉ እንኳን በመደበኛው የማረም ስርአት ውስጥ አልፈው ታርመው ወደ ህብረተሰቡ መቀላቀል የሚቸገሩ/የማይችሉ ስለሚሆኑ የሚያስፈልጋቸው እንደ ህክምና፣ ሊያድሳቸወ የሚችል የቀለም የሙያና መሰል ትምህርቶችና ስልጠናዎች መስጠት፣ ምክርና ተግሳጽ፣ በአንድ በተወሰነ ቦታ/አካባቢ ማቆየት፣ እና በሌሎች ሕጎች ሊመለከቱ የሚችሉ ሌሎች መፍትሔዎች ናቸው፡፡ ይህ ስርአት በነባሩ ሕግ ውስጥ ያልነበረ በመሆኑ የፍትሕ ስርአቱ እንደነዚህ አይነት ሰዎችን ለመርዳ ሲቸገር ቆይቷል፡፡

አማራጭ መፍትሔ ተለዋጭ እርምጃ መውሰድን የሚጠይቅ በመሆኑ የባለሙያ የቅርብ ክትትል፤ መፍትሔውን የሚያሰፈጽሙ አከላት በብቃት የማደራጀት፣ በየጊዜው የተሻሉ መፍትሔዎችን እየቃኙ ለአጥፊው እርምት በሚስማማው መልክ የማሰተካከልን፣ መፍትሔው ባለተፈጸመ ጊዜም ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ቀጣይ እርምጃዎች እንዲሁም እርምጃው በአግባቡ ተፈጽሞ ለመጠናቀቁ እያጠና ሃሳብ

የሚያቀርብ ባለሙያ ወይም ተቋም ያስፍልገዋል፡፡ ይህ ተቋም ራሱም በቻለ ሕግ የሚቋቋም ሲሆን ከፍትሕ አካላት በተውጣጣ ቦርድ የሚመራ ተቋም ይሆናል፡፡

ሌላ መፍትሔ የሚስፈልጋቸው ሰዎች ከእርቅ ስርአትም ሆነ ከባህላዊ ስርአት ሊመጡ የሚችሉ በመሆኑም ከእነዚህ አካላትም በወንጀል ጉዳይ ተመሳሳይ መፍትሔ የሚፈልግ ጉዳይ ከገጠማቸው በዐቃቤ ሕግ በኩል ወደዚሁ መፍትሔ ሰጪ አካላት ሊልኩ ይችላሉ፡፡ መፍትሔውም የሕግ ውጤት እንዲኖረውና ከግለሰቦች ሁኔታ ጋር ተለማጭ ሆኖ እንዲፈጸም በአቅራቢያው ባለ ፍርድ ቤት ቀርቦ መመዝገብ ይያገባዋል፡፡

እነዚህ መፍትሔዎች በባለሙያ ታግዘው መሰጠት ያለባቸው ናቸው፡፡ በአይነታቸው በርካታና በቁጥራቸውም የበዙ ሊሆን ስለሚችሉ በዚሕ መልኩ መፍትሔ የሚሰጡ ተቋማትን እንዲሁም ስለዝርዝር አሰራራቸው ጠቅላይ አቃቤ ሕግ በጥናት ላይ የተመሰረተ እውቅና ይሰጣል፡፡

## 12.5.ክስ የመመስረት ውሳኔ

አቃቤ ሕግ በምርመራ መዝገብ ላይ ሊወስናቸው ከሚችላቸው ውሳኔዎች ውስጥ ሌላው በመደበኛው ፍርድ ቤት ክስ መመስረት ነው፡፡ እንደቀደመው ሕግ ሁሉ ክስ ለመመስረት ተከሳሽን ጥፋተኛ ሊያሰኝ የሚያስችል በቂ ማስረጃ መኖረን ማረጋገጥ በቂ ነው፡፡ በቂ ማስረጃ የሚባለው በማስረጃ ምዘና ደንብ መሰረት ተከሳሽን ጥፋተኛ ሊያስብል የሚችል ማስረጃ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተከሳሽን ጥፋተኛ ሊያሰኝ የሚያስችል በቂ ማስረጃ ቢኖርም በተወሰነ መልኩ ክስ መመስረቱ የህዝብን ጥቅም ሊጎዳ የሚችል መሆኑ ከተረጋገጥ ክስ ላይመሰረት ይችላል፡፡ የሕዝብ ጥቅም መለኪያ ዋና ዋና መስፈርቶች በወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ውስጥ ተመልክተዋል፡፡ አነዚህ መስፈርቶች ክስ የማይመሰረትባቸውንና አማራጭ መፍትሔ የሚወሰድባቸውን አጣምረው የያዙ በመሆናቸው በስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ተለይተው እንዲቀመጡ ሆኗል፡፡ በሕዝብ ጥቅም መነሻነት የአቃቤ ህግ የመወሰን ስልጣን ከፍ ሲል የተመለከተው ቢሆንም በተወሰኑ ወንጀሎች ላይ የሕዝብ ጥቅም አለ ተብሎ ከወዲሁ ስለሚታሰብ (ለምሳሌ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 28 ስር በተመለከቱ ወንጀሎች) **በቂ ማስረጃ ካለ አቃቤ ሕግ በቀጥታ የወንጀል ክስ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንዲያቀርብ ይገደዳል፡፡**

የህዝብ ጥቅም የሚባለው በነባሩ ሕግ ውስጥ ተካቶ የነበረ ቢሆንም በኋላ ላይ የተሻረ መሆኑ ይታወቃል፡፡ አንዱ ምክንያት በተቻለ መጠን በግልጽ ባለመቀመጡ የሚፈጠሩ ችግሮች ናቸው፡፡ የህዝብ ጥቅም የሚባሉት በአግባቡ በሕጉ ላይ ካልተመለከቱ ለአፈጻጸም አስቸጋሪ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በስልጣን አላግባብ

መገልገልንም ሊያስከትሉ ይችላሉ። ስለሆነም ዝርዝራቸውን ለመመመሪያ ወይንም ሰፋ ላለ አገላለጽ ከመተው በተቻለ መጠን ጠበው የሚታዩበትን አግባብ ሕጉ በግልጽ ድንጋጌ አስቀምጧል። በዚህ መሰረትም ክስ ላለመመስረት የህዝብ ጥቅም አለ የሚሰኘው በጉዳዩ ላይ ክስ ለመመስረት የሚስችል በቂ ማስረጃ ቢኖርም ተጠርጣሪው የፈጸመው የወንጀል ድርጊት በባሕላዊ ሕጎችና ተቋማት በተሻለ ሁኔታ መፍትሔ የሚያገኝ እንደሆነ፣ክሱ ቢመሠረት ዓለም አቀፍ ግንኙነትን ወይም ብሔራዊ ደኅንነትን የሚጎዳ እንደሆነ፤ወንጀሉ በማንኛውም ምክንያት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ሳይቀርብ በመቆየቱ ወቅታዊነቱን ወይም አስፈላጊነቱን ያጣ እንደሆነ እና የክሱ መመሥረት ከፍ ያለ  የጎንዮሽ ጉዳት የሚያስከትል እንደሆነ ብቻ ነው።

አቃቤ ህግ በውሳኔው ጉዳዩ በፍርድ ሂደት እንዲያልቅ ሲወስን ክስ በማናቸውም ጊዜ በጽሁፍ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ሲሆን ክሱ ስለሚይዛቸው ጉዳዮች አፈጻጸም ወጥነት ሲባልም በክስ ማመልከቻ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው ጉዳዮች በስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ውስጥ በዝርዝር እንዲካተቱ ሆነዋል። በዚህ ሂደትም የክስ ማመልከቻ ዝግጅት ከነባሩ ህግ ያለተለየባቸው ሁኔታዎች ቢበዙም በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ግን ለውጥ ተደርጓል። ለምሳሌ ክሶችንም ሆነ ተከሳሾችን አጣምሮም ሆነ ነጣጥሎ ማቅረብ/መክሰስ ስለሚቻልበት ሁኔታ በህጉ ውስጥ ተመላክቷል። ክስን በአነስተኛ ክስ በአማራጭ ማቅረብ የሚቻል ሲሆን ማስረጃው ባረጋገጠው ልክ እንደአግባቡ በአነስተኛ ወንጀል (ሙከራ፣ አነሳሽነት፣ አባሪነት...) ተከሳሽን ጥፋተኛ ለማለት ይቻላል።

ክስ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብም እንደ ወንጀሉ ክብደት  ተደንግጓል። የጊዜ ገደቡ መደበኛውን የይርጋ ጊዜ የማይተካ ቢሆንም የጊዜ ገደቡ አለመከበር ውጤት አልባ መሆን የማይገባው በመሆኑ ክስ ባለመመስረቱ ምክንያት ከእንቅስቃሴ ውጪ የሆኑ ወይንም እንቅስቃሴቸው የተገደቡ ሰዎቸ እና ንብረቶች ላይ ውጤት እንዲኖረው በሚያስችል አግባብ ተደንግጓል።

አቃቤ ሕግ የሚያቀርበው ክስ አማራጮችን ሁሉ ያለፈ በመሆኑ የተሻለ ጥራት ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል። ይሁን እንጂ በተለያዩ ምክንቶች ክስ የተሻሻለ፣ የተለወጠ ወይም የተጨመረ እንደሆነ ጉዳይ በሕገ መንግስቱ ከተረጋገጠው የተከሳሽ መከላከል መብት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ በመሆኑ የወንጀል ሂደቱ ከክስ መስማት አንስቶ በአዲስ መልክ ይካሔዳል።

አቃቤ ህግ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ክስ ለመመስረት ያልፈቀደ እንደሆነ የግል አቤቱታ አቅራቢ (እርሱም የሌለ እንደሆንም እንደቅደም ተከተላቸው የግል ተበዳይ ሚስት/ባል፣ ወላጅና ልጅ) ክስ እንዲመሰርቱ፣ በግል ክስ ሊቀርብ የሚችለውም በግል አቤቱታ ብቻ በሚያስቀጡ ወንጀሎች ቢሆንም ምርመራው ተጠናቆ ተከሳሽን ጥፋተኛ ሊያሰኝ የሚችል በቂ ማስረጃ መኖሩ በአቃቤ ሕግ ተረጋግጦ ለመክሰስ ፈቃድ ሲሰጥ መሆኑ፣ የግል ክስ አቅራቢ የመክሰስ ስልጣን ሲፈቀድለት እንደ አቃቤ ሕግ ክሱን በሙሉ ኃላፊነት መምራትና መከታተል ለበት መሆኑ፣ ፍርድ ቤትም የግል ክስ ክርክር ከመቀጠሉ በፊት በተቻለ መጠን ከሳሽንና ተበዳይን ለማስታረቅ ጥረት ማድረግ ወይንም እድሉን መስጠት የሚገባው ለመሆኑ  የግል አቤቱታ ክስ አቅራቢ መብቱን ከስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ አላማ ውጪ የተጠቀመበት ሆኖ ከተገኘ ወይንም ስልጣኑን ላልተገባ ተግባር ከተጠቀመበት ወይንም በሂደቱ በግል አቤቱታ የሚያስቀጣ ሳይሆን ከፍ ያለ ወንጀል መፈጸሙን የሚያመላክቱ ማስረጃዎች ከተገኙ ዐቃቤ ሕግ የግል ከሳሽን ተክቶ ክርክሩን ሊቀጥል የሚችል ስለመሆኑ ተደንግጓል።

ከክስ ጋር ተያይዞ ሌላው በሕጉ ውስጥ የተካተተው ጉዳይ ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ ሊቀርብ የሚችለው የፍትሐብሔር ክስ ነው። የፍትሐብሔር ክስ ከወንጀል ጉዳዩ ጋር ተጣምሮ እንዲታይ በአቃቤ ሕግ ወይም በተጎጂ አማካኝነት ለወንጀሉ ጉዳይ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል። ተጎጂው ሕጻን፣ ሴት፣ ድሀ ወይም አቅመ ደካማ ከሆነም የጉዳት/የኪሳራ ካሳ ክሱን አቃቤ ሕግ የማቅረብ ግዴት ተጥሎበታል። የወንጀሉም ሆነ የፍትሐብሔር ጉዳዮች በተቻለ መጠን ተሳልጠው እንዲታዩ ይጠበቃልም። ያም ሆኑ ጉዳዮቹ ከመወሳሰባቸው የተነሳ በተለይ በተጎጂው መብትና በተከሳሽ መከላከል መብት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ሁለቱ ጉዳዮች ተነጣጥለው እንዲታዩ ትእዛዝ መስጠት የሚያስችለው ድንጋጌም ተካቷል። በህጉ ላይ የተመለከቱት የፍትሐብሔር ጉዳዮች አመራርንም በተመለከት ከክስ መመስረት አንስቶ ውሳኔ እስከመስጠትና ውሳኔውን እስከ ማሰፈጽም ድረስ ያሉት ጉዳዮች የሚመሩት የፍትሐብሔር ጉዳዮች በሚመሩበት ሕግና ደንብ መሰረት አንዲሆን ሕጉ ግልፅ ድንጋጌ ይዟል።

## 13. ዳኝነት ነክ ጉዳዮች

በ1954 የወጣው የሥነ ሥርአት ሕግ የፍርድ ቤትን ጉዳይ በተመለከተ የያዛቸው ጉዳዮች ውሱን እንደሆነ ይታወቃል። ይህ በመሆኑም ፍርድ ቤትን የተመለከቱ በርካታ ሕጎች ከሥነ ሥርአት ሕጉ በኋላ ወጥተው ከስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ጋር ጎን ለጎን በመፈጸም ላይ ይገኛሉ። ይህ ሁኔታም ሕጎቹን በአግባቡ

ለመጠቀም የማያስችል በመሆኑና በአንድ ማጠቃለል የሚያሰፈልግ ከመሆኑም በላይ ሕጎቹ አለማችንና አገራችን የደረሰችበትን እድገት በሚያገናዝብ መልኩ መቃኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ቀድሞ የወጡትን ሕጎች ወደ አንድ ከመሰብሰቡም በላይ ይህንን እድገት ያገናዘቡ ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡ የሚከተሉት ክፍሎች ይህንን ያመላክታሉ፡፡

## 13.1 የዳኝነት ሥልጣን

የዳኝነት ስልጣን የመጀመሪያ ገጽታው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የሚኖራቸውን ስልጣን (ጁዲሺያል ጁሪስዲክሽንን) የተመለከተው ነው፡፡ ይህ ስልጣን በነባሩ የሥነ ሥርአት ሕግ ውስጥ ዘርዘርና ግልጽ ብሎ ያልተመለከተ ነው፡፡ በሌላ በኩል የወንጀል ሕጉ ይህንን ጉዳይ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡ ጉዳዩ የሥነ ሥርአት ጉዳይ በመሆኑና የአሁኑም የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግም እንደ መጽሃፍ የተሟላ መሆን ስለሚገባው ይህንንም ጉዳይ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡ በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በዋነኛነት በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በተፈጸመ ወንጀል ላይ፣ ወደ ውጪ በሚጓጓዝ መጓጓዣ ላይ በሚፈጸም ወንጀል ላይ፣ በወንጀል ሕጉ ቁጥር 238-260፣ 355፣ 374 በመጣስ የተፈጸሙ ወንጀሎች ላይ፣ የማይደፈር መብት ያለው ኢትዮጵያዊ በውጪ በሚፈጽመው ወንጀል ላይ፣ የኢትዮጵያ ወታደር በውጪ አገር በሚፈጽመው ወንጀል ላይ፣ ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች በመጣስ በመፈጸም ወንጀል ላይ እንዲሁም የውጪ ሃገር ፍርድ ማስፈጸምን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ስልጣን (ጁዲሺያል ጁሪስዲክሽን) አላቸው፡፡

የዳኝነት ስልጣን ሌላው ጉዳይ ሃገሪቱ የምትከተለው ቅርጸ መንግስት ጋር የተያያዘ ሆኖ የስረ ነገርንና የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ስልጣንን የሚመለከት ነው፡፡ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት በ1954 ዓ.ም በወጣበት ጊዜ ኢትዮጵያ ፍፁም አሃዳዊ አወቃቀር በሚከተል ስርአትና መንግሰት ትመራ ነበር፡፡ በመሆኑም የፍርድ ቤቶች አወቃቀርና ሥልጣንም ይህንኑ አሃዳዊ አወቃቀር የተከተል ሲሆን የፍርድ ቤቶችም ግንኙነት ከላይ ወደታች ወይም ከታች ወደ ላይ ብቻ ነበር፡፡ ይህ አሃዳዊ አወቃቀር እስከ ደረግ መውደቅ (1983) ድረስ ሲሰራበት የቆየ ቢሆንም የደርግ ከስልጣን መወገድን ተከትሎ የአገሪቱ ፖለቲካዊ አወቃቀር ወደ ፌዴራላዊ ቅርፀ መንግሥት መለወጡ ይታወቃል፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 1 መሰረትም የአገሪቷ ስያሜ "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ" ሆኗል፡፡ ፌዴራላዊ አወቃቀሩን ተከትሎም ፍርድ ቤቶች በፌዴራልና በክልል መንግስታት ውስጥ በወረዳ፣ ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ደረጃ ተዋቅረዋል፡፡ የክልል ፍርድ ቤቶች ራሳቸውን ችለው በየክልሉ የተቋቋሙ ሲሆን

የፈዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞችና በጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል፣ አፋር፣ ሶማሊያ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልሎች በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሰረት ተደራጅተዋል፡፡ የተቀሩት ክልሎች ማትም የትግራይ፣ አማራ፣ ሐረሪ እና ኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግስቱ መሰረት ውክልና የፌዴራል ዳኝነት ስልጣን አላቸው፡፡

የአገሪቱ ፍርድ ቤቶች የፌዴራሉን አወቃቀር ተከትለው የተቋቋሙ ከመሆኑ አንጻር በርካታ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ የወንጀል ሕግን የማውጣት ስልጣን የፌዴራል መንግስት ስልጣን እንደመሆኑ መጠን የወንጀል ጉዳዮችን የመዳኘት ስልጣን የየትኛው ፍርድ ቤት ነው? የፍርድ ቤቶችን ስልጣን እንዴት መለየት ይቻላል? የፌዴራል መንግስት ሕግ ባላወጣባቸው የወንጀል ጉዳዮችስ? የፌደራል መንግሥት  የሚያወጣው የወንጀል ሕግ ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ውጭ እንዴት ይፈፀም? የሚሉና መሰል ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ሕገ መንግሰቱ በሰጠው ውክልና መሰረት ክልልች የፌዴራል ወንጀል ጉዳዮችን በውክልና መመልከት ይችልሉ፡፡ በሌላ በኩልም አዋጅ ቁጥር 25/88 በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወንጀል ስልጣን ስር የሚወድቁ ጉዳዮችን የሚዘረዝር በመሆኑ ቀሪ ጉዳዮችን ክልሎች ሊመለከቱ ይችላሉ፡፡ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 7 መሰረት ከአዋጁ ጋር የማይጋጩ በሥራ ላይ ያሉ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥር0ት ሕግ እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው በመሆኑ በአዋጅ 25/88 ባልሸፈነው ጉዳይ ከዚህ በፊት የወጡት የወ/መ/ሕ/ስ/ስ አንቀጽ 4 እና በዚሁ ሥነ ሥር0ት አንደኛው ሰንጠረዥ ሦስተኛው አምድ የተዘረዘሩት የፍርድ ቤቶች ሥልጣን እና ደንብ ቁጥር 17/67 የሚፈፀሙበት አግባብ ይኖራል ማለት ነው፡፡ ከእነዚህ የቀደሙት ህጎች በተጨማሪ አዋጅ ቁጥር 25/88 ለማሻሻል በተከታታይ የወጡ ሕጎች (አዋጅ ቁጥር 25/1988፣ 138/1991፣ 254/1993፣ 321/1995፣ 322/95፣ 454/1995) እንዲሁም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተለያዩ ጊዜያት የተሰጡ የሰበር ውሳኔዎች የፍርድ ቤቶች ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

ይህም የፍርድ ቤቶችን አደረጃጀት ውስብስብ፣ በቀላሉ ለመጠቀም የማይመችና ግልፅነት የጎደለው የሚያደርግ ሲሆን የፍርድ ቤቶቹን ስልጣን በአንድ ሕግ ተጠቃሎ እንዳይገኝና የሕግ አስፈፃሚዎችም (ዳኞችና፣ አቃብያነ ሕግ፣ ፖሊስ፣ አጠቃላይ ሕብረተሰቡ) የፍርድ ቤትን ስልጣን በቀላሉ እንዳይለዩ ያደረገ ነው፡፡ በሌላ በኩልም በነባሩ የሥነ ሥርአት ህግ አንቀፅ /106/ መሠረት አንድ ወንጀል ፈፅሞ የተከሰሰ ሰው የሚዳኘው ወንጀሉ በተፈፀመበት አካባቢ በሚገኝ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ይህ በወንጀል ምርመራም ሆነ በአቃቤ ሕግ ስራዎች ላይ ያለውን ትርጉም የነባሩ ሥነ ሥርአት ሕግ አይመልስም፡፡

በወንጀል ፍትሕ ሂደት ውስጥ በአዲስ አበባና ድሬዳዋ መስተዳድር ፍትሕ ተቋማት እና በፌዴራል መንግሥቱ የሥልጣን ክፍፍል እና በክልል ፍትሕ ተቋማት መካከል ሊኖር ስለሚገባው የትብብር እና የግኑኝነት ሥርዓት ግልጽ ድንጋጌዎችን ነባሩ ሕግ ያላካተተ በመሆኑ ተጨባጭ ችግሮች እየተፈጠሩ ይገኛሉ። ለምሳሌም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚሠጡ ትዕዛዞችን፣ ብይኖችን እና ውሳኔዎችን የክልል ፍትሕ አካላት ለመፈፀም በሕግ የሚገደዱበትን ሁኔታ በሥነ ሥርዐት ሕጉም ሆነ በሌሎች ሕግች ውስጥ አልተካተተም። በዚህም ምክንያት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ወንጀለኞችን አስመልክቶ የሚሰጡ የተለያዩ ውሳኔዎች አፈፃፀም ሳንካ እየገጠማቸው በወንጀል ደርጊት የተጠረጠሩ ግለሰቦች ለሕግ ሳይቀርቡ ተመልሰው ህብረተሰቡ ውስጥ በመግባት የኅብረተሰቡን ሰላምና ጸጥታ የሚያውኩበት ሁኔታ እንዳይፈጠር ማድረግ ይገባል። በዚህ ረገድ አልፎ አልፎ ችግሮች ያጋጥማሉ። በመሆኑም የወንጀል ጉዳዮችን አስመልክቶ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የክልል ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ፍርደች ፣ ትእዛዞች፣ ብይኖችና ውሳኔዎች በሌሎች ክልሎች የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እውቅና ለመስጠት እና ለማስፈጸም የሚገደዱበት ሕጋዊ ሥርአት መገንባት ይስፈልጋል።

አገራችን የፌዴራል ስርአትን የምትከተል ከመሆኑ አንፃር የሥነ ሥርአት ሕጉ ያሉበትን ክፍተት ለመሙላት ይህ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ የፌዴራል ቅርፀ መንግስትን ግምት ውስጥ በማስገባት የወንጀል ዳኝነት ስልጣንን በሕገ መንግሰቱ አግባብ በፌዴራልና በክልል ፍርድ ቤቶች መክከል እንዲከፋፈል ያደርጋል። ይህ የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል በመሰረቱ ይኑር እንጂ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ዋነኛ መነሻ የወንጀል ጉዳይ በሕገመንግስቱ ላይ እንደተመለከተው ሁሉ የፌዴራል ጉዳይ ነው በሚል ነው። የፌዴራል መንግስቱ በሕግ የተሰጠውን ስልጣን ማስፈጸም ያለበትም ሲሆን በወንጀል ጉዳይ ላይ የወንጀል ሕግ የማውጣት ስልጣን በተሰጠው መሰረት ሕጉን ያወጣ ሲሆን በተሰጠው ስልጣን መሰረት ያወጣውን የወንጀል ሕግ ስራ ላይ ለማዋል የሚስችለውን የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ የማውጣት ግዴታም አለበት። ስለሆነም በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ላይ የተቀመጠው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ወንጀል የዳኝነት ስልጣን ከሕገ መንግስቱ በቀጥታ የሚመነጭ ሲሆን የክልል ፍርድ ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ስልጣን የፌዴራል መንግስቱ በዚህ ሕግ መሰረት በሚወስነው ልክ የሚሰጥ ስልጣን ነው የሚሆነው። የክልል ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ ላይ በሰንጠረዥ ተለይቶ የተሰጣቸው የዳኝነት ስልጣን የፌዴራል መንግሰቱ በውክልና የሚሰጣቸው መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባና ይህ ስልጣንም በፌዴራል መንግስቱ በየጊዜው መሻሻል ሊደረግበት የሚችል መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። ይሁን እንጂ ክልሎች በስልጣናቸው ውስጥ የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት

በማድረግ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የተለየ ውሳኔ መወሰን ይችላሉ። ለምሳሌ በሰንጠረዡ የተሰጣቸው የክልል ጉዳዮችን አስመልክቶ የትኛው የወንጀል አይነት በየትኛው ደረጃ በሚገኝ የክልል ፍርድ ቤት መታየት እንደሚችል በተለየ ሁኔታ መወሰን ይችላል።

የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ የወንጀል የዳኝነት ስልጣንን በፌዴራልና ክልል ፍርድ ቤቶች መካከል ሲደለድል አንድ ጉዳይ የፌዴራል ወይም የክልል ሊሆን የሚችልበትን መመዘኛ ወይም መርህ አስቀምጦ ነው። በዚህ መመዘኛ ውስጥ ከተቀመጡት መስፈረቶች ውስጥም ጉዳዩ የፌዴራል ስርአቱን፣ ሕገ መንግስትን፣ አለም አቀፍ ግንኙነትን፣ ከአንድ ክልል በላይን ወይም ከአንድ ክልል በላይ የሆኑ ሰዎችን እና በሕጉ የተለዩ ቦታዎች (ለምሳሌ አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ) የሚሉት መመዘኛዎች ይገኙበታል። የፌዴራል ስርአቱን የሚመለከቱ ጉዳዮች የተባሉት በወንጀል ሕግ ከቁጥር 238 አንስቶ የተመለከቱት ናቸው። የወንጀሉ ጉዳዮች ከእነዚህ ነጥቦች ጋር የሚገናኙ ከሆነ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ ይሆናሉ።

ይህ አጠቃላይ መመዘኛ የተቀመጠ ቢሆንም በፌዴራል የፍትሕ አካላት የሚታዩት ጉዳዮች በሕጉ ውስጥ በዝርዝር ተቀመጠዋል። በዚህም መሠረት አፈጻጸማቸው የፌዴራል መንግሥት ወይም አንድ የክልል መንግሥት ከሚያስተዳድረው የአስተዳደር ክልል በላይ የሆኑ ወንጀሎች፣ ዓለም አቀፍ ባሕርይ ያላቸው ወይም ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች፣ ከውጭ ጉዳይ ተያያዥነት ያላቸው ወንጀሎች፣ በፌዴራል መንግሥቱ ተቋማትና ንብረቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣ የፌዴራል መንግሥቱ ሕግ እንዲያወጣ በሕገ መንግሥቱ ሥልጣን በተሰጠው ጉዳዮች ጋር ተያያዘው የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣ ከኃላፊነት ጋር በተያያዘ በፌዴራል መንግሥቱ ባለሥልጣናትና ሠራተኞች የሚፈጸም ወንጀል፣ የጉምሩክና የፌዴራል መንግሥት ግብርና የገንዘብ ጥቅም ሕጎችን በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎችና ለፌዴራል መንግሥቱ ተጠሪ የሆኑ ከተሞች ወይም ቦታዎች የሚፈጸሙ ወንጀሎችና በሕግ መንግሥቱና በሕገመንግሥታዊ ሥርዐቱ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቁ ወንጀሎች መሰረት መሆናቸው በግልጽ እንዲገባ ተደርጓል።

የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል በመንግስታት ደረጃ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በየመንግስታቱ ውስጥ ባሉ ፍርድ ቤቶችም የተከፋፈለ ነው። በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ የተቋቋሙት ፍርድ ቤቶች በሶስት ደረጃ የተመለከቱ በመሆናቸው የዳኝነቱም ስልጣን በሶስቱ ፍርድ ቤቶች ዘንድ የተከፋፈለ ነው። በድልድሉ መሰረትም የጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በውክልና ከሚያዩዋቸው ጉዳዮች በቀር የቀጥታ ዳኝነት ስልጣን

አይኖራቸውም። የሌሎች ፍርድ ቤቶች የዳኝነቱ ስልጣን የሕጉ አካል በሆነው ሰንጠረዥ የተመለከተ ሲሆን ሰንጠረዡ የእስራት ቅጣትንና የወንጀል አይነትን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው። በዚህ መሰረት የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ (ለምሳሌ በሙስና፣ ሽብር፣ ሕገ መንግስታዊ ስርአት ላይ በሚፈጸም ወንጀል፣ የባለስላጣናት የወንጀል ጉዳይ ጉዳይ) ቀጥታ የዳኝነት ስልጣን ሲኖረው አብዛኛው የወንጀል ጉዳይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚታይ ይሆናል። በክልል ፍርድ ቤቶችም የቅጣት ጣሪያው አስራ አምስትና በታች የሆኑ ጉዳዮች በወረዳ ፍርድ ቤት የሚታዩ ናቸው። ይህ ጠቅላላ መስፈርት እንደተጠበቀም ሆኖ እያንዳንዱ ወንጀል እየታየ ቅጣቱ ዝቅ ያለ ቢሆንም ውስብስብ የመሆን እድሉ ከፍተኛ ሲሆን በበላይ ፍርድ ቤት ስር እንዲሆኑም ተደርገዋል።

በዚህ መሰረት በፍርድ ቤቶች አወቃቀር የበታች የሆኑት ፍርድ ቤቶች (የወረዳ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች) ሙሉ በሙሉ በሰንጠረዥ አንድ የተመለከቱት ጉዳዮች ላይ የቀጥታ ክስ ጉዳይን የሚመለከቱ ናቸው። መካከለኞቹ ፍርድ ቤቶች (የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች) በአብዛኛው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ናቸው። ይሁን እንጂ የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በጣም በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ቀጥታ የዳኝነት ስልጣን አላቸው። የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በውክልና ካላቸው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን እና ከክስ ይዛወርልኝ ጉዳይ በቀር ሙሉ በሙሉ ይግባኝ እና ሰበር ሰሚ ፍርድ ቤቶች ናቸው። ይህ ስልጣን ክፍፍልም መሰረታዊ በመሆኑ መሻሻልም ቢያስፈልገው የተወካዮች ምክር ቤት በሚያጣው ሕግ መሰረት ብቻ ሊሻሻል የሚገባው ነው። በተመሳሳይም ወደፊት በሚወጣ ሕግ አዲስ ወንጀል በሚደነገግበት ጊዜ ሕግ አውጪው በተለየ ፍርድ ቤት እንዲታይ ካልወሰነ በስተቀር በወረዳ ፍርድ ቤቶች/በመጀመሪያ ፍርድ ቤት እንዲታይ ሃሳብ እንዳለው ይገመትና ወንጀሉ በወረዳ ፍርድ/በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይታያል።

ከፌዴራል እና ክልል ፍርድ ቤት ውጪ የሆኑና ለሌላ አካላት ቀርበው ውሳኔ ሊገኙ የሚችሉ ጉዳዮችም (በሕገ መንግስት ዐጣሪ ጉባኤ የሚታይ እና በወታደራዊ ፍርድ ቤት የሚታዩ ጉዳዮች) በተመሳሳይ ተለይተው ተቀምጠዋል። በነዚህ ፍርድ ቤቶችም ቢሆን የበታች ፍርድ ቤቶች ቀጥታ ክስን የሚቀበሉ ሲሆን የበላይ ፍርድ ቤቶች ደግሞ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች መሆናቸውን ባገነናዘበ መልኩ ነው የስልጣን ድልድሉ የተሰራው። የእነዚህ አካላት ስልጣንም በሕገ መንግሰቱ እና በወታደራዊ ፍርድ ቤት ማቋቋሚያ ሕግ በተቀመጠው አግባብ የተቀመጡ ናቸው። ከዚህ ውጪ ያሉት ጉዳዮች (በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥትና በሌሎች ሕጎች ለፌዴራል መንግሥቱ ፍርድ ቤቶች ባልተሰጡ የወንጀል ጉዳዮች፣ ሰዎች እና ቦታዎች ላይ) ክልሎች የመጀመሪያ ደረጃ፣ የይግባኝና የሰበር የዳኝነት ስልጣን እንደሚኖራቸው በግልጽ ተመልክቷል።

የክልል ፍርድ ቤቶች የወንጀል ጉዳይን የመመልከት ስልጣን ቢኖራቸውም የወንጀል ጉዳይ የፌዴራል ጉዳይ ከመሆኑ አንፃር በየትኛውም ደረጃ የታየ ጉዳይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሊታዩ የሚችሉ መሆናቸው ተገቢ በመሆኑ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሕገ መንግስቱ መሰረት የክልል ጉዳዮችን ጨመሮ የወንጀል ጉዳዮችን በሰበር ማየት የሚያስችለው ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

የዳኝነት ስልጣን በተለያዩ ፍርድ ቤቶች መካከል የተከፋፈለ ከመሆኑም አንፃር አንድ ጉዳይ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች የመቅረብ እድል ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህም የሕገ መንግስት ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል በመሆኑ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ እንደዚሕ አይነት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ሊፈቱ የሚችሉበትን አግባብም አስቀምጧል፡፡ ጉዳዮቹም በአንደኛው ፍርድ ቤት ተጣምረው እንዲታዩ ዐቃቤ ሕግ ወይም ተከሳሽ ማመለከት እንደሚችልና ጉዳዩን በይግባኝ ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ከሁለቱ በአንደኛው ፍርድ ቤት ተጣምሮ እንዲታይ ትእዛዝ መስጠት እንደሚችል በሕጉ ውስጥ ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩልም ከክሶቹ በከፊል በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ በከፊል በከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚታዩ እንደሆነ ከክሶቹ ከባዱን ክስ ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ሆኖ ክሶቹን በማጣማር መስማት እንደሚቻል፣ እንደዚሁም ከክሶቹ በከፊል በፌዴራል ፍርድ ቤት እና በከፊል በተለያዩ የክልል ፍርድ ቤቶች ስር የሚወድቁ ከሆነ የፌዴራል ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዳኝነት ለመመልከት የዳኝነት ስልጣን የሚኖረው ሲሆን ከፊሉ በክልል ፍርድ ቤቶች ወይም በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን የሚወድቅ እንደሆነ ከባዱን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ክሶቹን አጣምሮ መስማት እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ምናልባት ከቀረቡት ጉዳዮች ውስጥ ከባዱን መለየት የሚያስቸግር በሚሆንበት ጊዜም የጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ከባድ የሚባለውን ወንጀል ለይተው መወሰን እንዲችሉ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ክፍፍሉ ከፍ ሲል በተመለከተው መርህ መሰረት ላይ የተመሰረተ ቢሆንም የየፍርድ ቤቱ ስልጣን በግልጽ እንዲታወቅ የስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ አካል በሆነው ሰንጠራዠ ተለይቶ ተቀምጧል፡፡ በሰንጠረዠ ሊለይ የማይችለው የአሰተዳደር ወሰን የዳኝነት ስልጣን ቢሆንም ይህ ስልጣን መንግስት በሚወስነው መሰረት የሚኖርን የአስተዳደር (ፌዴራል/ ክልል/ ዞን/ ወረዳ) ወሰን አከላለል የሚከተል ይሆናል፡፡ መደበኛ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣንን በሚመለከት ረቂቁ አገሪቱ ከምትከተለው ፌዴራላዊ የመንግሥት ሥርዓት ጋር በሚጣጣም መልኩ የፌዴራሉ መንግሥት ስልጣን በሆኑ የወንጀል ጉዳዮች ላይ በሥረ ነገር ስልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ወይም ድርጊቱ ውጤት ባገኘበት የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች ላይ

የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን እንዳላቸው፤ የክልል ፍርድ ቤቶች በክልሉ የግዛት ወሰን ውስጥ በተፈጸሙ ወይም ድርጊቱ ውጤት ባገኘበት የክልል የወንጀል ጉዳዮች ላይ የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን እንዳላቸው በአዲስ አበባና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ወይም በሌሎች በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በተፈጸሙ የፌዴራል የወንጀል ጉዳይ ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ወሰን የዳኝነት ሥልጣን እንዳላቸው አመላክቷል፡፡

አስተዳደር ወሰኑ በሕግ አግባብ በተለወጠ ቁጥር የዳኝነት አካሉም የአስተዳድር የዳኝነት ስልጣንም ሌላ ሕግ ማውጣት ሳያስፈልገው ይህንኑ ተከትሎ ይለወጣል፡፡ ተደራራቢ የአስተዳደር ዳኝነት ስልጣን ቢያጋጥም የቀደምትነት መርህ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ይህ ስልጣንም በትክክል ሊለይ ያልቻለም እንደሆነ የስረ ነገር ስልጣን ባለው በአንደኛው ፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል ሲሆን የፍርድ ቤቱ ስልጣን ምርጫ ግን የስነ ስርአትና ማስረጃ ህግን አላማ በይበልጥ የሚያስፈጽም መሆን ይገባዋል፡፡ ይህንን ጉዳይ ፈጻሚ አካላት ክስ ሲመሰርቱ አስቀድመው ይለዩታል በሚል እሳቤ ሕጉ የተቀረጸ ቢሆንም በሂደት የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉን አላማ ለማሳካት የሚያስችል አለመሆኑ ከተረጋገጠ ግን ክሱ የተሻለ ውጤት ሊያስገኝ ወደሚችል ፍርድ ቤት ሊያዛወር እንደሚች ተደነገገ ሲሆን ለዚህ እና መሰል ጥያቄዎች አቀራረብም ሆን ለውሳኔ አሰጣጥ አመቺነትም ዝርዝር መስፈርቶች በስነ ስርአትና የማስረጀ ሕጉ ውስጥ እንዲካተቱ ሆኗል፡፡

የሌሎች የፍትሕ አካላት (ፖሊስ፣ አቃቤ ሕግ፣ ማረሚያ ቤት) ስልጣንም የፍርድ ቤቶችን ስልጣን ተከትሎ የተቀመጠ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ማረሚያ ቤቶች ካቋቋሟቸው የፌዴራልም ሆነ የክልል መንግስት ውጪ የሌላ ፍርድ ቤት የሚሰጠውን ትእዛዝ ሊፈፅሙ የሚችሉበትም አግባብ አይኖርም ማለት ግን አይደለም፡፡

## 13.2 ችሎትና ግልፅነት

የሕገ መንግስቱ አንቀፅ 12(1) የመንግስት አሰራር ለሕዝብ ግልፅ ሆኖ መከናወን እንዳለበት የሚያስገድድ ሲሆን አንቀፅ 20(1) በተለይ ስለተከሰሱ ሰዎች ሲደነግግ በተመሳሳይ መልኩ የተከሰሱ ሰዎች ለሕዝብ ግልፅ በሆነ ችሎት የመዳኘት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ ችሎት በዝግ ሊታይ የሚችልባቸውን የተለዩ ሁኔታዎችንም ሕገ መንግስቱ በተመሳሳይ ደንግጓል፡፡ ችሎት በዝግ ሊካሔድ የሚችለውም ጉዳዩን በያዘው ዳኛ ውሳኔ ወይም በሕግ መሰረት ብቻ ነው፡፡ ችሎት በዝግ እንዲታይ ጉዳዩን በያዘው ዳኛ ሊወሰን የሚችለው የጉዳዩ በግልፅ ችሎት መታየት የተከራካሪ ወገንን የግል ሕይወት፣ የሕዝብ ሞራል ወይም የአገር ደሕንነትን ይጎዳል የሚል እምነት ሲኖር ነው፡፡ ሕገ መንግስቱ የዳኛነት ነፃነትን ያረጋገጥ በመሆኑ በዚሕም

ጉዳይ ቢሆን ውሳኔ መስጠት ያለበት ጉዳዩን በያዘውና በቅርብም በሚያውቀው ዳኛ እንጂ በፍርድ ቤቱ (በተቋሙ) ወይም በሌላ አካል እንዲሆን አልተመረጠም። አንድ ጉዳይ በዝግ ችሎት ሊታይ የሚችልበት ሌሎች ምክንያች ጉዳዩ የወጣት ጥፋተኞች ሚመለከት ሲሆን እንዲሁም አንድ ጉዳይ በዝግ ችሎት ይታይ የሚል ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ጥያቄውን ለመመርመር ነው። እነዚህ ምክንያች በመጀመሪያው ምክንያት ውስጥ የተካተቱ ለመሆናቸው በትርጉምም ቢሆን የሚደረስባቸው በመሆናቸው በህግ መደንገጋቸው ግር የሚል አይሆንም።

አንድ ጉዳይ ለሕዝብ በግልፅ ችሎት ይታያል ማለት ለመገናኛ ብዙሃንም ግልጽ ይሆናል ተብሎ የሚወሰድ ነው። ይሁን እንጂ ዳኛ በሚወስነው የግልጽነት መጠን ላይ ተንተርሶ የመገናኛ ብዙሃን ስለሚዘግቡት/ስለማይዘግቡት ጉዳይ፣ አዘጋገብ፣ የዘገባ መሳሪያ አጠቃቀም ወዘተ ዳኛው ሊወስን ይችላል። የሌሎች አገራች ልምደ የሚያሳየው የዚህ ጉዳይ አፈጻጸም ዝርዝር ስለሚሆን ወደፊት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚወጧ መመሪያም ጭምር የሚመራ እንደሚሆን የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ጥንቃቄን እድርጓል።

በችሎት መሰየምንም በተመለከት እስካሁን የሚሰራበት የ1፣3፣ 5 ዳኛ አሰያየም ላይ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በተወሰነ መልኩ ለውጥ አድረጎበታል። በዚህም መሰረት ችሎት ለሁሉም ጉዳዮች ወጥ በሆነ አግባብ ከሚሰየም ይልቅ በተወሰነ ደረጃ ተለማጭ አሰያየምን መከተል በሚያስችል መልኩ ድንጋጌዎች ተካተዋል። በመሰረቱ የሕጉ መነሻ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአንድ ዳኛ ያስችላል የሚል ሲሆን የበላይ ፍርድ ቤቶች በሶስት ወይም ከሶስት በላይ በሆኑ ዳኞች ሊያስችሉ ይገባል የሚል ነው። ይሁን እንጂ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ቢሆን በፍርድ ቤቱ ከሚታዩ ጉዳዮች ብዛትና ሊያጋጥም ከሚችል የጉዳይ ውስብስብነት አንፃር አንድ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ከአንድ በላይ የሆኑ ዳኞች መሰየም ሊኖርባቸው ይችላል። በሌላ በኩልም በከፍተኛ እና በጠቅላይ ፍርድ ቤቶችም ቢሆን ሁሉም የዳኛነት ስራ የግድ በሶስት ወይም በአምስት ዳኞች መታየት አያስፈልጋቸውም። ለምሳሌ ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠት የዳኝነት ስራ ቢሆንም የግድ በአምስት ዳኛ ሊሰራ ይገባል የሚያሰኝ አይደለም።

በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚታይ አንድ ጉዳይ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ ውሳኔ ሶስት ዳኞች በሚሰየሙበት ችሎት ሊታይ እንደሚችል የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ድንጋጌ አካቷል። በሌላ በኩል በከፍተኛ እና በጠቅላይ ፍርድ ቤቶች አንድ ጉዳይ በመሰረቱ በሶስት፣ በአምስት ወይም ከአምስት በላይ

በሆኑ ዳኞች መታየት ያለበት ቢሆንም ተለይተው የተዘረዘሩ የተወሰኑ ተግባራት ግን በአንድ ወይም በሁለት ዳኞች መታየት እንደሚችሉ ሕጉ በዝርዝር አሰቀምጧል፡፡

ከሶስት በላይ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት ውሳኔ በሙሉ ድምጽ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ የሙሉ ድምጽ ውሳኔ ባልተገኘበት ጊዜ በድምጽ ብልጫ የሚሰጥ ውሳኔ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የሚሆን ሲሆን ይህንንም የድምጽ ብላጫ ማገኘት የማይቻል ቢሆን (ለምሳሌ በባለ አምስት፣ ሰባት…ችሎት ላይ ድምጽ 2፣2፣1 ሆኖ ቢከፈል) የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የሚሆነውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ እንዲወስን ሕጉ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስልጣን ይሰጣል፡፡

## 13.3. ከፍርድ እና ከፍትሕ ሂደት ስለመነሳት

ማንኛውም ባለጉዳይ ጉዳዩን በሚመለከተው የፍትሕ አካል ባለሙያ ላይ ቅሬታ ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህ ቅሬታም ባለሙያው ጉዳዬን ሊመለከት አይገባውም እስከማለት ሊደርስም ይችላል፡፡ እስካሁን ባለው አሰራር የዚህን አይነት ጥያቄ በወጥነት የሚያሰተናግድ ሕግም ሆነ አሰራር የለም፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኞች ከችሎት ስለሚነሱበት ምክንያትና አሰራር በፍርድ ቤቶቹ ማቋቋሚያ ላይ የተመለከተ ቢሆንም የክልል ዳኞችና እና የሌሎች ፍትሕ አካላት ሕግና አሰራር የዚህን ያህል ግልጽ አይደለም፡፡ በመሆኑም በሁሉም የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች (ዳኛ፣ ዐቃቢ ሕግ፣ ፖሊስ፣ ተከላካይ ጠበቃ) ላይ ተመሳሳይ ቅሬታ ሊነሳ የሚችል በመሆኑ ይህንንም ጉዳይ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ሕጉ አካቷል፡፡ በዚህም መሰረት እያንዳንዱ ባለሙያ ማንኛውንም ስራ በባለሙያነትና በኃላፊነት ስሜት መስራት እንዳለባቸው፣ አንድን ጉዳይ ማየት የሌለባቸው መሆኑን እንዳወቁ አቤቱታ እስኪቀርብባቸው መጠበቅ ሳይገባቸው ጉዳዩን መመልከታቸውን ማቆም እንዳለባቸው፣ ባለማወቅ ይህንን ቢያልፉ ወይም በሕጉ ላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ከጉዳዩ ላይ እንዲነሱ ጥያቄ ሲቀርብላቸው ወዲያውኑ ውሳኔ መስጠት እንዳለባቸው የሚያስገነዝቡና መሰል ድንጋጌዎች በሕጉ ውስጥ እንዲካተቱ ሆኗል፡፡

ከፍትሕ ሂደቱ ሊነሱ የሚችሉባቸው ምክንያች የጥቅም ግጭትን ሊያስከትሉ የሚችሉ፣ ባለሙያውን ገለልተኛነትና ነጻነት የሚመለከቱ በመሆናቸው በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ የተመለከቱ ቢሆንም ሌሎች ምክንያች ባለሙያዎቹ በሚመሩባው ደንቦች ውስጥም የሚገኙ ቢሆን ለዚሁ ስርአት ተፈጻሚ የሚሆኑ ናቸው፡፡

### 13.4. መጥሪያ

የቀድሞው የሥነ ሥርአት ሕግ ለፍትሕ ሥርአቱ የሚፈልገውን ሰው (ተከሳሽ፣ ምስክር፣ ሰነድ አቅራቢ ወዘተ) ስለሚጠራበት መንገድ ዝርዝር ድንጋጌ የሌለው በመሆኑ ስለመጥሪያ አይነቶችም ሆነ ስለ ውጤታቸው በተግባር ሰፊ ክፍተቶች ያጋጥሙ ነበር። ይህንን ከፍተት አሁን ካለው የቴክኖሎጂ እድገት ጋር አጣጥሞ መሙላት የሚያስፈልግ በመሆኑ የስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ መጥሪያን አስመልክቶ ዝርዝር ድንጋጊዎችን ይዟል። መጥሪያ በወንጀል ጉዳይ ከምርመራ አንስቶ እስከ ፍርድ መስጠት ድረስ በሁሉም የፍትሕ አካላት ሊወጣ የሚችል ነው። በመሆኑም የፍርድ ሂደትን በሚደነግገው ክፍል ውስጥ የተመለከተው መጥሪያ ለሁሉም የፍትሕ አካላት (ፖሊስና አቃቤ ሕግ) እንዳግባቡ እንዲፈጸም ሆኖ በሕጉ ተቀምጧል።

በየትኛውም ደረጃ የሚወጣ/የሚታዘዝ መጥሪያ አላማው ፍትሕ የማግኘት መብትን ለማረጋገጥ፣ የመሰማት መብትን ለማረጋገጥ፣ በፍትሕ አካላት ዘንድ የመጠየቅ ግዴታን መወጣት መቻልን ለማረጋገጥና የፍትሕ ሂደቱን ሊያቀላጥፉ የሚችሉ ሌሎች ተግባራትን ለማከናወን ነው። በመሰረቱ መጥሪያን ማዘጋጀት ያለበት ተግባሩን የሚፈጽመው አካል ሲሆን የሚያደርሰው ግን ፖሊስ ነው። ለፍርድ ቤት በሚቀርብ ጉዳይ መጥሪያን ፍርድ ቤት የሚያዘጋጅ ሲሆን ጉዳዩን ላመጣው አካል (ምሳሌ ክሱን ላመጣው አቃቤ ሕግ) ፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ መጥሪያውን የማዘጋጀትና የመስጠት ኃላፊነት አለበት። ፍርድ ቤቱ ይህንን መፈጸም ባይችል አቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት ድረስ መጥሪያውን የማድረስ ኃላፊነት ይኖርበታል።

መጥሪያ ምንጊዜም ቢሆን ለተጠሪው በአካል መድረስ ያለበት በመሆኑ ሕጉም ይህንን አደራረስ በመርህ ደረጃ አስቀምጦታል። መጥሪያን በአካል ለተጠሪ ማድረስ የማያስችል በቂና አሳማኝ ምክንያት ከተገኘ ምትክ መጥሪያ ሊታዘዝ ይችላል። ለምሳሌ ተጠሪው በአገር ውስጥ የሌለ ለመሆኑ በሚገባ ከተረጋገጠ በምትክ መጥሪያዎች ሊጠራ ይችላል። በመሆኑም በህጉ ላይ የተቀመጠው አግባብ መጥሪያ በአክል፣ በፖሊስ በኩል፣ በመገናኛ ብዙሃን የሚደርስበትን አድል የሚያሰፋ ነው። ምትክ መጥሪው በቀጥታ መድረሱ ባይረጋገጥ እንኳን ሰፊ ሽፋን ባለው የመገናኛ ብዙሃን አማካኝት ከተነገረ መጥሪያው በምትክ እንደደረሰ ግምት ሊወሰድ ይችላል።

ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ካልቀረበ ጉዳዩ መካከለኛና ከባድ ወንጀሎችን የሚመለከት ከሆነ በሌለበት ታይቶ ፍርድ ሊሰጠ ይችላል። ተከሳሽ በሌለበት የሚታዩ ጉዳዩች ቀድሞ ከነበረው በሰፋ ሁኔታ የተደነገጉ በመሆቸው መጥሪያው በአግባቡ ለመድረሱ አጠራጣሪ በሆነ ቁጥር አላስፈላጊ ክርክር እየተነሳ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ አላማ እንዳይሳካ እና ክርክር በጭፍጫፊ ጉዳይ ላይ እንዲያተኩር ያደርጋል። በመሆኑም በምትክ መጥሪነት የተመረጡት እንደ ፖስታ፣ ራዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣ እና ስልክ ያሉት ሆነው መጥሪያ የደረሰ ለመሆኑ በማያከራክር ሁኔታ ሊረጋገጥባቸው የሚችሉ ናቸው። በዚህ መሰረት ምንም እንኳን መጥሪያ ሊላክ የሚችልባቸው ሌሎች አግባቦች ቢኖሩም (ምሳሌ የኢ-ሜይል፣ ፋክስ...) መጥሪያው ለተጠሪው ለመድረሱ በእርግጠኝነት ማረጋገጥ የማይቻል በመሆኑ በምትክ መጥሪነት አልተካተቱም።

ከመጥሪያ አላማ አንፃር ምትክ መጥሪያ ቅደም ተከተሉን ጠብቆም መላክ ያለበት ስለመሆኑ፣ ለተጠሪው በሚገባ መድረሱ ወይም ሰፊ ሽፋን ባለው የፌዴራል ወይም የክልል መገናኛ ብዙሃን መነገሩ ከተረጋገጠ ለተጠሪው እንደደረሰው ይቆጠራል።

መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ ተከሳሽ ተይዞ እንዲቀርብ (ለምሳሌ ለከባድ ወንጀል፣ መቅረብ የሚችል በሆነባቸው ጊዜያት ሁሉ) ሊታዘዝ ይችላል። በተወሰኑ ጉዳዮች (ከወጣት አጥፊና ከቀላል ወንጀሎች ውጪ) ላይም መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ ተከሳሽ ጉዳይ በሌለበት ይታያል። ቀላል ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች በአብዛኛው አካባቢቸውን ለዚህ ብለው የማይለቁ በመሆኑ በአካል ቀርበው ሊከራከሩ የሚገባቸው ሲሆን በእንደዚህ አይነት ጉዳይ መዘገቡ ለጊዜው ቢቋረጥ እንኳን ቀላል የወንጀል ጉዳዮች ከወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው አንጻር ከመካከለኛ እና ከከባድ ወንጀሎች ቅደሚያ የማይሰጣቸው በመሆኑ በቀላል ጉዳይ ተከሳ በሌለበት ማየት አዋጪ ኤደለም። በሌልም በኩለ የወጣት ጥፋተኞች ጉዳይም ከክርክር ይልቅ ለወጣቱ ችግር መፍትሔ መፈለግ ላይ ማተኮር ያለበት በመሆኑ ክርክሩ ምንጊዜም ባለበት መካሔድ ያለበት ነው።

መጥሪያ የሚታዘዝበት ሌላው ምክንያት ማስረጃ እንዲቀርብ ለማስቻል ነው። በመጥሪያ የተፈለገ ማስረጃ በበቂ ምክንያት ሊቀርብ ካልቻለ በዚህ ምክንያት ብቻ ሁል ጊዜ መዝገብን ማቋረጥ ተመራጭ አይሆንም። በመሆኑም በቀረበው ማስረጃ መወሰን እስከተቻለ ድረስ ጉዳዩ ተመርምሮ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚችል በመሆኑ ሕጉ ድንጋጌ ይዟል።

ከመጥሪያ አላማ አንጻር በመጥሪያ ያልቀረበ ማናኛውም ተከሳሽ ክርክሩ በደረሰበት ደረጃ ወደ ክርክሩ መግባት ይችላል። ቀድሞ በተጠራበት ጊዜ ሊቀርብ ያልቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑን ወይም መጥሪያ ሳይደርሰው በመቅረቱ ምክንያት ለመሆኑ ካስረዳ ክርክር መኖሩን በተረዳ ወይም በቂ ነው የተባለው ምክንያት በተወገደ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ወደ ክርክሩ ለመግባት ፍርድ ቤት ቀረቦ ማመልከት ይችላል። ያቀረበው ምክንያትም ተቀባይነትን ካገኘ ክርክሩን እርሱ ባላበት ለማካሔድ እንደገና እንደ አዲስ ይጀምራል። በሌላ በኩልም በቂ ምክንያት ከሌለው ወይም መጥሪያ ደርሶት ያልቀረበ ከሆነም ክርክሩ በደረሰበት ደረጃ ገብቶ መከራከር ይችላል። የበቂ ምክንያት መለኪያን ማሰቀመጥ አስቸጋሪ በመሆኑ ጉዳዩን የሚመለከተው ፍርድ ቤት የቀረበውን ምክንያት እና የነገሩን ዙሪ መለስ ተመልክቶ የሚወስነው ምክንያት ነው።

## 13.5.የቅድመ ክስ መስማት ተግባራት

አሁን ባለው ሕግና የችሎት አመራር ዳኞች ሙሉ ትኩረታቸውን በጉዳዩ መሰረታዊ ነገሮች ላይ ከሚያተኩሩ ይልቅ በጉዳዩ ዋና ነገር ላይና በጭፍጫፊ ጉዳይ ላይ ሁሉ ተጠምደው ውድ ጊዜያቸውን ሲያባክኑ እንደሚውሉ ግልፅ ነው። ይህ ችግር በመሰረቱ ሊቀረፍና ዳኞች ሙሉ ጊዜያቸውን በፍሬ ጉዳዩ ላይ ብቻ አተኩረው ውጤታማ ፍትሕ ሊሰጡ የሚችሉበትን እድል ማስፋት ያስፈልጋል። ዳኞች ጉዳዩን ውጤታማ በሆነው አግባብ የሥነሥርአትና ማስረጃ ህጉን አላማ አሳክተው መቋጨት ያለባቸው በመሆኑ አሁን በስራ ላይ እንደሚታየው በጥቃቅን ጉዳይ ውድ የሆነውን የችሎት ጊዜም ማባከን አይኖርባቸውም። በዚህ መሰረት የሕጉ ዋነኛ ትኩረት ዳኞች በጉዳዩ ፍሬ ነገር ላይ እንዲያተኩሩና ቀሪ አስተዳደራዊ ተግባራት ከችሎት ስራ ውጪ ሆነው እንዲጠያናቅቁ ማስቻል ነው።

በመሆኑም ክስ እንደቀረበ የመጀመሪያው ተግባር አስተዳደራዊ የሆኑና የዳኛውን ትኩረትና ጊዜ የግድ የማይፈልጉ ጉዳዮችን ለይቶ ተገቢውን ስራ በመስራት የችሎት ጊዜን የሚፈልጉትን ለይቶ ማዘጋጀት ይሆናል። ይህ ስራ በሕጉ ላይ የቅድመ ክስ ስራ ተብሎ ተለይቷል። እስካሁን ያለተሰራበትም ሲሆን በጸረ ሙስና ጉዳዮች ላይ በሕግ ከተፈቀደው የቅድመ ክስ መስማት ጋርም ግንኙነት የለውም። የቅድመ ክስ መስማት ተግባራት አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ተግባራትን የሚያካትት በመሆኑ በዋናኘነት በሬጂስትራር አማካኝነት መከናወን የሚገባው ነው። በዚህ መሰረት የፍርድ ቤቱ ሬጂሰትራር የክሱን ብቃት የሚያረጋግጥ ሲሆን የክስ ብቃቱ የተረጋገጠው ክስ ዳኛ መጥሪያ ከማዘዙ **በፊት የክሱን ሕጋዊ ብቃት ያረጋግጣል። ይህም በክሱ ላይ ወደኋላ ሊነሳ የሚችልን ተቃውሞ አስቀድሞ** እልባት በመስጠት

ለማስቀረት ያግዛል በሚል እሳቤ የገባ ነው። የክሱ ሕጋዊነት እንደተረጋገጠም መዝገቡ ለዳኛ የሚቀርብ ሲሆን ዳኛውም ጉዳዩ የሚመራትን የክርክር መስመር መለየት ይኖርበታል። ይህ ተግባር ይከናወን/አይከናወን የሚለውንና በማን አማካኝነት (በዳኛው ወይም በሬጂስትራር) ይከናወን የሚለውን በሕግ ከማስቀመጥ እንደጉዳዩ የተለየ ባህሪ ጉዳዩን በቅርብ በሚያውቀው ዳኛ ቢወሰን የሚመረጥ በመሆኑ በሕጉ ላይ የመምረጥ ስልጣኑ ለዳኛው ተትቷል። ክሱን ተመልክቶም ሁለት ነገሮች ላይ ትእዛዝ መስጠት ይችላል። እነዚህም አንደኛ በጉዳዩ ላይ የቅድመ ክስ ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል አያስፈልግም በሚለውና በሁለተኛ ደረጃም የቅድመ ክስ ተግባራት መከናወን የሚገባው ከሆነው በማን አማካኝነት (በሬጂስትራር ወይም በዳኛው) መከናውን ያለበት ስለመሆኑ በመለየት ትእዛዝ ይሰጣል። ስለሆነም ከመደበኛው ችሎት አስቀድመው ማለቅ ያለባቸው ጉዳዮችም በወቅቱ ማለቅ እንዲችሉ አቃቤ ሕግና ተከሳሹ በራሱ በዳኛው ፊት ወይም በሬጂስትራሩ ፊት ቀርበው መፈጸም ያለባቸው ጉዳዮች ካሉ ተለይተው እንዲፈጸሙ ጉዳዩን በሚመለተው ዳኛ ተጨማሪ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል ማለት ነው።

ይህ ተግባር የቅድመ ክስ መስማት ተግባራት በሚል በሕጉ እንዲካተት የሆነ ሲሆን በዚህ ተግባር ውስጥም አቃቤ ሕግና ተከሳሹ በዳኛው ወይም በሬጂስትራሩ ፊት ቀርበው እንደ የተከላካይ ጠበቃና አስተርጓሚ አስፈላጊነትን የመለየትና የማሟላት፣ ክርከሩ የሚመራበትን ሥርአት የመለየት፣ ለምስክር ወይም ለሌላ ማስረጃ አቀራረብ አስፈላጊ የሆነውን የመጥሪያ አይነት የመለየት፣ ለክርክሩ አስፈላጊ የሆኑትን ቅድመ ሁኔታዎችን የመለየት፣ ክርክሩ የሚጠናቀቅበትን አጠቃላይ እቅድ የማውጣትና የመሳሰሉት ተገባራት ሊያከናወኑ ይችላል። እነዚህና መሰል ጉዳዮች አስቀድመው ከተጠናቀቁ ክሱ በሚሰማት እለት ጠበቃ የለም፣ አሰተርጓሚ አልተገኘም፣ ችሎቱ በአግባቡ አልተዘጋጀም...እየተባለ የሚነሱትን አላስፈላጊ ክርክሮች መቀነስ (ማሰወገድ) የሚቻል በመሆኑ ችሎቱም ክርክሩ በሚሰማበት እለት ሙሉ ትኩረቱን በዋናው ፍሬ ነገር ላይ ብቻ በማድረግ ጊዜውን ጉለበቱን በአግባቡ መጠቀም እንዲችል እንዲሁም ክርክር ሳይቆራረጥ ወዲያውኑ ውሳኔ የሚሰጥበትን እድል መጨመር ይቻላል።

በቅድመ ክስ መስማት ዝግጅት ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን የክስ መክፈቻ ንግግር በግልፅና በተሟል ሁኔታ መዘጋጀቱ አስፈላጊ ነው። ለፍርድ ቤት ከሚቀርበው ክስ እና መከላከያ ጋር የከስ እና የመከላከያ ሙሉ መግለጫ መቅረብ እንዳለባቸው ሕጉ የሚደነግገው መግለጫው አቃቤ ሕጉ ወይም ተከሳሹ ክርክሩን እንዴት ሊያሰኬደው እንዳሰበ የሚያመለክተውን እቅድ ፍንትው አድርገው ስለሚያሳዩና ክርክር በድብቅ ሳይሆን በግልጽነትና አስቀድሞ በሚታወቅ አቅድ የሚመራ መሆኑ የስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ

ያሰበውን አላማ ለማሳካት ያግዛሉ በሚል እምነት ነው። እስከአሁን በሚደረጉ ክርክሮች ይህንን ጉዳይ በግልጽ የሚመራ ሕግ በተሟላ ሁኔታ ያልነበረ በመሆኑ አንድ ጉዳይ መቼ ተጀምሮ መቼ እንደሚጠናቀቅ እንኳን አስቀድሞ ለመገመት አይቻልም ነበር። ተከራካሪ ወገኖችም በአግባቡ እንዳይተጉ እድሉን ሲከፍትና የክርክር ጥራትም እንዲጓደል የበኩሉን አስተዋጽዎ ሲያበረክት ቆይቷል። ይህም በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ጉዳዮች አመራር ላይም ሳንካ ሲፈጥር የቆየ በመሆኑ በሕጉ ውስጥ ይህንን በግልጽና በግዴታ መፈጸም የሚያስችል ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል።

## 13.6. የክርክር ሥርአቶች

በሕገ መንግስታችን ዕውቅና ካገኙ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች መካከል አንዱ የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት የመሰማት እና ፍትሐዊ ውሳኔ የማግኘት መብት ነው። ይህ መብት በወንጀል ድርጊት የተጠረጠሩ እና ክስ የተመሰረተባቸው ሰዎች ሌሎች መብቶቻቸውን ለማስከበር ብቸኛ ዋስትናቸው ሲሆን በተለይም ተጠርጥረው ለተያዙና በእሥር ላይ ሆነው ውሳኔ ለሚጠባበቁ ተከሣሾች እጅግ በጣም ወሳኝ ነው። ይህ መብት ለተከሳሹ ብቻ ሳይሆን ለተጎጂዎችና ለህብረተሰቡም ጭምር ትልቅ ጠቀሜታ አለው። የተከሰሱ ሰዎች የተከሰሱበት ጉዳይ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ በአጭር ጊዜ ውስጥ የማይወሰን ከሆነ የተከሳሾች መብት ብቻ ሳይሆን የሌሎች ባለጉዳዮችም እንዲሁም የሕብረተሰቡ ጥቅም በአጠቃላይ ይጣሳል።

የቀደመው ስነ ሥርአት ሕግ (በተለይም ከወንጀል ፍትህ አስተዳር የለውጥ ስራ ማሻሻያ ትግበራ በፊት) የተደረጉ ልዩ ልዩ ጥናቶች እንዳረጋገጡት የወንጀል ጉዳይ ከጥቆማ እስከ ፍርድ ድረስ በአማካኝ እስከ አራት አመት ጊዜ ይፈጅባቸዋል። "የዘገየ ፍትሕ እንደተከለከለ ይቆጠራል" የሚለው የሕግ ሊቃውንት አባባል ለዚህ አይነት መዘግየት ጠቃሚ አባባል ነው።

የተቀላጠፈ ፍትሕ የማግኘት መብት እውን ከሚሆንባቸው ህጎች ውስጥ አንዱ ጉዳዮች የሚመሩባቸውን ስርአቶች በአግባቡ የለየ የወንጀል ስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ መኖሩ ነው። ከሥነ ሥርአት ህግ አንፃር አንደ ጉዳይ እልባት ሳያገኝ ከሚጓተትባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ደግሞ ክርክር የሚመራበት ስርአት ያለበት ችግር በመሆኑ በሥራ ላይ ያለውን የሥነ ሥርአት ክርክር አመራርና አያያዝ ስርአት መፈተሽና ማስተካከል ይገባል።

የነባሩ ሕግ አንዱ ችግር አብዛኛው ጉዳይ በተመሳሳይ ስርአት እንዲመሩ ማድረጉ ነው። ነባሩ የሥነ ሥርአት ሕግ ከተወሰኑ ጉዳዮች (ወጣት ጥፋተኞች፣ ደንብ መተላለፍ…) ውጪ ያሉ ክርክሮች በተለያየ መንገድ መመራት የሚችሉ ስለመሆናቸው የሚያሰቀምጠው ዝርዝር ድንጋጌ የለውም። ይህም በመሆኑ ጉዳዮች ሁሉ በመርህ ደረጃ መሰረታዊ ልዩነቱ ጎለቶ በማይታይበት በተመሳሳይ የመደበኛው መስመር እየተመሩ ይገኛሉ። በአብዛኛውም የጉዳዮች በፍጥነት መጠናቀቅ ወይም አለመጠናቀቅ የሚወሰነው በየፍርድ ቤቱ ባለው መዝገብ ማነስ/መብዛት ላይ እንጂ በክርክሩ መስመር ወሳኝነት አለመሆኑ ግልፅ ነው። ይህም የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ላይ የራሱን ጫና ያሳደረ በመሆኑ ይህ ስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ የተለያዩ ጉዳዮች በተለያዩ የስነ ስርአትና ማስረጃ መስመሮች እንዲመሩ የሚያስችል ድንጋጌዎችን ይዟል። በመሆኑም ጉዳዮች እንደገና የሚታዩባቸው የይግባኝ፣ ሰበር፣ ጉዳይን እንደገና የማየት እና የመሰየም ስርአቶች እንደተጠበቁ ሆነው አንድ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ማየት ከመጀመሩ በፊት በዋነኛት ጉዳዩ ከተቀላጠፈ፣ ከተፋጠነ፣ ከወጣት ጥፋተኛ ወይም ከደንብ መተላለፍ ስርአቶች ውስጥ በየትኛው ስርአት እንደሚመራ አስቀድሞ መለየት ይገባዋል።

የክርክር መስመሮች የተለያዩ ቢሆኑም ጉዳዮች በጊዜ ገደብ ሊመሩና በጊዜ በታጠረ ገደብ ውስጥ ተከውነው መጠናቀቅ ያለባቸው ናቸው። የክርክር ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሌሎች ፍትሕ አካላትም ተግባራት ሁሉ በጊዜ ገደብ ውስጥ ታጥረው መከናወን ያለባቸው መሆኑ በርካታ ጠቀሜታ አለው። ስራዎች ሁሉ በቅልጥፍና ከተከናወኑ ፈጣንና ጥራት ያለው ፍትሕ የማረጋገጥ እድል ይጨምራል እንዲሁም የፍትሕ አካላትን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ያግዛል። ስራዎቹ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ያለመጠናቀቃቸው በተጠርጣሪ እና በሌሎች ሰዎች ላይ (በዋስትና፣ በመንቀሳቀስ መብት ላይ፣ …) እንዲሁም በንብረት አስተዳደር ላይ (የታገደ ንብረት የሚለቀቅበት ሁኔታ፣ የታሸገ ንብረት እሽጉ የሚነሳበት ሁኔታ…) አፍራሽ ውጤትን ያስከትላል። በተጨማሪም ስራው በጊዜ የታጠረ መሆኑ የፈጻሚ ባለሙያ ትጋት በአዎንታ እንዲጨምር የማድረግ ኃይል ያለው ሲሆን ባልበቃ ምክንየት ስራን በሚያጓትት ባለሙያ ላይም የተጠያቂነትን ስርአት በግልጽ ሕግ አግባብ ተፈፃሚ ለማድረግ ያስችላል።

ይህም በሕገ መንግስቱ የተመለከተውን የተፋጠነ ፍትሕ የመስጠት ግዴታን ለመወጣት የሚያስችል ከመሆኑም በላይ የሚዘገዩ ጉዳዮችን ለይቶ በአሉታም ሆነ በአዎንታ እገዛ ለማድረግና የሕጉን አላማ ለማሳካት ያግዛል። በመሆኑም ሁሉም የክርክር መስመሮች አንድ ጉዳይ በመስመራቸው ሲገባ ሊጠናቀቅ

ይገባዋል የሚባልበትን የመጨረሻ  ጊዜ አካተው ይዘዋል፡፡ የክርክር ስርአቶቹን በአጭሩ እንደሚከተለው ተመልክተዋል፡፡

የተቀላጠፈው ስርአት በሥነ ስርአት ህጉ የተመለከተው መደበኛው ስርአት ሆኖ በመሰረቱ በስነ ስርአትና የማስረጀ ህጉ ውስጥ የተቀመጠው ስርአት በሙሉ (እንዳስፈላጊነቱ) ማለፍን የሚጠይቅ ስርአት ነው፡፡ የተሟላ ማስረጃ እስከቀረበ ድረስ ማናቸውም ክርክር በተቀላጠፈ መንገድ መመራት እንደሚገባው ህጉ የሚያስገነዝብ ሲሆን ክርክር እንደተጠናቀቀም ፍርድ/ውሳኔ ወዲያውኑ እንዲሰጥ ሕጉ ግድ ይላል፡፡ ቀጥሮ የሚሰጠው ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት ይረዳል ተብሎ በተከራካሪዎች ጥያቄ ወይንም በፍርድ ቤቱ አስተያየት ሲታመንበት ነው፡፡ አንድ ጉዳይ የሚመራበት የተለየ ስርአት ባልተመለከተበት ጊዜ ወይም የተለየው ስርአት ክፍተት ባለበት ጊዜ ሁሉ ለሁሉም ጉዳዮች የሚፈጸመው ስርአት ይኸው የተቀላጠፈው ስርአት ነው፡፡ ሌሎች ስርአቶች ከመደበኛው ስርአት የተለየና ጉዳይን በአጭር ጊዜ መቋጨት የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን ይዘዋል፡፡ በዚህ ስርአት የሚያልፍ ጉዳይ እልባ የሚያገኝበት ከፍተኛው ጊዜ ሁለት አመት ነው፡፡ ቀላል እና መካከለኛ ጉዳዮች እንደቅደምተከተላቸው በሶስት እና በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ እልባት እንዲያገኙ ይጠበቃል፡፡ ከባድ ጉዳይ ደግሞ አስከ ዘጠኝ ወር ባለው ጊዜ እልባት ያገኛሉ፡፡ ጉዳዮች በዚህ ጊዜ ውስጥ እልባት ስለሚያገኙበት የጉዳይ ፍሰት አስተዳደር የበላይ ፍድ ቤቶች መመሪ ወይንም ማኑዋል እንዲያወጡ ይጠበቃልም፡፡ ጉዳዮቹ በዚህ ህግ የ3፣6 ወይም የዘጠን ወራት ጊዜ የማይጠናቀቁበት የተለየ ምክንያት ከተገኘ ጉዳዩን የሚመለከተው ዳኛ ይህንን ጊዜ እስከ 45 ቀናት፣ 9 ወራት እና 2 አመት ሊያራዝም እንደሚችል በሕጉ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህም የሚሆነው ለተለዩ ጉዳዮች በተለዩት መዝገቦች ላይ በሚሰጥ ትዝዛዝ ነው፡፡ ሁሉም ጉዳይ ከዚህ በታችም ባጠረ ጊዜ ሊጠናቀቅ የሚችልበት እድል ያለም በመሆኑ እያንዳንዱን ጉዳይ መሰረት ያደረገ የጉዳይ ፍስት አስተዳደር መመሪያ በፌዴራል ወይም በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉባኤ እንደሚወጣ ሕጉ ታሳቢ ያደርጋል፡፡

ከመደበኛው ስርአት የሚለየው ሌላው ስርአት የተፋጠነ የክርክር መስመርን የተመለከተው ነው፡፡ በዚህ ስርአት ውስጥ እንደ በወንጀል ጉዳይ ውስጥ የገቡ የወጣት ጥፋተኞች ጉዳይ፣ የደንብ መተላለፍ እና በክለሳ የሚታዩ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች፣ ቀላል የሆነ የእጅ ከፍንጅና የማስረጃ ይዘታቸው ያልተወሳሰቡ እንደ የእጅ ከፍንጅ፣ በቅድመ ክስ ተግባራት የታመኑ ወይም በማናቸውም ደረጃ የታመኑ ጉዳዮች እና ግልፅና የማያሻማ ማስረጃ የቀረበባቸው ጉዳዮች የሚታዩበት ነው፡፡

የወጣት ጥፋተኞች ጉዳይ የወጣቱን የላቀ ጥቅም ማስከበር ያለበት ለመሆኑ ሕገ መንግስታዊ እውቅና ያገኘ ጉዳይ ነው፡፡ የወጣት ጉዳይ አያያዝ ወጣቶች ከገቡበት የተሳሳተ መንገድ እንዲወጡ፣ ቀና አስተሳሰብ እንዲያዳብሩና ሰላማዊና ለህግ ተገዢ የሆኑ ዜጋ እንዲሆኑ የሚያስችል ዘዴን የተከተለ መሆን የሚገባው ለመሆኑ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ያሰምርበታል፡፡ አላማውም ወጣቶቹን ማሰተማር እና ከቤተሰቡና ከህብረተሰቡ ጋር በተሳካ ሁኔታ እንዲዋሃድ ማድረግ ነው፡፡ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ቁጥር 6.4.2. እንደሚያመለክተው ወጣቶች በፍርድ ሂደትም ቀርበው እንዲመሰክሩ፣ ጥፋተኛነታቸውን እንዲያምኑ፣ መስቀልኛ ጥያቄ እንዲጠየቁ ወይም የአቃቤ ሕግ ምስክር ሆነው እንዲመሰክሩ አይገደዱም፡፡ በተቻለ መጠን ጉዳያቸው በአማራጭ መፍትሔም ማለቅ የሚገባው በመሆኑ መንገዱም ሆነ መፍትሔው አማራጭ መንገድን ያሰበ ድንጋጌ ተካቷል፡፡

የወጣት ጥፋተኞችን ጉዳይ በተመለከተ የቀድሞው ሕግ ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ አሰራር እንዲኖር የሚያስችል ድንጋጌ የነበረው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ በሕገ መንግስቱ የታወቁትን ድንጋጌዎች ባሟላ መልኩና አለም በደረሰበት ደረጃ ሕጉን መቃኘት የሚያስፈልግ በመሆኑ ተጨማሪ ድንጋጌዎች በሕጉ ውስጥ እንዲካተቱ ሆኗል፡፡ በመሆኑም የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ይህንን የወጣት ጥፋተኛን ጉዳይ አመራርና አያያዝ አላማ ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት የስርአቶቹ ሁሉ ዋነኛ አላማ የወጣቱን ደሕንነትና ጥቅም ማሰከበር በመሆኑ በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ላይ የወጣት ጥፋተኞች ድንጋጌ አላማ/መርህ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በመርህ ደረጃ በወጣት ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ ተፈፃሚ ከሚሆኑ መርሆዎች ውስጥ ፍጥነት፣ አሳታፊነት፣ ምቹነት፣ አያያዙ የማያስፈራ መሆን፣ መደበኛ ያልሆነ መሆን፣ የተለያዩ ልዩ እውቀት ያላቸው ባለሙያዎች አስተያየት የሚሰጡበትና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ መርሆዎቹ ይበልጥ መከበራቸውን ለማረጋጥ የወንጀል ምርመራ ተግባሩም የሚከናወነው በአቅራቢያው ባለው ፍርድ ቤት መሪነት ነው፡፡ ሕጉ ለወጣቶቹ ጉዳይ የተስማማ ልዩ መርማሪ፣ አቃቤ ህግና ችሎትም እንዲኖር ያስገድዳል፡፡

በመሰረቱ ወጣት ጥፋተኛ የሚባሉት ወንጀል በተፈፀመበት ጊዜ እድሜያቸው ከዘጠኝ እስከ አስራ አምስት አመት ድረስ ያሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ወጣቶች ወንጀል በተፈጸመበት ጊዜ እድሜያቸው በዚህ ክልል ውስጥ ቢሆንም የወንጀሉ ምርመራ በሚደረግበት ጊዜ ግን እድሜቸው ከአስራ አምስት አመት በላይ ሊሆን ይችላል፡፡ እድሚያቸው ከአስራ አምስት አመት በላይ ከሆነ ለወጣቶች የሚደረገው እንክብካቤና አያያዝ ትርጉም የሚያጣበት ሁኔታ ስለሚፈጠር (ለምሳሌ ሞግዚት መመደብ አስፈላጊ ስለማይሆን) የምርመራ

አያያዙና የፍርድ ሂደቱ ለወጣቶች በተደነገገው ሕግ ላይመራ ይችላል፡፡ ቅጣት የሚወሰነው የአእምሮን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በመሆኑ ለወጣቶቹ የተደነገጉት ቅጣቶች የሚፈጸሙበት ቢሆንም የጉዳዩ አመራር ግን በዚህ አግባብ ላይቀጥል ይችላል፡፡ ስለሆነም እድሜው ከ15-18 ከሆነ በፍርድ ቤቱ አስተያየት ጉዳዩ በወጣት ጥፋተኞች ደንብ ወይም በአዋቂዎች ስርአት ሊመራ የሚችል ሲሆን እድሜው ከ18 አመት በላይ ከሆነ ግን ጉዳዩ ለአዋቂዎች በተደነገገው ስርአት እንዲመራ የሚያስችል ድንጋጌን ሕጉ አካቷል፡፡

የወጣቱ ጉዳይ ምርመራ የሚጀምረው ወጣቱ ወንጀል ሲፈፅም ያገኘው ሰው/አካል ፍርድ ቤት እንዳቀረበው ሲሆን ያመጣው ሰው/አካል ስለወንጀሉ ያሰመዘግባል፡፡ ይህ ሰው የሚያስረዳው ነገር ውስጥ ወንጀል የሚመስል ነገር ከተገኘ ፍርድ ቤቱ በወጣቱ ላይ የወንጀል ምርመራ እንዲጀመር የሚያዝ ሲሆን ምርመራውም በፍርድ በቱ መሪነት ተከናውኖ ይጠናቀቃል፡፡

የወጣቱ ጉዳይ በፍርድ ቤት የሚታይ ሆኖ በፍርድ ቤትም ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በአጥፊው ላይ ሊወሰድ የሚችለው እርምጃ ከመደበኛው ቅጣት የተለየ ሆኖ ወጣቱን በመርዳት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የወንጀል ምርመራው ከተለመደው ምርመራ በተጨማሪ ለዚህ መፍትሔ አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉ የወጣቱን ባሕሪ፣ ማሕበራዊ፣ ቤተሰባዊ፣ አካባቢያዊ፣ ትምሕርት ነክ እና ሌሎች ባለሙዎች አስፈላጊ ናቸው በሚሏቸው ጉዳዮች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ መሆን እንዳለባቸው ህጉ ያስገነዝባል፡፡ የሚመለከተቻው አካላትም ለወጣቱ ግንባታ በሚያስፈልግ አግባብ ክትትል እንዲያደርጉ ሊታዘዙ ይችልሉ፡፡ በመርህ ደረጃ ወጣቱ በሞግዚቱ ወይም አግባብ ባላቸው ሰዎች ስር ሆኖ ምርመራውም ሆነ የፍርድ ሂደቱ የሚከናወን ሲሆን በየትኛውም ደረጃ ጉዳይ ክትትል የሚደረገውም በጠበቃ ተወክሎ ነው፡፡ ለወጣቱ ደሕንነትም አስፈላጊ ከሆነ ስለወጣቱ ማሕበረሰባዊ ግንኙነት (የሌሎች ሰዎችን መብት ሊነክ ቢችልም) ጊዜያዊ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህ ትእዛዝ ለወጣቱ ጥቅም ሲባል አስተያየቱን በመቀበል የሚሰጥ ሲሆን ትእዛዙም በወጣቱ ቤት ውስጥ ያለ ሰው ቤት እንዲለቅ፣ ወጣቱን የተወሰኑ ሰዎች እንዳያገኙት ወይም እንደይጎበኙት የማድረግ እና የመሳሰሉት/ን እርምጃዎችን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

ክሱ የዳኝነት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የሚታይ ቢሆንም ለወጣቱ ጥቅም ሲባል ወደ ሌላ የስረ ነገር ወዳለው ፍርድ ቤት ሊዛወር ይችላል፡፡ የተዛወረለት ፍርድ ቤትም ጉዳዩን አልቀበልም ለማለት አይችልም፡፡ የፍርድ ሂደቱም የተወሰኑ ሰዎች ብቻ በተገኙበት በዝግ ችሎት የሚካሔድ ነው፡፡ ክስ የቀረበበት እንደሆነም እንደመደበኛው ስርአት ክሱ በንባብ የሚነበብለት ከሚሆን ይልቅ በቃል የሚነገረው ይሆናል፡፡ ሒደቱ

በሙሉ መደበኛ ያልሆነ ስርአትን የሚከተል ነው፡፡ በማናቸውን መንገድ ውሳኔው ለሕዝብ የሚገለፅ ቢሆንም እንኳን ዘገባዎቹ ወጣቱ ተለይቶ እንዲታወቅ የሚያደርጉ (እንደ ስሙ፣ ምስሉ፣ አድራሻው፣ ትምሕርት ቤቱ....) ፍሬ ነገሮችን መያዝ አይገባውም፡፡ ዘገባው ለሕዝብ መገለፁ የራሱ ጥቅም ቢኖረውም ዝርዝር ጉዳዮቹ የወጣቱ የወደፊት ህይወት ላይ የራሳቸውን አሉታዊ ሚና የሚጫወቱ በመሆኑ ቢዘገቡ ወጣቱ በማናቸውም መንገድ እንዲለይ በሚያደርግ መልክ አይዘገቡም፡፡ ፍርዱም በቅርጽ ደረጃ መደበኛ የፍርድ ቅርፅ ቢኖረውም በይዘቱ ግን የወጣቱን እድገትና ስብእና በማናቸውም መልኩ በማይጎዳ አግባብ መፃፍ ይኖርበታል፡፡ እንደምርመራው ሁሉ የእርምት እርምጃዎች ላይ አግባብነት ያላቸው ባለሙያዎች አስተያየት ሊሰጡ ያስፈልጋል፡፡

በወጣቱ ላይ ሊወሰድ ከሚችለው እርምት እርምጃ በተጨማሪ ወጣቱ ወደ ጥፋት እንዲገባ ያደረገውን እንክብካቤ ያጓደሉ ሰዎች ያልተከሰሱና ራሱን በቻለ ወንጀል ያልተጠየቁ ከሆነ በፍርድ ቤቱ ተጠርተው ተግሳፅ፣ ማስጠንቀቂያ ወይም ሌላ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ሊደርግ ይችላል፡፡ ለወጣቱ ደሕንነት አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ አግባብ ያላቸው ባለሙያዎች የሚሰጡትን አስተያየት መሰረት በማድረግ በወጣቱ ላይ የተሰጡ ማናቸውም የእርምት እርምጃዎች በማናቸውም ጊዜ ሊለወጡ፣ ሊቀየሩ ወይም ቀሪ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

የተፋጠነ ስርአት ውስጥ ከሚመደቡ ስርአቶች ውስጥ ሌላው የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች የሚመለከተው ስርአት ነው፡፡ ደንብ መተላለፍን በተመለከተ በዋነኛነት ጉዳዩ የክልሎች ወይም ከፍትሕ አካላት ውጪ ያሉን አስፈጻሚ የመንግስት አካላትን የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም በደንብ መተላለፍ ጉዳይ ላይ ክስ የሚያቀርበውን፣ የዳኛነት ውሳኔ የሚሰጠው፣ የሚጣለው ቅጣት አይነት እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርአቱ ሁሉ ደንቡ በሚወስነው አግባብ የሚፈጸም ነው የሚሆነው፡፡ በዚህ አግባብ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች በዋነኛት መተላለፉን በደነገገው ደንብ ወይም በሕጉ ልዩ ክፍል የሚመራ ቢሆንም በልዩ ደንቦች ባላተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ብቻ በሥነ ሥርአቱ የተደነገጉት ስርአቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

በሕጉ መሰረት የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች ሁሉ በቀላል ስርአት አልፈው በሁለት ሳምንት ውስጥ  አልባት እንዲያገኙ ይጠበቃል፡፡ በደንብ መተላለፍ ጉዳይ ላይ ከሳሻም የሚሆነው ደንቡን የሚያስፈፅመው አካል ሲሆን ይህም ካልተመለከተ አቃቤ ሕጉ ጉዳዩን በከሳሽነት ሊከታተል ይችላል፡፡ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችም መደበኛ ያልሆነውን ስርአት ሊከተሉ የሚችሉ ከመሆናቸው በላይ በአብዛኛው በገንዘብ መቀጮ

የሚያስቀጡ በመሆናቸው የደንብ ተላላፊው ሌላ ስራ ትቶ ፍርድ ቤት መቅረብ ግድ አይሆንበትም። በመሆኑም የደንብ መተላለፍ የቀረበለት ፍርድ ቤት ማመልከቻውን ለደንብ ተላላፊው የሚላክለት ሲሆን መጥሪው የተላለፈለት ተከሳሽም ፍርድ ቤት ሳይቀርብ በማመን መቀጫውን ጭምር በወኪሉ፣ በፖስታ ቤት መልእክት ወይም በሌላ አመቺ በሆነ አግባብ ለፍርድ ቤቱ ሊልክ ይችላል። ፍርድ ቤቱም የገንዘብ መቀጮ ብቻ የሚቀጣው ከሆነ ቅጣቱን ወስኖ ተከሳሽ ከላከው መቀጮ ጋር ልዩነቱ እንዲታሰብ ያደርጋል። ተከሳሽ ያልቀረበም እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ተመልክቶ ውሳኔ በመስጠት ውሳኔውን እንዲፈጽም ይልክለታል።

ከፍ ሲል በተመለከተው መሰረት የደንብ ተላላፊው ፍርድ ቤት መቅረብ የማያስፈልገው ቢሆንም የደንብ ተላላፊው በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል ወይም እንዲቀርብ ሊገደድ ይችላል። የመጀመሪያው ክሱን የካደ እንደሆነ ነው። በዚህ ግዜ ተከሳሹ ቀርቦ የመከራከርና የመከላከያ ማስረጃ የማሰማት መብት ይኖረዋል። ደንብ ተላላፊው ቀርቦ የሚከራከር ቢሆንም ክርክሩ በተቀላጠፈ ሁኔታና በቃል ብቻ የሚደረግ ይሆናል። የሚሰሙ ምስክሮች ካሉም በዋናው ፍሬ ነገር ላይ ብቻ የሚመሰክሩ ሲሆን ቃላቸውም በሙሉ ሳይመዘገብ ከቃላቸው ውስጥ ዋናው ብቻ ተለይቶ ይመዘገባል። የደንብ መተላለፍ የፈፀመው ሰው ፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችልበት ሌላው ምክንያት በፍርድ ቤት የሚወሰነው ቅጣት ከገንዘብ ቅጣት ውጪ የሆነ እንደሆነ ነው።

በደንብ መተላለፍ ስርአት ውስጥ የሚገኘው ሌላው ልዩ ስርአት የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች በክለሳ (ሳመሪ) ስርአት የሚታዩበት ስርአት ነው። በተወሰኑ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች ላይ የቀረበው ክስ ግልጽና በተከሳሹ የማይካዱ ሲመስሉ አቃቤ ሕግ (ወይም ከሳሹ) ከክሱ ጋር ተከሳሽ ሊቀጣ ይገባዋል የሚለውን የቅጣት መጠንና አይነት አካቶ ክስ እንዲያቀርብ ሕጉ የሚፈቀድ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የቅጣት መጠኑን እንዳለ በመቀበል ለተከሳሽ ይልክለታል። ተከሻሽም ጥፋቱን አምኖ ከተቀበለው ፍርድ ቤቱ ከክሱ ጋር የተመለከተውን ቅጣት ተከሳሹ እንደፈጸም ትእዛዝ በመስጠት መዝገቡን ይዘጋዋል። ተከሳሽ መጥሪያው ደርሶት በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ መልስ ካልሰጠም ክሱን እንዳመነ ተቆጥሮ በተመሳሳይ ውሳኔውን እንዲፈፅም ይታዘዛል። ተከሳሽ ክዶ ከተከራከረ ግን ጉዳዩ በደንብ መተላለፍ ደንብ መሰረት ይታያል። በዚህ መልኩ ከሚካተቱት ቅጣቶች ውስጥ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሆነ ቅጣት፣ የስራ ፈቃድን (ላይሰንስን) መመለስን የሚመለከት ቅጣት፣ በገንዘብ ብቻ የሚያስቀጣ የደንብ መተላለፍ፣ በአንድ ነገር ከመገልገል መከልከልን የሚመለከት ቅጣትና የመሳሰሉት ይገኙበታል።

በተፋጠነ ስርአት የሚታው ሌላው ጉዳይ የእጅ ከፍንጅ ጉዳይ ነው። የእጅ ከፍንጅ ጉዳይ ከዚህ ቀደም መሰል እና ተመሳሳይ በመባል የሚታወቁትን በማካተት በሕጉ አንድ ወጥ ግልጽ ትርጉም ተሰጥቶታል። በባህሪው ማስረጃ የተሟላበት ስለሆነ ያለቀጠሮ ያልቃል ተብሎ የሚታሰብ ነው። ይህ ሂደት የመደበኛ ስርአቶችን መከተልን ግድ ሊል ቢችልም በባህሪው ያልተወሳሰበ እና የተሟላ ማስረጃ የሚቀርብበት በመሆኑ ቢዘገይ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ እልባት የሚሰጥት ጉዳይ ነው። ከመደበኛው ስርአት የሚለየው ክርክር የማይቆራረጥበት መሆኑና ይህ አጭር የጊዜ ገደብ ያለው መሆኑ ነው።

የታመኑ እና በአማራጭ መንገዶች የታዩ ጉዳዮችም በዚህ ስርአት ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። እነዚህ ስርአቶች ከሌሎቹ ለየት የሚያደርጋቸው ሙሉ የክርክር መስመርን ማለፍ የማይጠበቅባቸው ሲሆኑ ሁነቶቹ እንደተከሰቱ (ለምሰሌ እንደታመነ፣ የእርቅ ውጤት እንደቀረበ) ያለ ቀጠሮ ወዲያውኑ ውሳኔ የሚሰጥባቸው መሆናቸው ነው።

## 13.7. ቀጠሮ፣ መቃወሚያና እምነት ክህደት

ክርክሮች በየትኛውም አግባብ የሚመሩ ቢሆን ክርክር በመሰረቱ ሳይቆራረጥ በተከታታይ መመራት ያለበት ነው። ይህ መርህ በግልጽ የተመለከተ ከመሆኑም በላይ ቀጠሮ ሊያሰጡ የማይገባቸው ምክንያቶችም (ለምሳሌ ለረፍት፣ ለሬጂስትራር ተግባራት፣ በህግ ጉዳይ ላይ በቀረበ መቃወሚያ ብይን ለመስጠት፣ እና ለመሰል ምክንያቶች) በሕጉ ላይ በግልጽ ተቀምጠዋል። ጉዳዩ በተከታታይ የታየ ለመሆኑ የሚመለከትበት አንዱ መንገድ የእለት ተግባራትን በመዝገብ በአግባቡ መመዝገብ ሲቻል ነው። በመሆኑም ጉዳዩ መታይት ከጀመረበት ሰአት አንስቶ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ ያለው የየእየለቱ የችሎት ክንውኖች እና ሌሎች ፍሬ ነገሮች (ለምሳሌ የችሎቱ ስም፣ የዳኛና ተከራካሪ ወገኖች ስም፣ ፊረማ...) በመዝገብ ላይ መስፈር ወይም በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ መቀረፅ የሚገባቸው እንደሆነ ሕጉ ድንጋጌ የያዘ ሲሆን ይህም ለግልጸኝነት፣ ለተጠያቂነት እንዲሁም ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተግባር አጋዥነት እንዲሆን ታስቦ የተካተተ ነው። ይህ ተግባር በክስ መስማት ጊዜ በተለየ ትኩረት የሚፈፀም ቢሆንም ፍርድ ቤት ማናቸውንም ተግባራት በሚያከናውንበት ጊዜ እነዚህ ኩነቶች መመዝገብ ወይም መቅረፅ ይጠበቅበታል።

ክርክር ተከታታይ ቢሆንም በተወሰኑ ምክንቶች በተለይም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሲባል ቀጠሮ መስጠት የሚያስፈልግ በመሆኑ ይህንን ሁኔታ ያገናዘበ ቀጠሮ የሚሰጥባቸውን ምክንያቶች እና ለቀጠሮ ልክ መወሰኛ መርህን ህጉ ያስቀምጣል። በዚህ ረገድ ነባሩ ህግ ላይ መሰረታዊ ለውጥ አልተደረገም።

ቀጠሮ ከሚሰጥባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የተከሳሽ የጤንነት ሁኔታ ነው። የችሎት ተግባር ተከታታይ ቢሆንም ተከሳሽ በአእምሮ ወይም በአካሉ ላይ በደረሰበት የጤና ችግር የተነሳ የችሎት ተግባርን በአግባቡ ለመከታተል የማይችል ሊሆን ይችላል። የዚህ አይነት አጋጣሚዎች በተግባር የሚያጋጥሙ ቢሆንም ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ህግ የሌለ በመሆኑ የፍትህ አካላት ሲቸገሩ ቆይተዋል። ይህ ሁኔታ በህግ ሊፈታ የሚገባው በመሆኑ ተከሳሽ በክስ መስማት ሂደት በጤናው የተነሳ ችሎቱን መከታተል ያልቻለ እንደሆነ እንደሁኔታው ችሎቱ ለተወሰነ ጊዜ የጉዳዩን መታየት የሚያቋርጥበት ወይም ጉዳዩ ላይ ፍርድ ሰጥቶ ቅጣት የማይወስንበት ነገር ግን አማራጭ እርምጃዎች (መፍትሔዎች) እንዲወሰዱ የሚደረግበት አግባብ ተደንግጓል። ተከሳሹም የጤንነቱ ሁኔታ በተመለሰለት ጊዜ ክርክሩ እንደገና እንዲታይ የመጠየቅ መብት አለው።

ፍርድ ቤት በማናቸውም ቀጠሮ በሰጠባቸው ጊዜያት የሚያከናውናቸው ተግባራት አሉ። ከእነዚህ ተግባራ ውስጥ ተከራካሪ ወገኖች መቅረባቸውን የማረጋገጥ፣ ማንነታቸውን ማረጋገጥና የመሳሰሉት ተግባራት ይገኙበታል። ፍርድ ቤቱ የተከሳሽን ማንነት ለማረጋገጥ ከተለመዱት ስም፣ እድሜ፣ ስራና አድራሻ በላይ ሌሎች ጥያቄዎችን ጭምር ጠይቆ መመዝገብ እንደሚችል በሕጉ ተደንግጓል። ተጨማሪዎቹ ጥያቄዎች ፍርድ ቤቱ በሰተኋላ ለሚያከናውናቸው ተግባራትም ጠቀሜታ አላቸው። ለምሳሌ የተከሳሽ ቤተሰብ ብዛት ወይም እምነቱ የማንነቱ ማረጋገጫ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በቅጣት ውሳኔ ወቅት ወይም ማስረጃ በሚመረመርበት ወቅት ሃሰተኛ ማስረጃ እንደያቀርብ ወይም ለሚቀርበው ክርክር ታማኝነት ለመፈተሽ የሚያግዝ ጠቃሚ ማገናዘቢያዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ማንነትን ማረጋገጥን በተመለከተ ሕጉ ዝም ከማለት መብት ጋር ያለውን አፈጻጸም የሚዳስስ ድንጋጌን አካቷል። በክርክር ሒደት ዝም የማለት መብት ያላግባብ ጥቅም ላይ የሚውልበት አጋጣሚዎችም ያሉ በመሆኑ ተከሳሹ ማንነቱን በማረጋገት ሂደት ውስጥ ዝም የማለት መብት አለኝ ሊል እንደማይችል ተመላክቷል። በቀሪ ጉዳዮች ላይ ግን ለሚቀርብለት ጥያቄ ዝም ማለት መብቱ ነው። የተከሳሽ ማንነት ከተረጋገጥ በኋላ የሚቀጥለው ተግባር የቅድመ ክስ መስማት ተግባራት እንዲከናወኑ የታዘዘ ከነበረ ይኸው መፈጸሙን ማረጋገጥና ከተፈጸመው ተግባር ቀጥሎ ያለውን ተግባር ማከናወን ነው። ስለሆነው ፍርድ ቤቱ በአብዛኛው በቀጥታ ክሱን (እያዳንዱን ክስ) በንባብ ወደ ማሰማትና ተከታይ ተግባራትን ወደ ማከናወን ይገባል ማለት ነው። ክሱ ከተነበበ በኋላ ተከሳሹ ክሱን (ወይም እያንዳንዱን ክስ) በአግባቡ የተረዳው ለመሆኑ ፍርድ ቤት በቀጥታ ጠይቆ ያረጋግጣል። ተከሳሹም የክስ መቃወሚያ ያለው እንደሆነ

ያቀርባል። የክስ መቃወሚያ የሚቀርብባቸው ምክንያቶች በሕጉ ውስጥ በዝርዝር የተመለከቱት ቢሆንም ዝርዝሩ አመላካች እንጂ ያለቀለት አይደለም። ስለሆነም ፍርድ ቤትን ወደ ፍሬ ነገሩ የማያስገባ ማናቸውም መቃወሚያዎች ክርክር በሚካሔድበት ወቅት እየቀረቡ ፍርድ ቤቱን ወደ ኋላ የሚመልሱ እንዳይሆኑ ቀድመው መነሳት የሚችሉበትን እድል ማስፋቱ የተገባ ነው። በሌላ በኩል ህንን ሰፋ ያለ እድል አላስፈላጊ በሆነው አግባብ ጥቅም ላይ በማዋል አላስፈላጊ ፍሬ ነገር ውስጥ እየተገባ ክርክር ያለቦታው እንዳይቀርብም ዳኛው ይቆጣጠራል ተብሎ ይታሰባል።ይህ እድል ከመጀመሪያው የሰፋ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዳይሰጥ የሚያደርጉ መቃወሚያዎችም ወደፊት በማናቸውም ጊዜ ሊነሱ ይችላሉ። የዚህ አይነት መቃወሚያዎችን ተከሳሽ በወቅቱ አያነሳቸውም ተብሎ የማይጠበቅ ከመሆኑም በላይ መቃወሚያዎች ሳይፈቱ ፍርድ ቤቱ የሚጸና ውሳኔ ይሰጣል ተብለው ስለማይታሰብ ወደፊት መነሳት እንዲችሉ መፈቀዱ ምክንያታዊ ነው። መቃወሚያ በመሰረቱ ከፍሬ ጉዳይ በፊት ያለ ክርክር በመሆኑ በተቻለ ወጠን ወዲያውኑ ወመሰን ይገባቸዋል። በተለይም መቃወሚያዎቹ የሕግ ጉዳይን የሚመለከቱ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ያለቀጠሮ ውሳኔ ሊሰጥባቸው እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ድንጋጌ ተካቷል።

መቃወሚያ ያልቀረበ ወይም መቃወሚያው ውድቅ የተደረገ እንደሆነ የሚቀጥለው ሥነ ሥርአት የተከሳሹን እምነት ክሕደት ቃል መቀበል ነው። ተከሳሹ የእምት ቃል የሰጠ እንደሆነም አምኗል በሚል ብቻ ተመዝግቦ ውሳኔ የሚሰጥበት ሳይሆን የእምነት ቃሉ ከክሱ ጋር በሚጣጣም መልኩ ተዘርዝሮ መመዝገብ ይገባዋል። ይህም ተከሳሹ በእርግጥ የክሕደት ቃል እየሰጠ አምኗል በሚል ውስኔ እንዳይሰጥና የመከላከል መብቱ ያላግባብ እንዳይጠብ ያስችላል። ተከሳሹ በግልጽ ክሱን ከካደ፣ ዝም ያለ እንደሆነ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ጥፋተኛ አይደለሁም እንዳለ ተቆጥሮ ክሱ በማስረጃ እንዲረጋገጥ ይሆናል። ምንም እንኳን ተከሳሹ ክዶ የተከራከረ ቢሆንም በሂደት ወንጀል የፈጸመ ለመሆኑ የእምነት ቃሉን መስጠት ሊፈልግ ይችላል። በነባሩ ሕግ ይህንን ሁኔታ በቀጥታ የሚያስተናግድ ስርአት አልነበረም። የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ይህንን ክፍተት በመሙላት ተከሳሽ በሒደት የእምነት ቃሉን ሊሰጥ እንደሚችል ይደነግጋል። ይሁን እንጂ ተከሳሹ በዚህ ደረጃ የሚሰጠው ቃል በእርግጥ በመጸጸት የሚሰጠው ቃል እንጂ ክርክ ስለረዘመበት ለማሳጠር፣ ሌላ ወንጀል የፈጸመ ሰውን ለመደበቅ ወይም በማናቸውም ምክንያት እውነቱ እንዳይወጣ ለመደበቅ አለመሆኑን ግን ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

## 13.8. የማስረጃ ደንቦች

ኢትዮጵያ በአመዛኙ የሲቪል ሎው የሕግ ሥርዓትን የምትከተል አገር በመሆኗ የአገሪቱ የሕግ መፃሕፍት ወይም ኮዶች የተደራጁትና የዳኝነት ሥርአቱ የሚመራው በዚሁ የሕግ ስርአት ዘንግ አግባብ ነው። አንዳንድ የኮመን ሎው የሕግ አስተሳሰቦችና ፍልስፍናዎች በሥነ ሥርዐት ሕጎቻችን የተካተቱ ቢሆንም የተደራጁትና የተቀረጹት ግን በሲቪል ሎው የሕግ ሥርዓት እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ። በመሆኑም የኢትዮጵያ የማስረጃ ሕግ ድንጋጌዎች የተደራጁትና የተካተቱት በሲቪል ሎው የአቀራረጽና የአቀራረብ ሥርዓት ነው። የማስረጃ ሕጎች/ደንቦች በፍሬ ሕግ እና በሥነ ሥርዐት ሕጎች ውስጥ በተወሰነ ደረጃ በየቦታው ተካተው የሚገኙና ሲሠራበቸው የቆዩ መሆናቸው የሚታወቅ ከመሆኑ አንፃር የማስረጃ ሕግ የለንም የሚለው ጥቅል ድምዳሜ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል የማይቻል መሆኑን ያመለክተናል። ይሁን እንጂ በፍሬ ሕግም ሆነ በሥነ ሥርዐት ሕጎች ውስጥ ያሉት ደንቦች የተሟሉ ካለመሆናቸውም በላይ ለበርካታ ዘመናት ያገለገሉ በመሆናቸው በአሁኑ ወቅት ዘመኑ የወለደውን ዘመናዊ የኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ለውጦች እና መስተጋብሮችን ሙሉ በሙሉ ሊገዙ አልቻሉም። በመሆኑም በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት እና የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው ተቀባይነት ያገኙ የማስረጃ መርሆዎች በሕጎቹ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ያልተሸፈኑ ከመሆናቸውም በላይ ዘመኑ የፈጠራቸው የዳበሩ አዳዲስ መርሆዎችና አስተሳሰቦችም በተመሳሳይ ሁኔታ በሕጎቹ ውስጥአለመካተታቸው የማስረጃ ሕግ እንዲኖር ግድ ብሏል። ከዚህ አንፃር የማስረጃ ሕግ መኖሩ ግድ ከሆነ አወጣጡን በተመለከተም የሚኖሩት አማራጮች፤

1. ሁሉንም የማስረጃ ሕግ ደንቦችን የያዘ አንድ የማስረጃ ሕግ ወይም ኮድ ማውጣት፤
2. ዋና ዋና መርህዎችን ብቻ የያዘ ልዩ የማስረጃ ሕግ ማውጣት፤
3. በየኮዱ ውስጥ ያሉትን የማስረጃ ድንጋጌዎችን በማሻሻል የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ አካል አድርጎ ማውጣት፤

ሲሆኑ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ቅድመ ረቂቅ ጥናት ላይ እንደተመለከተው ሶስተኛው አማራጭ ከወንጀል ፍትሕ ስርአቱ ጋር የተጣጣመና በተሻለ ሁኔታ የማስረጃ ሕግ ችግሮችን ሊቀርፍ እንደሚችል በማመላከቱ የወንጀል ነክ የማስረጃ ድንጋጌዎችን የዚህ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ አካል ሆኖ ወጥቷል።

በመሆኑም ከዚህ ቀደም የነበረው የስነ ስርአትና ማስረጃሕግ የተወሰኑ የማስረጃ ደንቦችን የያዘ ቢሆንም ይህ የሥነ ስርአት ህግ ከዚህ ቀደም ከነበረው በመሰረቱ በተለየ መልኩ በወንጀል ጉዳይ ተፈጻሚ የሚሆኑ የማስረጃ ደንቦችን በዝርዝር አካቷል። የነበረው ሕግ የማስረጃ ደንቦችን እጅግ በተቀነጨበ ሁኔታ እዚህም እዚያም ይዞ የነበረ ቢሆንም በማስረጃ ጉዳይ ላይ የሚነሱ በርካት ጥያቄዎችን ሳይመልስ ቀርቷል። ስለሆነም በተግባር እንደሚታየው በማስረጃ ጉዳይ ላይ ከአገራችን ስርአት ይልቅ ከፍትህ ስርአታችን ጋር ስለመጣጣሙ በአግባቡ ያልተረጋገጠ ስርአት ወይም የሌሎች አገራት መርሆዎችና አሰራሮች ሲተገበሩ እንደነበር ይታወቃል። ይህ ወጥ አሰራር እንዳይኖር ያደረገ በመሆኑ በወንጀል ጉዳይ ወጥ ያልሆነ አሰራር በሰብአዊ መብት ላይ የሚያሰከትለው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑ ግልጽ ነው።

እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በማስረጃ ጉዳይ ላይ በርካት ውሳኔዎችን አሳልፏል። ይህም ቢሆን የሰበር ውሳኔ የሚሰጠው ለፍርድ ቤቱ የቀረበን ክርክር ብቻ መሰረት አድርጎ በመሆኑ ለሁሉም ጥያቄዎች በአንድ ጊዜ መልስ የመስጠት አቅም አይኖረውም። በመሆኑም ሌሎች አገራትን ልምድ በመውሰድና በወንጀል ጉዳይ ላይ ወጥነትን በማረጋገጥ ውጤታማ የፍትሕ አስተዳደር እንዲኖር እንዲሁም በክርክር ሂደት የፍትሕ አካላት እውነትን የማውጣት ሃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ለማስቻል የማስረጃ ደንቦችን በተቻለው መጠን ግልጽና ለአጠቃቀም በሚያመች መልክ የሥነ ስርአት ህጉ አካል እንዲሆኑ ተደርጓል።

ከዚህ አንፃር ሕጉ በማስረጃ ጉዳይ ሕጉ ማስረጃ ምንድን ነው የሚለውን በመጀመሪያ ደረጃ ግልጽ ያደርጋል። በዚህ መሰረት ማስረጃ በመሰረቱ አግባብ የሆነን ነገር ሁሉ ለማስረዳት የሚቀርብ ማንኛውም ነገር እንደሆነ የተደነገገ ሲሆን ይህም የተከሳሽ ቃልን፣ ምስክርን፣ የህሊና ግምትን፣ ግንዛቤ የሚወሰድባቸው ጉዳዮችንና ሌሎች ማስረጃዎችን ያካትታል። እነዚህ ማስረጃዎች በዋነኛት የተካደ ነገርን ለማስረዳ የሚቀርቡ ሲሆን የታመኑ እና በፍርድ ቤት ግንዛቤ የሚወሰድባቸው ነገሮች በማስረጃ መረጋገጥ የሚያስፈልጋቸው አይደሉም።

ማስረጃ ሁሉ በጭብጥ ለተያዘው ነገር አግባብነት ያለውና ተቀባይነት ያለው መሆን እንደሚገባው ሕጉ ያስቀምጣል። ጭብጥ የሚባለውም ከሳሽና ተከሳሽ ያልተማመኑባቸው ማናቸውም ነጥቦች ሁሉ ናቸው። ለምሳሌ ተከሳሽ ክስን ከላይ በተመለከተው ማናቸውም አግባብ ክዷል የሚባል ቢሆን የዐቃቤ ሕግ ክስ መረጋገጥ የሚገባው ጭብጥ ይሆናል ማለት ነው። ጭብጥን የሚያስረዳው አግባብነት ያለው ማስረጃ

ሲሆን ለአረዳድ እንዲቀልም አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች በግልጽ ተዘርዝረው ተመልክተዋል፡፡ ማስረጃዎች ሁሉ ሕጉን ተከትለው የተገኙ መሆን እንዳለባቸው በግልፅ የተደነገገ ከመሆኑም በላይ ሕገ መንግስቱና የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው (ቁጥር 3.16) በሚደነግጉት አግባብ በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘ ማስረጃ እንዲሁም በሥነ ሥርአቱ ከተደነገገው ስርአት ውጪ የሰብአዊ መብት ጥሰትን ባሰከተለ መንገድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት እንዳይኖረው የሚያስገድድ ሕግም ስነ ስርአትና ማስረጃህ ጉ አካቷል፡፡

በማስረጃ ዝርዝር ውስጥ መጀመሪያ የተመለከተው የሰው ምስክር ነው፡፡ የሰው ምስክርን በተመለከተ ህጉ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጉዳይ የመመስከር ብቃት እንዳለው የሚገመት እንደሆነና የመመስከር ግዴታም ያለበት ለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ ማንኛውም ሰው በተያዘው ጉዳይ ላይ ለጊዜው ወይም በአጠቃላይ የመመስከር ብቃት የለውም ሊባል የሚችለው ጉዳዩን የሚመለከተው ፍርድ ቤት ከተከሳሽ ሁኔታ (እድሜ መጃጃት፣ ጤንነት፣ወይም ሌላ ምክንያት) ላይ ተመስርቶ ምስክሩ በትክክል ጥያቄዎችን ለመረዳትም ሆነ የተረዳውን ለማስረዳት የማይችል ነው በማለት ሲወስን ነው፡፡ ከሙብት የተሻረ ልዩ አዋቂ ግን በሕግ መሰረት ከሙብት የተሻረ በመሆኑ የሙያ ምስክር ለመሆን ብቃት አይኖረውም፡፡

ማንኛውም ሰው የመመስከር ግዴታ ቢኖርበትም ከተከሳሽ ጋር ባለው ጥበቃ በሚደረግለት ልዩ ግንኙነት (የሓይማኖት፤የሕክምና፣ የጥብቅና ግንኙነት፣ የትዳር ግንኙነት) የተነሳ ያወቁትን እንዲመሰክሩ አይገደዱም፡፡ በዚህ ልዩ ግንኙነት የተነሳ የተገኘ እውቀት እንዲመሰከር ግዴታ ቢጣል ግንኙነቶች በጥብቅ ሚስጥር ላይ የሚመሰረቱና ለሕብረተሰቡ ማሕበራዊ ግንኙነትም መሰረታዊ በመሆናቸው ግንኙነቶቹ እንዳይኖሩ የማድረግ ውጤት ስለሚኖረው ጥበቃ መደረጉ ተገቢ ነው፡፡ የግንኙነቱ ባለቤቶች ግን ይህንን መብት ላለመጠቀም ሊፈቅዱ ይችላሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በመንግስት ሚስጥር ነው የተባለን መረጃ/ማስረጃ፣ ከአገር ደህንነት ጋር እንዲሁም በልዩ የምርመራ ዘዴ ስለተገኘ ማስረጃ እውቅና ያላቸው ሰዎች በዚህ ረገድ ስለሚያውቁት ነገር መመስከር የማይችሉ ከመናቸውም በላይ ለመመስከር በግል ቢፈቅዱም እንኳን እንዲመሰክሩ የሚፈቀድላቸው አይደሉም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ጥበቃ የሚደረግለት ምስክሩ ስለተሳተፈበት ስርአት እንጂ ስለግል ግንኙነት ባለመሆኑ መብቱን ላለመጠቀም በመወሰን መመስከር አልተፈቀደም፡፡

የምስክርን ብዛት እና የአቀራረብ ቅደም ተከተልን የመወሰን መብት ምስክርን የሚያቀርበው ወገን መብት በመሆኑ አንድን ጉዳይ (ክስን ጨምሮ) በተለምዶ ከሚነገረው በተቃራኒው በአንድ ምስክር ብቻም ቢሆን

ማስረዳት ይችላል፡፡ ምስክርን የሚያቀርብ ወገን ምስክርን በሃሰት ከማሰጠናት መቆጠብ ያለበት ሲሆን ምስክሩ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ትክክለኛ ቃሉን እንዲሰጥ ግን ቀድሞ አግኝቶ ሊያዘጋጀው ይችላል፡፡ ምስክሩ የሚመሰክርበትን ልክ በተመለከተም ምስክር ቃል ሊሰጥ የሚችለው ስለሚውቀው ጉዳይ ብቻ እንደሆነ ሕጉ በግልፅ ደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌም ከዚህ በፊት ቀጥታ/ቀጥታ ያልሆነ፣ የስሚ ስሚ እና ተዘዋዋሪ ማስረጃዎች በሚል ይታዩ የነበሩ የአረዳድ ብዥታዎችን በማጥራት ወጥ አረዳድ እና ትግበራ እንዲኖር ያስችላል በሚል እምነት ተስተካክሎ የገባ ነው፡፡ በሕጉ መሰረትም ምስክር የሚያውቀውን ያስረዳል ማለት አንድ ምስክር ሊመሰክር የሚገባው በአምስቱ የስሜት ሕዋሳቶቹ አማካኝነት በቀጥታ ስለተረዳው ጉዳይ ነው ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ምስክሩ በአይኑ ስላየው፣ በጆሮው ስለሰማው ወይም በአፍንጫው ስላሸተተው ጉዳይ ሊመሰክር ይችላል፡፡ አንድ ሰው በመሞት ላይ እያለ ለምስክሩ "አከሌ ነው የገደለኝ" ብሎ ቢነግረው ምስክሩ ይህንን የሰማውን ቃል ለፍርድ ቤት ማስረዳት ይችላል፡፡ ይህንን መመስከር ምስክሩን የስሚ ስሚ አያደርገውም፡፡ አንድ ሰው ቤት ያቃጠለ ለመሆኑ ክስ ቢመሰረትበት አንደኛው ምስክር ተከሰሹ ክብሪት ሲገዛ የተመለከተ ለመሆኑ፣ ሁለተኛው ጭስ የሸተተው መሆኑን፣ ሶስተኛው ምስክር ደግሞ ተከሳሹ ጋዝ ሲገዛ የተመለከተ ለመሆኑ መመስከር ይችላሉ፡፡ እነዚህ ምስክሮች ስለ ቃጠሎ የሚያውቁት ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ቢሆንም የሚመሰክሩት የሚያውቁትን ብቻ በመሆኑ ምስክርነቱ ቀጥተኛ መሆን አለመሆን ላይ ለውጥ አያመጣም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ምስክሮቹ የሚመሰክሩት በቀጥታ በስሜት ሕዋሳታቸው አማካኝነት ስለተረዱት ጉዳይ በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት እስካላቸው ድረስ ተቀባይነት አላቸው፡፡ ስለሆነም ምስክር የሚመሰክረው በቀጥታ ስለሚያውቀው ነገር ነው በማለት ህጉ ሲደነግግ ከሌላ የሰማውን፣ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ያወቀውን አይመሰክርም ማት አይደለም፡፡ ማስረጃው በቀጥታ አይሁ ብሎ እንደሚመሰክረው ሁሉ ሌላ ሰው ነገረኝ ብሎ መመስከር ይችላል፡፡ ትልቁ ጉዳይ ምስክሩ በማናቸውም መንገድ ያወቀውን በቀጥታ ሲናገር በዳኛ ምዘና የሚሰጠው የማስረጃት ክብደት ነው፡፡

ምስክር የሚያውቀውን ለማስመስከር ወይም ስለሚያውቀው ጉዳይ በትክክል እየመሰከረ መሆኑን ለመፈተሽ ዋና፣ መስቀልኛ፣ ድጋሚ፣ ማጣሪያ እና ማስተባበያ ጥያቄዎች እንዳግባቡ ሊቀርቡለት ይችላሉ፡፡ የጥያቄዎች ምንነት በሕጉ ውስጥ በግልጽ የተመለከቱ ሲሆን በጥያቄዎቹ አቀራረብ ላይ የተወሰኑ ገደቦች ተደርገዋል፡፡ ለምሳሌ በተወሰነ ምክንያት (አሰጠቂ፣ የረሳ፣ በፍቃድ…) ካለሆነ በቀር ምስክርን የጠራ ወገን ለምስክሩ መልስ በሚነግር ሁኔታ እየመራ ሊጠይቅ አይችልም፡፡ በተመሳሳይ ምክንያት ምስክርን በማዋረድ፣ ማንነቱን በመንካት ማንኛውንም ጥያቄ መጠየቅ ከስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ አላማ የሚወጣ

በመሆኑ እነዚህና መሰል ጥያቄዎችም የተፈቀዱ አይደሉም። የዚህ መሰል ጥያቄዎች በማናቸውም ሁኔታ ምስክር በትክክል የሚያውቀውን እንዳይመሰክር ሊያደርጉ የሚችሉና እውነት እንዳይወጣ ሊያደርጉ የሚችሉ በመሆናቸው መከልከላቸው የተገባ ነው። የቀሪ ጥያቄዎች አጠያየቅ ከሞላ ጎደል በነበረው ሕግ አይነት ነው።

በጉዳዩ ላይ የሚቀርቡ ምስክሮች በመሰረቱ በተከራካሪ ወገኖች የተቆጠሩ ቢሆንም ጉዳዩን የሚመለከተው ፍርድ ቤት ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት ያግዛል ብሎ ካመነ የፍርድ ቤት ምስክርን ጠርቶ ሊሰማና ቃሉን ሊመዝን ይቻላል። ለዚሕ አይነት ምስክር ጥያቄ የሚቀርበው በራሱ በፍርድ ቤቱ ብቻ ቢሆንም ተከራካሪ ወገኖች ይጠየቁልን የሚሏቸው ጥያቄዎች ካሉ ፍርድ ቤት ሲያምንባቸው በፍርድ ቤቱ አማካኝነት ሊጠየቁ ይችለሉ። የሚቀረበውን የጥያቄ አይነትም ፍርድ ቤቱ በሚመቸው አግባብ ሊያቀርበው ይችላል።

ለፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችለው ሌላው የማስረጃ አይነት የሰነድ ማስረጃ ነው። ሰነድ ማንኛውንም መረጃ የያዘና በመሳሪያ ሊነበብ የሚችል እንደሆነ ሕጉ ሰፋ ያለ ትርጉም ይሰጠዋል። በዚህ መሰረት ለተለያዩ አላማ የሚደራጁ መዝገባች፣ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች፣ ፅሁፍን ድምጸን ምስልን ወይም ሌላ መረጃን የሚይዙ ሁል ሰነድ ናቸው። ተመራጩ ሚሆነው የማሰረጃው ደንብ ዋናውን ሰነድ በማቅረብ ማስረዳት ነው። ይሁን እንጂ ዋናው ሰነድ የጠፋ፣ የተቀደደ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሊቀርብ ያልቻለ እንደሆነ በዋናው ሰነድ ምትክ በቅጂው ማስረዳት ይቻላል። በሰነድ ማስረጃ ጉዳይ ላይ አንዱ አሰቸጋሪ ነገር የሰነዱን ትክክለኛነት ማስረዳት በመሆኑ ሕጉ የሰነዶች ትክክለኛነት ሊረጋገጥ የሚችልባቸውን መንገዶችንም አመልክቷል። ከሰነድ ማስረጃ ውሰጥ የኤሌክትሮኒክስ ማስረጃ የራሱ የተለየ ባህሪ እንዳለው ይታወቃል። በዚህ ጉዳይ ላይም በሌሎች አካላት የሚወጡ ሌሎች እሌክትሮኒክስ ነክ ሕጎችም መኖራቸው ይታወቃል። ስለሆነም ለተለያየ አላማ የሚወጡ እነዚህን ሁሉ ሕጎች በስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ውስጥ አንድ ላይ አካቶ ማውጣት የማይቻል በመሆኑ በሌሎች ህጎች የተመላከቱት ደንቦች እንዳግባቡ ለዚሕ ሕግም ተፈፃሚ እንደሚሆኑ ማመላከቱ ተገቢ በመሆኑ በዚህ አግባብ ተመላክቷል።

ሌላው የማስረጃ አይነት ለፍርድ ቤት እይታ ቀርቦ የሚታየው ማስረጃ ወይም ኤግዚቢት በመባል የሚታወቀው ማስረጃ ነው። ከነበረው ህግ በተለየ መልኩ ኤግዚቢትን በፖሊስ ሊጠበቅና ሊተዳደር የሚገባው ለመሆኑ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ድንጋጌ ሕጉ ይዟል። ኤግዚቢት ማናቸውንም አይነት ለፍርድ ቤት ቀርቦ ሊታይ የሚችል ቁስን እንደሚያካትት ትርጉም ተሰጥቶታል። በማናቸውም ደረጃ

ኤግዚቢት የሚቆየው መርማሪ ጋር እንደሆነና ኤግዚቢቱ የሚወድም፣ የሚወረስ ወዘተ ባለመሆኑ የተነሳ ለባለቤቱ መመለስ ያለበት ከሆነ በአቃቤ ሕግ ውሳኔ (በፍርድ ሂደት ላይ በፍርደ ቤት ውሳኔ) ለባለቤቱ ሊመለስ እንደሚችል፤ ባለቤቱን መለየት ካልተቻለ ግን በፍትሐብሔር ደንቦች መሰረት በዐቃቤ ሕግ አማካኝነት ክስ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል። ክሱ የሚቀርበውም የኤግዚቢቱ ባለቤት በፍርድ ቤት አማካኝነት ተለይቶ እንዲወሰንና በፍርድ ቤት በሚወሰነው መሰረት ለባለቤቱ ሊመለስ እንደሚችል ህጉ ደንግጓል። ኤግዚቤትግዙፍ በመሆኑ ወይም በማናቸውም ምክንያት ፍርድ ቤት ለማቅረብ የማይመች በሚሆንበት ጊዜም ናሙናው ተወስዶ ሊቀርብ እንደሚችል ተደንግጓል።

የአቃቤ ህግ ማንኛውም ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ፍርድ ቤቱ አቃቤ ሕግ ክሱን አስረድቷል ብሎ ካመነ ተከሳሽ መከላከያ ማስረጃውን እንዲያቀርብ በውሳኔ ያሳውቀዋል። በዚህ ደረጃ አቃቤ ሕግ ክሱን አስረድቷል የሚባለው ባቀረባቸው ማስረጃዎች ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ለፍርድ ቤት ማስረዳቱን ፍርድ ቤቱ ያመነ እንደሆነ ነው።

ተከሳሽ የሚያቀርበው የመከላከያ ማስረጃ ከላይ እንደተመለከቱት አይነቶች ቢሆኑም ተከሳሹ ክሱን ተከላክሏል ለመባል እና በነጻ ለመሰናት ያቀረበው ማስረጃ የማስረዳት ደረጃው የአቃቤ ሕግማስረጃ ከ "ምክንያታዊ ጥርጣሬ" ደረጃ በታች መሆኑን የሚሳይ መሆን ይኖርበታል። ስለሆነም የተከሳሽ ማስረዳት ደረጃ በአቃቤ ሕግ ማስረጃ ላይ በቂ ጥርጣሬ መፍጠር እንጂ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ደረጃ ማቅረብ አይደለም። ይህንንም ተከሳሹ በመከላከይ ንግግሩ የሚያመላክት ሲሆን ዝርዝሩና አቀራረቡ ግን በክስ መክፈቻ አይነት ነው።

ማስረጃ በወቅቱ ሳይገለፅ ቆይቶ ከፍርድ በፊት በማናቸውም ጊዜ በድንገት በማናቸውም ወገን ሊታወቅ ይችላል። እንዲሁም በክርክር ሂደት በተጨማሪ ሊሰማ የሚገባው ማስረጃ መኖሩ ሊረጋገጥ ይችላል። በሌላ በኩልም ዋናው ማስረጃ በተለያየ መልኩ (ለምሳሌ ምስክር በመሞቱ፣ ኋላ በተከሰተ አእምሮ ጉድለት የተነሳ፣ በማናቸውም ምክንያት ምስክሩን በአካል ለማገኘት ወይም ለማቅረብ ባለመቻሉ ወዘተ) ጉዳዩን በዋናው ማስረጃ ማስረዳት የማይቻልበት ሁኔታ ያጋጥማል። አነዚህ ሁኔታዎች በተግባር የሚያጋጥሙ ቢሆንም ጉዳዩን በግልፅ የሚፈታ ሕግ የለም። በመሆኑም የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ የዚህ አይነት ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ተጨማሪና በድንገተኛ ማስረጃን ፍርድ ቤት ሊቀበል እንደሚችል የሚደነግግ ሲሆን በሌላ ፍርደ ቤት የተሰጠ የምስክርነት ቃልንም ሊቀበል እንደሚችል ይደነግጋል። በፍርድ

ቤት የሚሰጥ ቃልም በፖሊስ ከተሰጠ ቃል ጋር የሚጣረስ እንደሆነ በፖሊስ የተሰጠን ቃል ፍርድ ቤቱ የምስክሩን ቃል ለማስተባበል ሲባል ሊመለከተው ይችላል፡፡ ከዚህ ቀደም በዚህ ጉዳይ ይነሳ ለነበረው ክርክርም ሕጉ ግልፅ መልስ ይሰጣል ማለት ነው፡፡

## 14.ፍርድና ቅጣት

የማስረጃ መስማት ሒደት እንደተጠናቀቀ ፍርድ ቤቱ አቃቤ ሕግም ሆነ ተከሳሹ ስለጉዳዩ የሚያቀርቡት ክርክር ማቆሚያ ንግግር ካለ እንደአግባቡ በቃል ወይም በጽሁፍ እንዲያቀርቡ እድሉን በመስጠት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ፍርድ በመሰረቱ በተቀጠረበት እለት የሚሰጥ እንጂ ተለዋጭ ቀጠሮ የሚሰጥበት አይደለም፡፡ የክርክር ማቆሚያ ንግግር የሚቀርብበትን እድል ለማሰፋትና እንደጉዳዩ ሁኔታ አመቺውን መንገድ ለመምረጥም ለፍርድ ቤት ከቀደመው ሕግ ሰፋ ያለ ስልጣን ሕጉ ይሰጣል፡፡ በዚህ መሰረት ሁለቱም ወገኖች ስለጉዳዩ፣ ስለሕጉና እና ሊፈረድ ይገባዋል ስለሚሉት ጉዳይ በፅሁፍ ወይም በቃል በሚመቻቸው መንገድ የክርክር ማቆሚያቸውን እንዲያቀርቡ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡ ቀጥሎም ፍርድ ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡

ፍርድ የሕዝብ ስራ በመሆኑ ምንጊዜም **በሕዝብ/በመንግሰት ስም የሚሰጥ ነው፡፡** ይህም በፍርዱ ጸሁፍ ውስጥ ይመለከታል፡፡ ከዚህ ቀደም በፍርድ ውስጥ ይታዩ የነበሩ ሰፊ ክፍተቶችን ለመቅረፍ እንዲቻልም ስለ ፍርድ አፃፃፍ ሕጉ ዝርዝር ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡ በዚህ መሰረት እያንዳንዱ ፍርድ በአምስት የተከፈሉ አስራ ስድስት የሚሆኑ ነጥቦችን ባካተተ መልኩ መፃፍ እንዳለበት ሕጉ በግልፅ በአስገዳጅት ደንግጓል፡፡ ዝርዘሩን በሕጉ ውስጥ ማካተት ያስፈለገበት አንዱ ምክንያት የዳኝነት ሥራ በግልፅ ተከናውኗል ሊባል ከሚችልባቸው መመዘኛዎች ውስጥ አንዱ በምክንያት የተተነተነ ግልፅ ፍርድ ሲፃፍ በመሆኑ ነው፡፡ ዝርዝሮቹም ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በበቂ ሁኔታ የመረመረው ለመሆኑና ፍርዱን በማናቸውም ጊዜና ቦታ የሚመለከት ሰው አሳማኝ ፍርድ የተሰጠ መሆኑን እንዲረዳና እንዲያምን ያደርጋሉ ተበለውም ይታሰባሉ፡፡ ማንኛውም ማስረጃ እንዳግባቡ በፍርድ ውስጥ የሚጠቀስ ሲሆን ምስል ወይም ሌላ ወደ ፅሁፍ በቀጥታ የማይለወጡ ማስረጃዎችም በፍርድ ውስጥ ሊጠቀሱ የሚችሉበትን መንገድ (ለምሳሌ በማጣቀሻ) የፍርድ አፃፃፍ ደንቡ ያስረዳል፡፡

ፍርድ በመሰረቱ በመርህ ደረጃ እንደተሰጠ የሚፈፀም ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተሰጠ ፍርድ አፈፃፀም በተከሳሽ ላይ ወይም በፍትሕ ስርአቱ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ ጉዳዩ በይግባኝ ሰሚ

ፍርድ ቤት እስከሚታይ **ድረስ በፈረደው ፍርድ ቤት አማካኝነት** አፈፃፀሙ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ሊታገድ እንደሚችል ሕጉ ተጨማሪ ድንጋጌን ይዟል፡፡

በፍርድ መሰረት ተከሳሽ ነፃ ከተሰኘ ከእስር የሚለቀቅ ሆኖ (ታስሮ ከነበረ) በንብረቶቹ ላይም የተሰጡ ትእዛዞች ካሉ ፍርድ ቤት ተለዋጭ ትእዛዝ ይሰጥባቸዋል፡፡ በሌላ በኩልም ተከሳሹ ጥፋተኛ ከተባለ በሕጉ መሰረት ቅጣት ሊጣልበት ስለሚችል አቃቤ ሕግም ሆነ ጥፋተኛው ሊጣል ይገባዋል ስለሚባለው ቅጣት አስተያየታቸውን ያቀርባሉ፡፡ የሚቀርበውም ቅጣት በድፍኑ ሳይሆን የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎች ከቅጣት አወሳሰን ሕጎች ጋር በማገናዘብ ሊጣል የሚገባውን ቁርጥ ያለውን ቅጣት ነው፡፡ የቅጣት አስተያየትን በተመለከተ አቃቤ ህግ የክስ መክፈቻ ንግግር ሲያደርግ እንዲሁም ተከሳሽ የመከላከያ መክፈቻ ንግግር ሲያደርግ ጥፋተኛ ቢባል ሊጣል ይገባዋል ስለሚሉት ቅጣት አስተያየታቸውን ቀድመው የሚያቀርቡበትን እድል ከሌለ የጥፋተኛነትን ውሳኔ ተከትሎ በስተመጨረሻ ላይ የሚያቀርቡት ይሆናል፡፡

በተለየ ሁኔታ የቅጣት አስተያየት ቀድሞ እንዳይቀርብ ዳኛው ሊያዝ የሚችልበት እድል ግን ዝግ አይደለም፡፡ ዳኞች በትክክለኛው ትርጉሙ በሕግ የሰለጠኑ ባለሙያዎች ናቸው የሚለው ግምት ቀድሞ በሚቀርብ የቅጣት አስተያየት የተነሳ ወደ አንደኛው ወገን እንዲወግኑ እምብዛባም አያደርጋቸውም የሚል እምነት አለ፡፡ በአጠቃላይም በአገራችን የፍትሕ ስርአት ዳኞች በፍሬ ነገርም ሆነ በሕጉ ጉዳይ ላይ ውሰኔ የሚሰጡ ሲሆን ከጁሪ ስርአት በተለየ መልኩ በሕግ የተማሩ ባለሙያዎች ስለሆኑ የሚቀርቡ ክርክሮች ከሙያ ደረጃው በታችና ከሙያው ስነምግባር ውጪ አድሎአዊ አመለካከት ቀድመው እንዲይዙ አያደርገቸውም ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም በክስ መክፈቻ ንግግር ውስጥ ተካቶ የሚቀርብን የቅጣት አስተያየት ሊቀበሉ የሚችሉበት አጋጣሚ ሙሉ በሙሉ ዝግ አይደለም ማለት ነው፡፡ ይህ መሆኑ አቃቤ ሕግም ሆነ ተከሳሽ ስለክርክሩ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ያለውን ሀቅ በሚገባ እና በተሟላ ሁኔታ ተረድተውት እንዲከራከሩም ደርጋቸዋል፡፡ ያምሆኖ ዳኛው በዚህ መልኩ የቅጣት አስተያየት መቅረቡ በጉዳዩ ላይ ገለልተኛ ውሳኔ ለመስጠት አያስችለኝም ብሎ ካመነ የቅጣት አስተያየት ተከሳሹ ጥፋተኛ የተባለ እንደሆነ ብቻ እንዲቀርብ መደረጉ ይቀጥላል፡፡

## 14.1 የቅጣት ውሳኔ

አቃቤ ሕግ እና ተከሳሹ ያቀረቡትን የቅጣት አስተያየት ከሕጉ ጋር በማገናዘብ ፍርድ ቤቱ ቅጣትን ይወስናል፡፡ ቅጣት በዋነኛነት የሚወሰነው በወንጀል ሕጉ መሰረት ነው፡፡ የቅጣት አይነተቶቹም (የሞት፣

እስራት፣ የገንዘብ፣...) የሚወሰኑት በወንጀል ሕጉ መሰረት ነው። የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ የያዛቸው ድንጋጌዎች በዋነኛነት የቅጣት አላማን ለማሳክት እንዲቻል ቅጣት ሲወሰን ዳኛ ሊከተላቸው የሚገቡ መርሆዎችንና የእያንዳንዱን ቅጣት አወሳሰን ሥርአቶች እንደሚከተለው ጠቅለል ብለው ተመልክተዋል። ቅጣት ከተወሰነ በኋላ በሕጉ መሰረት ስለ መፈጸሙ የመከታተል እና የማረጋጥ ኃላሲነት የአቃቤ ሕግ ነው።

የሞት ቅጣት አፈፃፀምን በተመለከተ ውሳኔው ተፈፅሞ በፍፁም የማይተካው የሰው ሕይወት ከማለፉ በፊት የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ ስለአፈፃፀሙ ከፍተኛ ጥንቃቄቆችን ያደርጋል። በዚህ መሰረትም ማንኛውም የሞት ፍርድ የፈረደ ፍርድ ቤት በፍርዱ ላይ ይግባኝ የተባለበት ቢሆንም ወይም ባይሆንም የፍርዱን ግልባጭ እንዳግባቡ ለክልል ወይም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መላክ እንዳለበት ሕጉ በአስገዳጅነት ደንግጓል። ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ትክክለኛ ፍርድ የተሰጠ መሆኑን አረጋግጦ ለጠቅላይ አቃቤ ሕጉ ይልከዋል። በፍርዱ ላይ ይግባኝ የተባለበት እንደሆነም የፍርዱ ትክክለኛነት የፍርደኛውን ቅሬታ ጭምር አካቶ ይመረመራል። በማናቸውም ሁኔታ የሞት ፍርድ ጉዳይ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ የሚታየው አምስት ዳኛች በተሰየሙበት ችሎት ነው። ጠቅላይ አቃቤ ሕጉም ፍርድ በይግባኛ፣ በምህረት ወይም በማናቸውም ሌላ ሕጋዊ ምክንያት ያለተለወጠ መሆኑን በማረጋገጥ ለአገሪቷ ርእሰ ብሔር ይልከዋል። የሞት ፍርዱ በርእሰ ብሔሩ ከፀደቀ ለአፈፃጸም ለማረሚያ ቤቱ የሚላክ ሲሆን በወንጀል ሕጉና የጠቅላይ አቃቤ ሕጉ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የፍርደኛውን ክብር ጠብቆ በማረሚያ ቤቱ ውስጥ ይፈፀማል።

የሞት ፍርድ አፈፃጸምን ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት በአቃቤ ህግ አመልካችነት የሚከታተለው ሲሆን የሞት ፍርድ ሳይፈፀም ለረዥም ጊዜ መቆየቱ በራሱ በፍርደኛው ላይ የስቃይ አያያዝን የሚያስከትል በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ፍርዱ ሳይፈፀም ሁለት አመት ያለፈው እንደሆነ ወደ እድሜ ልክ እስራት እንዲቀየር ሕጉ ይደነግጋል።

ነፃነትን የሚያሳጣ ቅጣትን በተመለከተ ቅጣቱ እንደተፈረደ ወዲያውኑ መፈጸም ስለሚኖርበት ስለቅጣቱ አፈፃፀም ግልፅ ትእዛዝ ጭምር በመስጠት ፍርደ ቤቱ ለማረሚያ ቤት ትእዛዝ ያስተላልፋል። ቅጣቱ እንደተወሰነ ወዲያውኑ መፈፀም ያለበት ቢሆንም በተወሰኑ ምክንያቾች ግን የእስራ ቅጣት አፈፃፀም ለተወሰነ ጊዜ ሊተላለፍ ይችላል። ነባሩ ስነ ስርአትና ማስረጃሕግ እጅግ በጠበበ ሁኔታ ይፈቅድ የነበረውን የእስራት ቅጣት ማስተላለፍ ጉዳይ የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ ሰፋ በማድረግ ሰዎች በመታሰራቸው

ምክንታያት የእድሜ ልክ ቅጣት/ችግር በሕይወታቸው ላይ እንዳይገጥማቸው ጥንቃቄ ያደርጋል። በዚህ መሰረትም በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ቅጣት እንደተወሰነ ሳይፈፀም ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ተላልፎ እንዲቆይ ሕጉ ታሳቢ ያደርጋል። የቅጣት ውሳኔ አፈፃፀምንበፍርደኛው የግል ሁኔታ ላይ ተመርኩዞ ለተወሰነ ጊዜ ማሰተላለፉ በስራው፣ በቤተሰብ ሕይወቱ፣ በምርቱና በምርታማነቱ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት የሚቀንስ ከመሆኑም በላይ ፍርደኛው ቅጣትን ሲፈፅም በሙሉ እምነት በመታረሙ ላይ ብቻ እንዲያተኩር ያደርገዋል። በዚህ መልኩ የእስራት ቅጣቱን ፈፅሞ ሲወጣም ይበልጥ የታረመና ምርታማ ዜጋ ይሆናል።

የቅጣት ውሳኔ አፈፀፀም ሊተላለፍ የሚችለው ቅጣቱ እስከ አምስት አመት የሚደርስ ቀላል የሆነ እንደሆነ፣ ተቀጪው ለሕብረተሰቡ ደሕንነት አደጋ የማይሆኑ እንደሆነና ለአፈፃፀሙ በቂ ዋስታና የሚጠራ ሲሆን ነው። በዚህ መልኩ ቅጣት የሚተላለፍላቸው ሰዎች ውስጥም አንድ አመት ያልሞላት ልጅ ያላት እናት፣ በጠና የታመመና በዚሕ ምክንያት ቅጣትን መፈጸም የማይችል፣ አጣዳፊ ወይም ወቅታዊ ስራ ያለው ባለሙያ፣የማየተላለፍ ወቅታዊ ስራ ለው አርሶ ወይም አርብቶ አደር እና የመሳሰሉት ይገኙበታል። እንደዚህ አይነት ሰዎች ከፍ ሲል የተመለከተውን መስፈርት አሟላተው እስከተገኙ ድረስ የገጠማቸው ችግር ወይም ያሉበት ሁኔታ እስኪለወጥ ድረስ የቅጣት አፈፃፀሙን ለተወሰነ ጊዜ ማሰተላለፉ ተገቢና አሳማኝ ነው። ቅጣቱ የሚተላለፈውም እንደ ምክንያቶች በቂነት ለእያንዳንዱ ምክንያት በተቀመጠው የጊዜ ጣሪያ ልክ ሲሆን (ለጉዳዩ የሚስፈልገውን ያህል ጊዜ መስጠቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የበዛው እስከ አንድ አመት ነው) ፍርደኛው ቅጣቱ የተላለፈበትን ምክንያት ያላግባብ ስራ ላይ ካዋለው ወይም የተላለፈበት ጊዜ እንዳበቃ የእስራት ቅጣቱን መፈጸም ይጀምራል።

የገንዘብ ቅጣትን በተመለከተ በተመሳሳይ በወንጀል ሕጉ መሰረት የሚፈጸም ቢሆንም የገንዘብ ቅጣት እስካሁን ባለው ሁኔታ በአግባቡ እየተፈጸመ ባመሆኑ ቅጣቱ ሳይፈፀም እንዳይቀር ሕጉ ጥንቃቄዎችን አድርጓል። በመሆኑም ገንዘብ ቅጣት ወዲያውኑ ገቢ መሆን ያለበት ከመሆኑ አንስቶ ፍርደኛው በህግ አግባብ ተገዶ የቅጣት ገንዘቡን ገቢ የሚያደርግበትን ስርአት ተቀምጧል። በዚህ መሰረትም የገንዘብ ቅጣት በፍርደኛው ፈቃደኛነት ለመንግሰት ገቢ ካለሆነ ወይም በቀጥታ ገቢ እንዲሆን የሚታዘዝበት ገንዘብ በፍትሕ አካላት ያልታወቀ (ለምሳሌ ለዋስትና የተያዘ ገንዘብ አለመኖሩ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ) እንደሆነ በዋነኛት የመንግስትን ገንዘብ የመሰብሰብ ሃላፊነት ያለበት የመንግስት ተቋም (የገንዘብ ሚኒስቴር ወይም የገንዘብ ቢሮ) ማንኛውንም የፍርደኛውን ገንዘብ ወይም ንብረት በማፈላለግ በፍትሐብሔር ፍርድ

አፈጻጸም አግባብ የቅጣት ገንዘቡ ገቢ እንዲሆን ወይም ንብረቱ ተሸጦ የቅጣት ገንዘቡን ገቢ እንዲሆን የማድረግ ሃላፊነት እንዳለበት ሕጉ ግልጽ ያደርጋል፡፡ ይህ ስርአት ከዚህ በፊት በአፈጻጸም ይታይ የነበረውን የባለቤትነት ችግርና የአፈጻጸም ክፍተት ይቀርፋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ገንዘብ ተፈልጎ ወይም ንብረት ተሸጦ ገቢ በሚሆንበት ጊዜ የተለያዩ ሰዎች በፍርደኛው ላይ የገንዘብ መብት አለን የሚል ክርክር የሚያቀርቡበት አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡ ገንዘቡ የሁሉንም ፍላጎት ሊያሟላ ካልቻለ የመብት ቅደም ተከተል ማሰቀመጡ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የወንጀሉ ጉዳይ በወንጀል ተጎጂው የመጀመሪያ ጉዳት የጀመረ በመሆኑ ለወንጀል ተጎጂ የተፈረደ የካሳ/የጉዳት ገንዘብ ካለ ከክርክሩ ወጪ ቀጥሎ ነገር ግን ከሁሉ እዳዎች ቀድሞ ይከፈላል፡፡ **የመንግስት እዳዎች ቀጥለው የሚከፈሉ ሲሆን ሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎችን በተመለከተ በሌሎች ሕጎች በተደነገጉት አግባቦች እልባት** ያገኛሉ፡፡

ፍርድ ቤቱ ከላይ ከተመለከቱት ቅጣቶች በተጨማሪ ተጨማሪ ቅጣቶች በፍርደኛው ላይ እንዲፈፀሙ ትእዛዝ ሊሰጥ ይቻላል፡፡ ተጨማሪ ቅጣቶች ንብረት መውረስን፣ተግሳፅ መስጠትን፣ ይቅርታ መጠየቅ ወይም ማውረድን፣ ማስጠንቀቂያን መስጠትን ወዘተ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ቅጣቶቹም ሳይፈጸሙ እንዳይቀሩ ፍርድ ቤት ቅጣቶቹ ሊፈጸሙ የሚችሉበትን ግልጽ አቅጣጫ ማስቀመጥና ግልጽ ትእዛዝ መስጠት እንዳለበት ሕጉ በአስገዳጅነት ደንግጓል፡፡ የተወሰኑ ቅጣቶችም (ለምሳሌ በፍርድ ቤት ሊሰጥ የሚችል ማስጠንቀቂያ) ወዲያውኑ በፍርድ ቤት ተሰጥተውና ተፈጽመው ሊቋጩ ይችላሉ፡፡ የተወሰኑት ተጨማሪ ቅጣቶች መደበኛውንና መደበኛ ያልሆነውን ስርአት በማዋሃድ ሊተገበሩ የሚገባቸው የሚሆንበት አጋጣሚም ይኖራል፡፡ ለምሳሌ ይቅርታ መጠየቅ ባህላዊ ስርአትን ባካተተ መልኩ የመፈፀም እድሉ ከፍተኛ በመሆኑ የፍትህ አካላት ስለዚህም ጉዳይ ያላቸው ግንዛቤ ሊዳብር ይገባዋል፡፡ በሌላ በኩል እንደ ከመብት መሻር፣ ከደረጃ ዝቅ ማድረግና ከሰራዊት አባልነት መሰናበት የመሳሰሉትን ተጨማሪ ቅጣቶች እንደ ሁኔታው ከፍትህ አካላት ውጪ ባሉ ተቋማት (ለምሳሌ በምርጫ ቦርድ፣ በመንግስት መስሪያቤት ወይም በመከላከያ ሚኒስቴር አማካኝነት) የሚፈፀሙ ይሆናሉ፡፡ የተወሰኑ ተጨማሪ ቅጣቶች (ምሳሌ ንብረት መውረስ) የሶስተኛ ወገን (ለምሳሌ የትዳር ጓደኛን) መብትን ሊነኩ የሚችሉ በመሆናቸው መብት አለን የሚሉ ወገኖች የመብት ጥያቄ አቅርበው ፍትሕ ሊያገኙ የሚችሉበትንም እድል ሕጉ ይፈቅዳል፡፡

የገንዘብ ቅጣት ተከታትሎ በገንዘብ ወይም በንብረት ላይ ማስፈፀም እንዲሁም የንብረት ይወረስ ውሳኔን ተከታትሎ ማስፈፀም ክትትል እና ትጋትን ይፈልጋል፡፡ በሕጉ ሊወረስ የሚችል ንብረት በክርክር ወቅት ተለይቶ ቢያንስ ሊታገድ የሚችል ነው፡፡ ንብረቱ ያላግባብ ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት ሊቀመጥ የማይገባው ከመሆኑም በላይ የሰዎች ተጨማሪ ንብረት የማፍራት መብታቸውም በፍትሕ አካላት ትጋት ማነስ የተነሳ ሊገደብ አይገባውም፡፡ የነፃ ኢኮኖሚ ስርአትም ሰዎች በንብረታቸው ተረጋግተው የሚጠቀሙበት እድል እንዲሰፋ ይጠብቃል፡፡ ስለሆነም ሕ ንብረት የሚወረስ እንደሆነ “ወዲውኑ” እንዲፈጸም የሚደርግ ድንጋዎችን ነው ያካተተው፡፡

በሕጉ ውስጥ ሌላው የተካተተው የቅጣት አይነት አማራጭ ቅጣትን የሚመለከተው ነው፡፡ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ መሰረታዊ አቅጣጫ ጉዳዮች በፍርድ ሂደት ከሚያልፉ ይልቅ ከፍርድ በፊት ተጠርጣሪዎች ያጠፉ ከሆነ ጥፋታቸውን የሚያምኑበትንና ለዚህም የሚበረታቱበትን ስርአት መዘርጋት ነው፡፡ ስለሆነም አማራጭ መንገዶችና አማራጭ መፍትሔዎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡ የአማራጭ መፍትሔ እርምጃ ትኩረት ጥፋተኛው ለጥፋቱ በመፀፀት ኃላፊነት እንዲወስድ ማድረግ፣ ማሰታረቅና ካሳ ማስከፈልን ሊመለከት ይችላል፡፡ መፍትሔው በዘፈቀደ የሚወሰድ ሳይሆን የሕዝብ ጥቅምን በዚህ መንገድ በተሻለ መልኩ ማረጋገጥ እንደሚቻል ሲታመንበት የሚወሰን ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተውም ተከሳሽ ምንግዜም የጠበቃ እርዳት ማግኘት ያለበት መሆኑ በግራ ቀኙ መካከል በእኩል ደረጃ የመሰማት መብትን ለማረጋገጥ ያግዛል፡፡

አማራጭ ቅጣት ቀላል ወንጀል የፈጸሙ ሰዎችን (በተለይ ወጣት ጥፋተኞች፣ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ በሴቶች ላይ እና ደጋጋሚ ባልሆኑ ተጠርጣሪዎች) በእስር ከማረም ይልቅ የማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ፣ ለተበዳዩ ካሳ በመክፈል ወይም ይቅርታ በመጠየቅ፣ ወይም የአእምሮ ህክምና እንዲያገኙ በማድረግ ወደ ጤናማ ዜጋነት ለመመለስ የሚረዳ ሥርዐት ነው፡፡ አማራጭ ቅጣቶች የእስረኛን ቁጥር ለመቀነስ፣ የምርመራን ወይም የፍርድ ሂደትን ለማቀላጠፍ ጠቃሚ ናቸው፡፡ ይህ ቅጣት በፍርድ ቤት አነሳሽነት ወይም በፍርደኛው ጥያቄ (በተፈጥሮ ሰው ላይ ብቻ) ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ነው፡፡

አማራጭ ቅጣትም የጉልበት ስራንም ይመለከታል፡፡ የጉልበት ስራ ጉዳይ ራሱን በቻለ የተለየ አዋጅ ጭምር የሚመራ ቢሆንም የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በቀላል እስራት ወይም በገንዘብ እስራት የተቀጣና ስራ መስራት የሚችል ሰው ከሚታሰር በጉልበት የስራ ቅጣት ማህበረሰቡን ቢያገለግልል ለፍርደኛውም ሆነ

ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ ጠቃሚ ከመሆኑም በላይ ቅጣትን ይበልጥ ውጤታማ በሆነ የተሃድሶ እና የትምህርት መስመር ማጠናቀቅ የሚስችል ለመሆኑ ሕጉ ታሳቢ ያደርጋል፡፡ የዚህ ቅጣት አፈፀፀም ላይ አገራት ሰፊ ተሞክሮ ያላቸው በመሆኑ ቢተገበርም አገራችን ካላት ሰፊ የስራ እድል አንፃር ታራሚዎች ከስራ እንዳይነጠሉ እንዲሁም የተወሰነ ገቢ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡ በዚህ መልኩ ሊሰሩ ከሚችሉት ስራዎች ውስጥ የመንገድ ጽዳት ማከናወን፣ የመዝናኛ ቦታዎችን ማጽዳት፣ በተለያዩ የመንግስትም ሆነ የህብረተሰብ ግንባታዎች ጥገናዎች ላይ የተለያዩ ስራዎችን መስራት (ለምሳሌ ቀለም መቀበት)፣ ህጻናት በሚማሩበት ወይም በሚቆዩበት አካባቢ የጥበቃ አገልግሎት መስጠት፣ አንዳንድ ጊዜ የሚፈጠሩ ድንገተኛ አደጋዎችን (ለምሳሌ የእሳት አደጋን) ለመከላከል ተመድቦ መስራትና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎችን በመርዳትም ስራ ላይ እንዲሰማሩ ሊደረግም ይችላል፡፡

ታሳሪዎች በመሰረቱ መስራት የሚችሉበት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ከመሆናቸው አንፃር ከማህበረሰቡ ሳይነጠሉ በዚህ መልኩ በጉልበት ስራ የሚቀጡ ከሆነ መልሰው ከሕብረተሰቡ ጋር ለመቀላቀል ሳይቸገሩ አጅግ በጣም ውጤታማ የተሃድሶ ስራ ሊሰራበት የሚችል በመሆኑ በሕጉ ውስጥ በግልፅና ዘርዘር ብሎ እንዲካተት ሆኗል፡፡ ይህ ቅጣት እንዳግባቡ በሥነልቦና፣ በማህበራዊ ሳይንስ እና ልዩ እውቀት ባለው ልዩ ባለሙያ ክትትል የሚፈፀም ሲሆን ከፍርደኛው ሁኔታና ከእርምት አላማ ጋር እየተገናዘበ እንደ ባለሙያው የሙያ አስተያየት በየጊዜው የሚለዋወጥ ወይም የሚሻሻል ይሆናልም፡፡

ከቅጣት አፈፃፀም ጋር ተያይዞ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ትኩረት የሰጠበት ሌላው ጉዳይ ቅጣቶችን የሚያስፈፅመውን አካል የተመለከተው ነው፡፡ በወንጀል ህጉም ሆነ በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ላይ በዝርዝር እንደተመለከቱት ከቅጣት አይነቶች ውስጥ በሞት እና በእስራት ከሚያስቀጡት ውጪ ያሉ ቅጣቶች በርካታ ከመሆናቸውም በላይ ፍርደኛ በሌላ አግባብ (በገንዘብ፣ በጉልበት፣ በተጨማሪ ቅጣቶች...) የሚቀጣባቸው የወንጀል አይነቶችም በርካታ ናቸው፡፡ እጅግ ከባድ ከሆኑት ወንጀሎች በቀርም ሌሎች ወንጀሎች በተሻለ ሁኔታ ፍርደኛን ሊያርሙ የሚችሉት ከእስራት ውጪ በሌሎች ቅጣቶች እንደሆነም በርካት ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡ በሌላ በኩልም እስራት ቅጣት ውጤታማ ሊሆን የሚችለው በእስራት ጊዜ ሊኖሩ የሚገባቸው በአለም አቀፍ አነስተኛ የእስረኞች አያያዝ ደንብም ሆነ በሕገ መንግስቱ በተመለከቱት ውጤታማ የእርምት እርምጃዎች (እንደ ትምሕርት፣ ስልጠና፣ ጤና፣ ስፖርት፣ አመጋገብ፣ የውጪ ግንኙነቶች እና የመሳሰሉት ያሉት) ውጤታማ በሆነው አግባባ መፈጸማቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ቅጣት በፍርድ ቤት በሚወሰንበት ጊዜም ሆነ ፍርደኛው ፍርዱን ጨርሶ ወደ ሕብረተሰቡ በሚቀላቀልበት ጊዜ

ውጤታማ ተያያዥና ተከታታይ ተግባራት ሲከናወኑ ነው። እስረኛን በማረም ሂደት ውስጥ ጥሩ ተሞክሮዎች እንዳሉም ሁሉ በርካታ ችግሮችም እንዳሉ የተለያዩ ጥናቶች (ለምሳሌ በ2003 የወጣው የኢተዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ሪፖርትን ጨምሮ) ያረጋግጣሉ። በሌላ በኩል ፍርድ ቤቶች የቅጣት ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በአቃቤ ሕግና በፍርድኛው የቅጣት አስተያየት ላይ ተሞርኩዘው ውሳኔ ከመስጠታቸው በቀር በባለሙያ አስተያየት እገዛ አይደረግላቸውም። እስረኛ እስራን ጨርሶም ይሁን በሌላ አግባብ ወደ ማህበረሰቡ በሚቀላቀልበት ጊዜም ይህንን የሚከታተልና የሚያስፈፅም አካል የለም። በተለያየ ምክንያትም ፍርደኛ ለጊዜው ቅጣት ሲገደብለት (በአመክሮ፣ በእግድ፣ በእስራ ቅጣት ማስተላለፍ...) ይህንን የሚከታተል አካል የሌለ በመሆኑ ለጌዜው መለቀቅ ማለት በውጤቱ የመጨረሻ መለቀቅ ያህል ሀኗል። እስራቱን ጨርሶ ወደ ማህበረሰቡ የሚቀላቀልንም ሰው በስርአቱ ይዞ በአግባቡ የሚቀላቅል ስርአትም የለም። እነዚህ ሁሉ ተግባራት በውጤታማነት ቢከናወኑ የአገራችን የእርምት ስርአት ይበልጥ ውጤታማ ይሆናል፤ በመሆኑም ደጋጋሚነትም ይቀንሳል ተብሎ ይታሰባል። ይህንንም በውጤታማት ለማከናወን የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ ከእስራትና ከሞት ቅጣት ውጪ ያሉትን እና ከላይ የተመለከቱትን ተጨማሪ ኃላፊነቶች እንዲያከናውን ሃላፊት የሚሰጠው ራሱን የቻለ አንድ የመንግስት ተቋም እንዲቋቋም የሚያሰችል ድንጋጌ አካቷል።

## 15. ፍርድ እንደገና የሚታይባቸው አግባቦች

ፍርድ ምንጊዜም እንከን አልባ የሆነ ፍፁም የዳኛ ተግባር ነው ተብሎ የማይወሰድ በመሆኑ ፍርዱን በሰጠውም ፍርድ ቤትም ይሁን በበላይ ፍርድ ቤት ስሕተቶቹ ሊታረሙ የሚችሉበትን እድል ክፍት ማድረግ ተገቢ ነው። በመሆኑም አንድ ፍርድ ጉዳዩን በቀጥታ የተመለከተው ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ስህተት አለበት ቢባል ፍርዱ በድጋሚ ታይቶ ተገቢው ማስተካከያ የሚደረግበትን ስርአት ሕጉ በዝርዝር አካቷል። እነዚህ ስርአቶች በአብዛኛው በነባር ሕግጋትም የተመለከቱ ሲሆን በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ ክፍተቶችን፣ ለውጦችን እንዲሁም የሚስተዋሉ ችግሮችን መፍትታ በሚያስችል አግባብ እንዲካተቱ ሆኗል። እነዚህ ስርአቶችም መሰየምን፣ በሌለበት የተሰጠ ፍርድን እንደገና ማየትን፣ ይገባኝን፣ ስበርን እና ፍርድን እንደገና የማየት ስርአትን የሚመለከቱ ናቸው።

የመሰየም ስርአትን በተመለከተ በመሰረቱ የሚተገበሩት የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ናቸው። በመሰየም ጉዳይ ላይ የወንጀል ሕጉ ከደነገገው እምብዛም የተለየ ድንጋጌ በስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ አልተካተተም።

ፍርድን እንደገና የማየት ጉዳይም ከፍ ሲል የተገለፀ ሲሆን ፍርድ እንደገና ይታይልኝ የሚል ተከሳሽ ወይም ፍርደኛ መጥሪያ ያልደረሰው ወይም መጥሪያ የደረሰው ቢሆንም በበቂ ምክንያት ቀርቦ ለመከራከር ያልቻለ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ በማናቸውም ጊዜ ይህንን ማረጋገጥ ባይችል ግን ክርክሩ በደረሰበት ገብቶ ክርከሩን መቀጠል ወይም ፍርዱን መፈፀም ይጠበቅበታል፡፡

ሌሎች ስርአቶች ጠቅለል ተደርገው እንደሚከተለው ተመልክተዋል፡፡

## 15.1 ይግባኝ

ይገባኝን በተመለከት ከዚህ ቀደም የነበረው የሥነ ሥርአት ህግ ግልፅ የሆነ የይግባኝ አላማን ያላስቀመጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕግ ከነበረው ስርአት በተለየ መልኩ የይግባኝን አላማ የሚያስቀምጥ ሲሆን በዚህ መሰረትም የይግባኝ አላማ በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመን የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ስሕተትን ማረም፣ በአንድ የአስተዳደር ወሰን አካባቢም ተቀራራቢ የሕግ ትርጉም ማስፈን የመሳሰሉና ሌሎች አላማዎች ማሳካት ሆኖ ተቀምጧል፡፡ ይህም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ባላቸው አስተዳደራዊ ክልል ውስጥ በግልፅ የተመለከተውን አላማ ያገናዘበ ስራ እንዲሰሩ ያግዛቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከአቃቤ ሕግ አንፃር ይግባኝ ሊጠየቅ የሚገባው የሕዝብ ጥቅምን የማረጋገጥ አላማን ለማሳካት መሆን እንደሚገባውም ግልፅ ተደርጓል፡፡

አላማው ይግባኝ ሊባልባቸው የማይገቡ ጉዳዮችን የሚያመላክት ቢሆንም ሕጉ በትርጉም ክፍሉ ትዝዛዝ የሚለውን ግልፅ ያደረገ ከመሆኑም በላይ ይግባኝ የማይባልባቸውን የስር ፍርድ ቤት የትእዛዝ እና ሌሎች ጉዳዮች በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ይግባኝ የማይባልባቸው ጉዳዮች እንደ መዝገብን በዘላቂነት የማያዘጋ ትእዛዝ፣ ድርድር፣ በእምነት ላይ ተመስርቶ የተፈፀመ ተግባር እና የመሳሰሉት ሲሆኑ እነዚህ ጉዳዮች አንድም በስር ፍርድ ቤት በተለያየ መልኩ ሊታረሙ የሚችሉ አለዚያም በተከሳሹ ፍቃድ ላይ ተመስርተው የተከናወኑ ተግባራት በመሆናቸው ይግባኝ ማቅረብ የበላይ ፍርድ ቤትን አላስፈላጊ በሆነው አግባብ በስራ ከማጨናነቅ በቀር ለውጥ የሚያመጣ ትርጉም የሌላቸው ናቸው፡፡

የይግባኝ ማመልከቻዎች የተለያዩ ከጉዳዩ ጋር የማይካተቱ ጉዳዮችን ጨምረው እያካተቱ ግልፅ የማይሆኑ፣ የሚያደናግሩ እና ጊዜና ጉልበት ብቻ የሚያባክኑ የሚሆኑባቸው አጋጣሚዎች ቀላል አለመሆናቸው በተግባር የሚታወቅ በመሆኑ የይግባኝ ማመልከቻ መያዝ የሚገባቸውን ጉዳዮች ሕጉ ዘርዝሮ ይዟል፡፡ የይግባኝ ማመልከቻውም ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ዘመናዊ **ቴክኖሎጂ** መጠቀምን ጨምሮ አመቺ

በሆነ አግባብ መቅረብ እንዲችሉ እድሉ በስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ስፍቷል፡፡ ከዚህ ቀደም የነበረው 15 እና የ30 ቀናት ልዩነት የይግባኝ ማቅረቢያው ጊዜ ቢሰፋም የይግባኝ መጠየቅ እድል ያጠበበ ከመሆኑም በላይ ትርጉም ያለው ክፍፍል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ማለት የሚፈልግ ሰው በ60 ቀናት ውስጥ ይግባኝ ማመልከቻ ማቅረብንም ሆነ ይግባኝ ማቅረብን እድል እንዲጠቀምበት ሆኗል፡፡ ይህ ጊዜም መዝገቡን ለመገልበጥ የሚወስደው ጊዜ ግምት ውስጥ ሳይገባ የሚታሰብ ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ማቅረብ ያልቻለ ይግባኝ ባይ በቂ ምክንያት ያለው ከሆነ ጊዜው ያለፈበትን ይግባኝ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ፈቃድ **ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ካሰቀመጠው አላማ አንጻርም በቂ ምክንያት ባይኖር እንኳን በከፍተኛ ደረጃ የሚዛባ ፍትሕ** አለ ከተባለ ጊዜው ያለፈበት ይግባኝ ሊታይ የሚችልበትን እድል ሕጉ ዝግ አላደረገም፡፡ ይግባኝ ማቅረቢያ መንገዱ ሰፋ ያለ እንደመሆኑ መጠን በማናቸውም **ምክንያት ይግባኝ ሳይጠየቅ አንድ አመት ያለፈ እንደሆነ ከወንጀል** ቅጣትና ከሥነ ሥርአቱ አላማ ውጪ ስለሚሆን በይግባኝ እንዲታይ የሚፈቀድ አይሆንም፡፡ በወንጀል ጉዳይ ቅሬታ ያለው አካል ለዚህን ያህል ጊዜ ቅሬታ ያስከተለበትን የወንጀል ፍርድ ተሸክሞ ይቆያል ማለትን አይቻልም፡፡ ጉዳዩ ከተከሳሽ ነጻነት እና ከተጎጂ ፍትሕ የማግኘት መብት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ በመሆኑ ስህተት ያለበትን የወንጀል ፍርድ ለማሳረም ፍርደኛውም ሆነ አቃቤ ሕግ ይህንን ያህል ጊዜ ይግባኝ ሳይጠይቁ ይቆያሉ ማለትም አስቸጋሪ ነው፡፡

የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ስልጣንን በተመለከተም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፈፃፀም ማገድ የሚችል ሲሆን ለዚህ አፈፃፀም የሚረዱ ድንጋጌዎችንም ሕጉ ዘርዝሮ ይዟል፡፡ ይህም ከዚህ በፊት እግድን አስመልክቶ የነበረውን ክፍተት ይሸፍናል ተብሎ ያታሰባል፡፡ ያልተጠየቀ ዳኝነት አይሰጥም በሚለው መርህ መሰረት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከይግባኝ ቅሬታ በላይ የከበደ ውሳኔ ሊሰጥ እንደማይችል ሕጉ ታሳቢ በማድረግ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ስልጣን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን የማፅናት፣ የመለወጥ፣ የማሻሻል እና የመሻር ስልጣን እንደሆነ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ በዚህ ስልጣኑ የራሱን ውሳኔ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የመተካት ወይም ጉዳዩ እንደገና በስር ወይም በሌላ ፍርድ ቤት እንዲታይ የማድረግ ስልጣንም አለው፡፡ ይሁን እንጂ ባለጉዳይን በወንጀል ጉዳይ ማመላለስ ይበልጥ የማይደገፍ በመሆኑ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ በተቻለ መጠን ያለቀለት ስራ ይሰራል የሚል መነሻ ያለ በመሆኑ በተቻለ መጠን ጉዳዩ ወደ ስር ፍርድ ቤት ሳይመለስ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ቢሰጥበት ይመረጣል፡፡ ክርክሩ ከተጠናቀቀ በኋላም ይግባኝ ባይ

ወይም መልስ ሰጭ ሳይቀርቡ ከቀሩ ውሳኔ ሰጥቶ ውሳኔው እንዲፈጸም ትእዛዝ መስጠት እንጂ የግድ አሰፈላጊ ባልሆነው አግባብ እንዲቀርቡ ቀጠሮ ሲቀያየር ወይም መዝገብ ሲዘጋና ሲከፈት መቆየት አይኖረበትም። መዝገብ የግድ የሚቋረጥ ቢሆንም እንኳን ውሳኔ ለሰጥባቸው የሚገቡ (ንብረት እግድ፣ መውረስ፣ ዋስትና ጉዳይ ገነዘብ ገቢ ማድረግ/አለማድረግ...) የመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሳይሰጥባቸው ተንጠልጥለው አየቀሩ ከዘመናት በኋላም ጥያቄ እየተነሳባቸው መዝገብ የሚያነቀሳቅሱ በመሆናቸው መዝገብ በተዘጋ ቁጥር ተገቢው ማጣራ እየተደረገ ውሳኔ ሊሰጥባቸው እንደሚገባ ሕጉ ድንጋጌ ይዟል። በይግባኝ ውሳኔ ሊጠቀሙ የሚችሉ ሌሎች ይግባኝ ያልጠየቁ ፍርደኞች ቢኖሩ ይግባኝ ቢሉ ይጠቀሙ የነበሩ ለመሆናቸው በሚገባ ከተረጋገጠ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊጠቀሙ የሚችሉበትን እድልም አካቷል።

ከይግባኝ ጋር በተያያዘ የመጥሪያ፣ የሬጂስትራር ስልጣን፣ የተዘጋ መዝገብ የሚከፈትበት አግባብ፣ ተጨማሪ ማስረጃ አፈቃቀድ...የመሰሰሉት ጉዳዮች ከቀጥታ ክስ ጋር ተቀራራቢ በሆነ አግባብ የሚፈፀሙ ናቸው።

## 15.2 ሰበር

የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በሕገ መንግሰቱ ለጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የሰጠው የሰበር ስልጣን የሚመራትን ሥነ ሥርአት አከቷል። እስካሁን ባለው አሰራር ሰበር ራሱን ችሎ ለብቻው የወጣ የሰበር ስርአት የሌለው በመሆኑ ልዩ ልዩ ቅሬታዎችን ሲያስከትል መቆየቱ ይታወቃል። በመሆኑም ሕጉ የሰበር ስርአትን በዝርዝር አካቷል። ይሁን እንጂ ሰበር በመሰረቱ ፍርድ እንደገና የሚታይበት ስርአት በመሆኑ ከይግባኝ ስርአት ጋር የሚጋራቸው በርካት ጉዳዮች ያሉት ነው። በመሆኑም ለሰበር ስርአት የተለየ ድንጋጌ እስካልተቀመጠ ድረስ የይግባኝ ስርአቶች ለሰበር ስርአትም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

ሕጉ ለሰበር የተለየ ስርአት ያሰቀመጠው በዋነኛነት በሁለት ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው ሰበር ለተከራካሪ ወገኖች የተሰጠ መብት ሳይሆን ለጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ስልጣን ከመሆኑ የሚመነጭ ነው። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ሰበር በፍትሕ ስርአቱ ላይ ሊጫወት የሚገባው አጅግ የተለየ አላማ ያለው ከመሆኑ የሚመነጭ ነው።

እነዚህን ምክንያቾች መሰረት ያደረጉ የሰበር አላማ እና የሰበር መርህ በሥነ ስርአት ህጉ ውስጥ በግልፅ ተቀምጠዋል። የሰበር አሰራር ከሚተችባቸው ምክንቶች ውስጥ አንዱ ሰበር በተቋቋመበት ሕግ ላይ ግልፅ

አላማ ያልተቀመጠለት በመሆኑ ከስልጣኑ እየወጣ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮችና አጋጣሚዎች አሉ የሚል ነው፡፡ አላማውና መርሁ በግልፅ መቀመጣቸው ይህንን ችግር ለመቅረፍ ያግዛል ተበሎ ታሰቧል፡፡

ሰበር በመሰረቱ መሰረታዊ ሕግ ስህተት የሚታረምበት ስርአት እንጂ እንደ ይግባኝ ስርአት ስሕተት ሁሉ የሚታረምበት ስርአት አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሚለው ትርጉም ያልተሰጠው በመሆኑ እስካሁን ያለተቋረጠ እና የተደበላለቀ ክርክር የሚደረግበት ሆኗል፡፡ ከዚህ በመነሳትም የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በሁለት ዋና ዋና መመዘኛዎች ላይ ተንተርሶ ለመሰረታዊ የሕግ ስህተት ትርጉም ያሰቀምጣል፡፡ የመጀመሪያው ስህተት የህግ ስሕተት ሆኖ ስህተቱ በተከራካሪ ወገኖች ላይ ብቻ ሳይሆን በሕግ ስርአቱ ላይ መናጋትን (ሾክ) የሚፈጥር መሆን ይኖርበታል፡፡ ሁለተኛው መለኪያ ህግ የሚባሉት ላይ (ከሕገ መንግስት አንስቶ) በአፈጻጸም ወይም በትርጉም የሚያጋጥሙ ስህተቶችን የሚመለከት ሆኖ ዝርዝራቸው በሕጉ ላይ የተቀመጡት ናቸው፡፡ ስህተቱ መሰረታዊ እንዲባል ሁለቱ መመዘኛዎች በአንድነት መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ትርጉም እስካሁን የሚያጋጥምን ችግሮችን በተሻለ ሁኔታ ለመቅረፍ ያግዛል ተብሎ ይታሰባል፡፡ሕጉ መሰረታዊ ለሚባሉት የሕግ ስህተቶች ትርጉም ሲሰጥ በፍፁም መሰረታዊ ሊባሉ የማይገባቸው የሕግ ስህተቶችንም ለይቶ አስቀምጧል፡፡

ከተከራካሪ ወገኖች በላይ በህግ ስርአቱ ላይ መናጋትን የሚፈጥርን ስህተት የማረም ፍልጎት የሁሉም አካላት ፍላጎት ነው ተባሎ ይታሰባል፡፡ ስህተቱ በፍድ ቤት ሥርአት ካልተስተካከለ ስህተቱን ለማስተካከል ህግ አውጪው በጉዳዩ ላይ ግልጽ ህግ ለማውጣት የሚገደድበት እድሉም ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ ለተከራካሪ ወገኖች ፍላጎት ብቻ የሚተው ባለመሆኑ ስህተቱ እንዲታረም ጥያቄ ሊያቀርቡ የሚችሉ ሰዎችን ማስፋቱ ተገቢ ነው፡፡ በዚህ መሰረትም የየፍርድ ቤት ፕሬዚዳነቶች በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች አማካኞነት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳነቶች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍድ ቤት ችሎት ወይም ሌላ የሚመለከተው አካል በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አማካኝነት አንድ ጉዳይ በሰበር እንዲታይ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በስር ፍርድ ተጠቃሚ ወይም ተጎጂ በሆነው ፍርደኛ ቅሬታ ባያቀርብም የእርሱን መብት በማይጎዳ መልኩ ሕጉ ተቃንቶ ሊተረጎም ይገባዋል ስለሚባልበት አግባብ ግን በእነዚህ አካላት ጥያቄ ቀርቦ የፍርደኛው መብት ሳይጎዳ ስለ ሕጉ ትርጉም ብቻ ውሳኔ መስጥትም የተገባ ስለሚሆን ይህንን የሚገዛ ተጨማሪ ድንጋጌ ተካቷል፡፡

የሰበር አላማን ለማሳካት አመልካቾች የሚጫወቱት ሚናም ጉልህ ነው፡፡ ለምሳሌ አመልካቾች ጉዳያቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ላይ እንዲያኩር ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ በመሆኑም የሰበር አመልካቾች ለሰበር የሚያቀርቡት ማመልከቻ ከይግባኝ ማመልከቻም በተለየ መልኩ ተፈፀመ የሚባለውን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሚያመለክትና መሰረታዊው የሕግ ስሕተት ሊታረም ወይም ተቃንቶ የሚታረምበትን/የሚተረጎምበትን ምክንያት በግልጽ ማመላክት ይኖርበታል፡፡

የሰበር ሰሚውን ፍርድ ቤት ስላጣን በተመለከተ ችሎቱ አንድ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያለው ስልጣን ያለው ቢሆንም በተወሰኑ ጉዳዮች በተለይ በክልል ፍርድ ቤት ጉዳዮች ላይ የሕጉን ትርጉም በማቃናት ጉዳዮ ግን የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለስር ፍርድ ቤት መመለስን ቢመርጥ ተከራካሪ ወገኖች የሚኖራቸውን የመሰማት መብት ከፍ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን ሰፋ ባለ ስልጣን ተመልክተው ውሳኔ መስጠት ወደሚችሉት የስር ፍርድ ቤት ቢመልሰው ተመራጭ ነው፡፡ የሰበር ውሳኔ በውጤቱ በማናቸውም ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅ ቢሆንም ባይሆንም የሕግ አለዚያም የሞራል አስገዳጅነት ውጤቱ የማይቀር በመሆኑ "ሰብሮ መመለስ" የሚመከር ነው፡፡

የወንጀል ጉዳይ በዋነኛነት በሕገ መንግስቱ የተመለከቱትን የሰብኣዊ መብት ጉዳዮችን የሚመለከቱ መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡ እነዚህን ጉዳዮች የማክበርም ሆነ የማስከበር ሃላፊነት የሁሉም አካላት ግዴታ ነው፡፡ አሁን ባለው አሰራር ለሰበር የሚቀርቡት አበዛኛዎቹ ጉዳዮች ለሰበር ችሎቱ ሳይቀርቡ "አጣሪ ችሎት" በሚሰጠው ውሳኔ/ትእዛዝ እንደሚቋጩ ይታወቃል፡፡ የኃላ ኃላ ቢሆንም አጣሪው ችሎት ለሰበር ችሎቱ ከመራቸው ጉዳዮች ውስጥ በርካታ ጉዳዮች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለባቸውም ተብለው ይዘጋሉ፡፡ በሌላ በኩልም አጣሪው ችሎት ከመለሳቸው ጉዳዮች ውስጥ መሰረታዊ የሕግ ስህተት እያለባቸው ተዘግተዋል የሚል ቅሬታም የሚሰማባቸው ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም ይህንን አሰራር ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡

አሁን ባለው አሰራር አጣሪ ችሎቱ በሶስት ዳኛ የሚሰራ ነው፡፡ አጣሪ ችሎቱ የመጨረሻ ውሳኔን የመሻር፣ የመለወጥ እና የማሻሻል ስልጣን ባይኖረውም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመደበኛው ችሎት የተሰጠን የመጨረሻ ውሳኔን ግን የሚመረምር ችሎት ነው፡፡ በሌላ በኩል የሰበር ችሎቱም አካል አይደለም፤ ነው የሚባል ቢሆን ደግሞ አያስቀርብም የሚላቸውን ውሳኔዎች ጨምሮ ሌሎች ውሳኔዎቹ የሰበር ችሎቱ ውሳኔ ውጤት ይኖራቸዋል፡፡ አነዚህን አሰቸጋሪ ውጤቶችን ለመቆጣጠር እንዲሁም የሰበአዊ መብት ጉዳዮች በጠራ ሁኔታ እንዲመረመሩ ለማድረግ በወንጀል ጉዳይ ላይ የአጣሪ ችሎት አሰራር ቀሪ

እንዲሆን የስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ታሳቢ አድርጓል። የሌሎች አገራት ልምድም ይህንን ያመለክታል። አሰራሩ አጣሪ ችሎቱ ቀሪ የሚሆንበትንና የአጣሪ ችሎቱን የሰው ሃይል ጨምሮ የሰበር ችሎቱ ዳኞችን ቁጥር በማብዛት፣ በጉዳዮች አይነት የተካነ ዳኛ በማበርከት እንዲሁም ለስራው በሚያስፈልግ ቁጥር የበረከተ የሰበር ችሎት በማቋቋም ተግባራቱ ሁሉ በመደበኛው የሰበር ችሎት ተጠናቀው እንዲፈፀሙ ስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ያስባል። ይህም የሰብአዊ መብትን በተሻለ መልኩ በማስጠበቅ የሰበር ተግባርን ጥራት በእጅጉ ይጨምራል የሚል እሳቤ ይዟል።

ከሰበር አላማ አንፃር ሌላው ድንጋጌ ውስጥ የተካተተው ጉዳይ የሰበር ማመልከቻ ከቀረበ በኋላ የተከራካሪ ወገኖች ያለመቅረብን የሚመለከተው ጉዳይ ነው። ሰበር ከተከራካሪ ፍላጎት በላይ የሚያሳካው የተለየ ተልእኮ ያለው በመሆኑ ተከራካሪዎች ባለመቅረባቸው ብቻ ጉዳዩ መቋረጥ የሌለበት ሆኖ በሕግ ጉዳይ ላይ ችሎቱ የመሰለውን ውሳኔ መስጠት እንዳለበት የሚያስገነዝቡ ድንጋገዎች ተካተዋል።

የሰበር ውሳኔ በማናቸውም ፍርድ ቤት አስገዳጅ ውጤት ያለው ነው። አስገዳጅነቱ በፍርድ ቤት ላይ ይሁንም እንጂ በውጤቱ የመገደዱት ተከራካሪ ወገኖችና መላው ሕብረተሰቡ ነው። ምንም እንኳዋን ተግባሩ ሕግ መተርጎም ቢሆንም ሕብረተሰቡ በተሳትፎው ያወጣው ሕግ ባልተሳተፈበት ሁኔታ በተተረጎመው ሕግ የሚገደድበት አጋጣሚ ይበዛሉ ማለት ነው። ስለሆነም የሰበር ውሳኔ አስገዳጅነት የሚቀጥል ቢሆን ከተከራካሪ ወገኖች ፍልጎት በተጨማሪም ሌሎች ፍልጎቶች የሚሰሙበትን አድል ማስፋትና ስርአቱን ይበልጥ አሳታፊ ማድረግ ያስፈልጋል። ስለሆነም በውሳኔ መስጠት ሂደት ውስጥ ስለጉዳዩ ሳይሆን ስልህጉ ትርጉም ብቻ የሚመለከታቸው አካላት (የሕግ ትምህርት ቤቶች፣ የህግ ምርምርና ስልጠና ተቋማት፣ የሕግ አውጪው ሕግ ጉዳይን የሚመከታተሉ አካላት…) ተገቢ ነው ስለሚሉት የሕግ ትርጉም አስተያየት በፅሑፍ መስጠት የሚችሉበትን እድል ሕጉ ክፍት አድርጓል። ሰበር ሰሚው ችሎት በአሰተያየቶቹ የማይገደድ ቢሆንም አስተያየት መቀበሉ የሕጉ ትርጉም ሊያሳካ ከሚያስበው ግብ አንፃር ተገቢ ነው። ጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ውጤት ከተከራካሪ ወገኖች በላይ በመሆኑ የሚመለከታቸውን አካላት አስተያየት መቀበልና መመርመር ሕገ መንግስታዊ አሳታፊነት ነው። ስለሆነም የሰበር ችሎት በአሰራሩ ይበለጠ አሳታፊ እንዲሆን ታስቧል።

በሌላ በኩል የሰበር ስራ አላማውን ሙሉ በሙሉ ለማሳካት እንዲችል በጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚቋቋም የሕግ ምርምር ክፍል (ወይም የሕግ ጥናትና ምርምር ባለሙያዎች) ስለ ህጉ ትርጉም ጥናትና ምርምር እንዲደረግለት ለማድረግም እንዲችል ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## 15.3 ፍርድን እንደገና ማየት

በአንድ ፍርድ ቤት የተሰጠ ማናቸውም ፍርድ ፍርዱ በተሰጠበት ወቅት በየትኛውም ፍርድ ቤት ያልተገለጠ ስሕተት ያለበት ሆኖ መሰረታዊ የሆነ የፍርደኛ መብት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከተለ የሚሆንባቸው አጋጣሚዎች አሉ፡፡ በእንደዚህ ባለው አጋጣሚ የተሰሳተው ፍርድ የሚስተካከልበት ሁኔታ ሊኖር የሚገባው ነው፡፡ የዚህን አይነት ጉዳይ ሊሰተናግድ የሚችል ሕግም ሆነ አሰራር በአገራችን የሌለ በመሆኑ የፍርደኞች ጥያቄ ቢኖርም ስህተት መኖሩን መርምሮ መልስ የሚሰጥበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲውን፣ በተግባር የገጠሙ ችግሮችን እንዲሁም የውጪ አገራን ልምድ በመመልከት የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በዚህ ጉዳይ ላይ ዝርዝር ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡

በጠቅላላው አነጋገር የፍርድ እንደገና ይታይልኝ ጥያቄ አቀራረብ ለይግበኝ በሚቀርበው አይነት መሆን እንደሚገባው ሕጉ ያስቀምጣል፡፡ ይሁን እንጂ ከጉዳዩ ልዩ ባህሪ በመነሳት የተለዩ ጉዳዮችንም አካቷል፡፡ የፍርድ እንደገና ይታይልኝ ጥያቄ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ የሚቀርብ ቢሆንም ከተፈፀመው ስህተት እና በስህተቱ ምክንያት ከደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት አንፃር የጊዜ ገደብ ሳያግደው በማናቸውም ጊዜ እንዲቀርብ ሕጉ ሰፊ መብት ይሰጣል፡፡ ጥያቄ የሚቀርብበት ፍርድ የሞት፣ የእስራት፣ የገንዘብ ወይም ሌላ ቅጣት ቢሆንም በመጨረሻ ደረጃ የፍሬ ነገር ጉዳይ ላይ ውሳኔ በሰጠው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ስለሚሆንም ጥያቄውም የሚቀርበው ከሰበር በታች ያለውና ስህተት ያለበትን ፍርድ በመጨረሻ ደረጃ ለሰጠው ፍርድ ቤት ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም የቀረበውን ማመልከቻ ከተቀበለው አቃቤ ሕግ በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጥበት በማድረግ አንድም ቀድሞ የተሰጠውን ፍርድ ውድቅ በማድረግ አመልካቹን በነፃ ያሰናብታል ወይም ቀድሞ የተሰጠውን ፍርድ ያፀናል አለዚያም ቀድሞ የተሰጠው ፍርድ በማንሳት ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ያደርጋል አለዚያም ፍርዱን ሙሉ በሙሉ ውድቅ ያደርጋል፡፡ ፍርዱ እንደገና መታየት ያለበት ሆኖ ከተገኘ ማናቸውም የተሰጠ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ ተነስቶ ጉዳዩን ቀድሞ ያላየው ፍርድ ቤት ወይም ችሎት በጉዳዩ ላይ እንደገና ክርክር አድርጎ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡ ጉዳዩን እንደገና የሚመለከተውን የበታች ፍርድ ቤት የመጨረሻው ፍርድ ቤት በውሳኔ መርጦ ሲልክ በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ውሳኔ በመስጠት የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉን አላማ ያሳካል የሚባለውን ፍርድ ቤት በመምረጥ ነው፡፡

ፍርዱ የተሻረ እንደሆነ በተሰሳተ ፍርድ ፍርደኛው ወይም ቤተሰቡ መጎዳታቸው እርግጥ ነው። ይህ ጉዳት የገንዘብና የንብረት ጉዳት ብቻ ሳይሆን የጤናም ጭምር ስለሚሆን ጉዳቱን ሙሉ በሙሉ መካስ ሊያስቸግር ይችላል። ያም ቢሆን በተሳሳተ ፍርድ ለተጎዳ ፍርደኛ የሞራልም ሆን የንብረት ጉዳት ካሳ ማገኘት ያለባቸው በመሆኑ ተመጣጣኝ ካሳ ከመንግስት እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል። ፍርደኛው በሕይወት የሌለም እንደሆነ ለትዳር ጓደኛው ወይም ለወራሾቹ ካሳ ሊከፈል ይገባል። የካሳው አከፋፈልን በተመለከተ በጉዳዩ ላይ የአፈፃፀም ደንብ እንደሚወጣ ሕጉ ታሳቢ የሚደርግ ቢሆንም ደንቡ እስኪወጣ ድረስ ግን የካሳው መጠን ተመጣጣኝነት አግባብ ባለው ሌላ ሕግ (በፍትሐብሔር ደንብ) መሰረት የሚሰላ ይሆናል።

በተሳሳት ፍርድ የደረሰን ጉዳት በተለይም የሞራል ጉዳት የገንዘብ ካሳ ብቻ ይተካዋል ተብሎ አይታሰብም። ሕጉም ይህንን ታሳቢ በማድረግ ከካሳው በተጨማሪ በተጎጂው ላይና በቤተሰቡ ላይ ለደረሰው ጉዳት መንግሰት ይቅርታ እንደሚጠይቅ ይደነግጋል። የይቅርታ አጠያየቅ የራሱ ስርአት ሊኖረው ስለሚችል ተጨማሪ ደንብ የሚወጣ ሲሆን ደንቡ እስከሚወጣ ድረስ ግን በተመሳሳይ መልኩ ስራ ላይ ያሉ ሌሎች ሕጎች ተፈፃሚ ይሆናሉ። ስህተትን በይፋ መቀበልና ይቅርታ መጠየቅ የካሳን ጉድለት ሊሞላ የሚችል ከመሆኑም በላይ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠው የተጠያቂነት ስርአት ማረጋገጫና የሰለጠነ መንግስት መገለጫም በመሆኑ በሕጉ እንዲካተት ሆኗል።

## 16. በወንጀል ጉዳይ አለም አቀፍ የወንጀል ጉዳዮች ትብብር

ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች እና ጉዳዮች እየተወሳሰቡ የመጡ ከመሆናቸውም በላይ አለም አቀፍ ትብብርም እጅግ እየተወሳሰብ መጥቷል። የፍትሕ አካላት በዚህ ረገድ የሚኖራቸውን የትብብር ድርሻ በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ እና አገራችንም አለም አቀፍ ግዴታዋን በአግባቡ መወጣት እንደትችል በወንጀል ህግ ድንጋጌ ያሰፈልጋል። አለም አቀፍ ትብብር በመሰረቱ እንደቅደም ተከተሉ በአለም አቀፍ ህጎችና መርሆዎች፣ በሁለትዮሽ ወይም በብዙ አገራ መካከል በሚደረግ ስምምነተና በአገሪቷ ሕጎች (የወንጀል ስነ ስርአትና የማስረጀን ጨምሮ) አማካኝነት የሚተገበር ነው። አለም አቀፍ ትብብርን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በመሰረቱ አለም አቀፍ ተቀባይነትን ያተረፉ እና ደረጃቸውን የጠበቁ አሰራሮችን ለመስራት በሚያስችል መልክ መደንገግ ያለባቸው በመሆኑ ሕጉ ከዚህ ጋር የተጣጣሙ ድንግጌዎችን ይዟል።

የዓለም አቀፍ ጉዳዮችን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመቋቋምና ለችግሮቹ መፍትሔ ለማፈላለግ አገሮች ለየብቻቸው ከሚያደርጉት ጥረቶች ይልቅ ተባብረው በጋራ የሚሠሩት ሥራ የተሻለ ውጤት እንዳለው ይታመናል። በዚህ የተነሳ አገሮች የጋራ ችግሮቻቸውን ሊቋቋሙና ሊፈቱ የሚችሉበት የጋራ የአሠራር ሥርዓቶችን ቀይሰው ሲሠሩ ኖረዋል። አገሮችን በጋራ ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች መካከል አንዱ ከወንጀልና ከወንጀል ሕጐች ጋር ተያይዞ ያለ ችግር ነው። ይህንን ችግር ለመፍታትም ይረዳቸው ዘንድ በጋራ መግባባት ላይ የደረሱበትን የጋራ አሠራሮችን ቀይሰው አብረው ሲሰሩ ቆይተዋል። አሁን ባለው የልሉላዊነት ዓለም እንኳ ከወንጀል ጉዳዮች ጋር ተያይዘው ያሉ ችግሮች የሁሉም አገሮች የጋራ ችግሮች ሆነው ከመቀጠላቸውም አልፎ የዓለም ሕዝቦች የጋራ የስጋት ምንጭ ሆነዋል። አሁን ባለንበት ዓለም የሚፈፀሙ ወንጀሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በአይነትና በብዛት እንዲሁም በአፈፃፀም ስልቶቻቸው የተወሳሰቡና የተበራከቱ ሆነዋል። እንደ ሽብርተኝነት፣ በተደራጁ ቡድኖች የሚፈፀሙ ወንጀሎች፣ ሕገ ውጥ የሰው የጦር መሳሪያ እና መድሓኒት ዝውውር፣ የሳይበር እና የመሳሰሉት ወንጀሎች የዓለማችን የጋራ ችግሮች ሆነዋል። በመሆኑም ሃገሮች ብሔራዊ ጥቅሞቻቸውንና ደህንነታቸውን በማስጠበቅ ዜጐቻቸውንና ተቋሞቻቸውን ከወንጀል ድርጊት ለመከላከል ሲሉ የዓለም አቀፍ ትብብር አሠራሮችን ለማጠናከር ከምንጊዜም በበለጠ ትኩረት ሰጥተውበት እየሰሩ ይገኛሉ። አገራችን ኢትዮጵያም የዓለም አቀፍ ማሕበረሰብ አካል እንደመሆኗ እና ጉዳዩም በቀጥታ የሚመለከታት እንደመሆኑ መጠን የዓለም አቀፍ ትብብር አሠራርን አስመልክቶ ብዙ ሥራ መሥራት ይጠበቅባታል።

የዓለም አቀፍ ትብብር ሥራ የሚመሠረተው በዓለም አቀፍ እና በብሔራዊ ሕጐች ላይ ተመስርቶ ሲሆን በአገር ውስጥ የሚሠራ ሥራንና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚሠራ ስራን ያካትታል። በሃገር ውስጥ የሚሠሩ የዓለም አቀፍ ትብብር ሥራዎች በዋናነት በሃገር ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ተቋማት መካከል የሚኖረው ግንኙነትና ትብብር እንዲሁም በእነዚህ ተቋማት የሚከናወኑ ሥራዎችን በቀጥታ የሚመለከትነው። በዚህም መሠረት በአገር ውስጥ በሚገኙ ተቋማት መካከል የሚኖረው ግንኙነትና የአሠራር ሥርዓት አንዱ የዓለም አቀፍ ትብብር ገፅታ ነው ለማለት ይቻላል።

አለም አቀፍ ትብብር በዋነኛት የሚመራው በዓለም አቀፍ ሕጐችና ስምምነቶች ሲሆን ለሥራው መሳካት በአገራቱ መካከል የሚኖረው ዲኘሎማሲያዊ ግንኙነትም ወሣኝነት አለው። አገራችንን የሚመለከቱ ድንበርተሻጋሪ ወንጀሎችን ለመከላከል፣ ለመመርመር፣ ለሕግ ለማቅረብ ወይም ለመቅጣት በመጀመሪያ ከሚመለከታቸው አገሮች ጋር የሕግ መሠረት ያለው ግንኙነት መፍጠር የግድ ይላል። የሌሎች ሃገሮችን

የትብብር ጥያቄ ተቀብሎ አጥጋቢ መልስ ለመስጠትም ከላይ የተጠቀሰውን የትብብርና የአሠራር ሥርዓት መፍጠር የግድ ነው። በአገር ውስጥ ያሉ ብሔራዊ ተቋማት መካከልም ያለውን የሥራ ግንኙነትና ትብብር በሕግ አግባብ ሥርአት ማስያዝ በተመሳሳይ አስፈላጊ ነው። አገሮች የዓለም አቀፍ ትብብር ሥራዎችን አስመልክቶ በዓለም አቀፍ ሕጐች አማካይነት የገቧቸውን ግዴታዎች እና ያሏቸውን መብቶች መፈፀምና ማስፈፀም የሚችሉት በሀገራዊ ሕጐቻቸው አማካይነት ነው። በአንድ አገር በተለያዩ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ የተካተቱትን ሥነሥርዓቶች፣ አሠራሮች፣ አደረጃጀቶችና የመሣሠሉትን መፈፀምና ማስፈፀም የሚቻለው በአገራዊ ሕጐች ውስጥ በበቂ ሁኔታ ከተካተቱ ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። እነዚህ አገራዊ ሕጐች በዋናነት የትብብሩን ፍሬ ነገሮች የሚወስኑ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ የትብብሩን ሥራዎች ለማቀላጠፍ የሚረዱ የአደረጃጀትና የሃገር ውስጥ የፍትሕ ተቋማት የሥራ ግንኙነቶችን መልክ የሚያስይዙ ናቸው።

እስካሁን ባለው ሁኔታ የእነዚህን አይነት ግንኙነቶች በሁለትዮሽ ወይንም በባለ ብዙ አገራት ስምምነቶች እና አለም አቀፍ ሕጎች እየተመራ ቢሆንም በስነ ስርአትና ማስረጃ ህጉ ውስጥ የተመለከተ ወንጀል ነክ ግንኙነትም የሚመራ ስርአት አልነበረም። በመሆኑም ከላይ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት የስነ ስርአትና ማስረጃሕ ጉ ይህንን ጉዳይ ሊመራ የሚችል ድንጋጌ አካቷል። ግንኙነቱ የሁለትዮሽ በመሆኑም በሕ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በተለየ መልኩ ካልተመለከተ በስተቀር ኢትዮጵያ ትብብር ስትጠይቅም ሆነ ትብብር በምትጠይቅበት ወቅት ሁሉ የሚፈጸሙ ናቸው። የትብብር አይነቶቹ ለወንጀል ጉዳይ አዲስ በመሆናቸውም ምንታቸውን ጨምሮ የተካተቱበትን አግባብ ከዚህ በታች ያሉት ክፍሎች ይመለከቱታል።

### 16.1. የዓለምአቀፍትብብር ምንነት

በዓለም አቀፍ ግንኙነት ውስጥ የዓለም አቀፍ ትብብር የቆየ እና የታወቀ ቢሆንም እስከአሁን ድረስ ግልፅ የሆነ የሕግ ትርጉም አልተበጀለትም። ይህ አሠራር የዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የሃገር ውስጥ ሕጐችን መሠረት ያደረገ በመሆኑ በተለያዩ አገሮችና አገሮቹ በሚከተሏቸው ሥርዓቶች ውስጥ የተለያየ ይዘትና ትርጉም ሲሰጠው ይታያል። በሃገራችንም ቢሆን የዓለም አቀፍ ትብብር የሚባል በግልፅ ትርጓሜ የተሰጠው ሥራ የለም። ይሁንና በተለያዩ የዓለም አቀፍ ሰነዶችና የአገሮች ሕጐች ውስጥ የዓለም አቀፍ ሥራዎች ተዘርዝረው የሚገኙ ሲሆን በአገራችንም በተለያዩ አካላት የተወሰኑ ሥራዎች በዓለም አቀፍ ትብብር ሥራዎች ውስጥ ተካተው ሲሠሩ ቆይተዋል። በዚህም መሠረት በተለያዩ የዓለም አቀፍ ሰነዶችና

በሃገራችን የነበሩትን ልምዶች መሠረት በማድረግ በዓለም አቀፍ ትብብር ሥራ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉት እንደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡

## 16.2. አሳልፎ መስጠት (Extradition)

የአሳልፎ መስጠት አሠራር ሁለት ገፅታ አለው፡፡ አንደኛው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ወንጀል ፈፅመው ወደ ሌላ ሃገር የሸሹትን ፣ወይም በውጭ ሃገር ባሉ የኢትዮጵያ ጥቅሞች ላይ ወንጀል ፈፅመው ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኙ ተጠርጣሪዎች ወይም ጥፋተኞች ተላልፈው ለኢትዮጵያ እንዲሰጡ ጥያቄ ማቅረብን የሚመለከት ነው፡፡ ሁለተኛው በሌላ ሃገር ወንጀል ፈፅመው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ትተጠርጣሪዎች ወይም ወንጀለኞች ተላልፈው እንዲሰጡ የቀረበን ጥያቄ ተቀብሎ እንደ አግባብነቱ የማስተናገድ አሠራርን የሚመለከት ነው፡፡ ይህ አሠራር በኢትዮጵያ ሕጎችና ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው የዓለም አቀፍ እና የሁለትዮሽ ስምምነቶች መሠረት የሚሠራ ሥራ ነው፡፡ የአሣልፎ መስጠት ሥራ በብዙ የጋራ ስምምነቶች ውስጥ የተካተተ ሲሆን የአገራችን ሁኔታ በተመለከተ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 21 ሥር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አገራችን ከተለያዩ አገሮች ጋር የተፈራረመቻቸው የሁለትዮሽ (bilateral) ስምምነት ያለ ሲሆን ከጅቡቲና ከሱዳን መንግሥታት ጋር የተፈራረመችውን ስምምነት በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

## 16.3 በወንጀል ጉዳዮች መረጃ መለዋወጥ እና መተባበር (Mutual legal assistance)

ይህ አሠራር ከወንጀልና ከዳኝነት ሥራዎች ጋር ተያይዘው ያሉ መረጃዎችን ሃገሮች ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ የተጠየቀውን መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ ወይም እነዚህ አካላት በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ መረጃ እንዲሰጡ ጥያቄ ማቅረብንና መቀበልን የሚያጠቃልል አሠራር ነው፡፡ አሠራሩም የዓለም አቀፍ ሕጐችንና የሃገር ውስጥ ሕጐችን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በወንጀል ጉዳዮች መረጃ የመለዋወጥ ሥራን አስመልክቶ የተለያዩ አሠራሮች ያሉ ቢሆንም ሥራው በዋናነት የሚከተሉትን ተግባራት ያጠቃልላል፡፡ የሚጠየቁ ጥያቄዎች እና የሚላኩ የሥነ ሥርዐት ሰነዶችን ማፋጠን፣ የተለያዩ ግንኙነቶችን ለመጥለፍ የሚውሉ ቴክኒካል መሣሪያዎችን በማሳለፍ መርዳት፣ የሚተላለፉ መልዕክቶችን ለመቆጣጠር እና ስውር የምርመራ ሥራዎችን በድንበር አካባቢና በድንበር ላይ እንዲሰሩ መፍቀድ፣ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ምስክሮች በቪዲዮ እና በቴሌኮንፈረንስ የሚሰሙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ የታሰረ ሰው ለጊዜያዊ ምርመራ እንዲያግዝ ማስተላለፍ እና የመሣሠሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ አሠራሩ እና የትብብር ደረጃው

እንደየሀገሮቹ ብሔራዊ ሕጐች የሚለያይ ከመሆኑ የተነሳ የተለያዩ ችግሮች ያጋጥሙታል። ሃገራችን በወንጀል ጉዳዮች መረጃ መለዋወጥን አስመልክቶ ምንም ዓይነት ብሔራዊ ሕግ የሌላት በመሆኑ በዚህ ረገድ ብዙ ችግሮች ሲከሰቱ ይስተዋላል።

### 16.3.1.ፍርደኞችን መስጠት ወይም መቀበል (Transfer of sentenced persons)

በአንድ ሃገር ፍርድ ቤት የተፈረደባቸውን እስረኞች ለሌላ ሃገር መስጠት ወይም መቀበል የተለመደ የዓለም አቀፍ ትብብር ሥራ ነው። ይህ የሚሆንባቸው የተለያዩ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን በዋናነት ለምስክርነት ወይም ለሌላ የደህንነት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም በቅጣት መርህ መሠረት ፍርደኛው ይታረማል ተብሎ የሚታሰበው በራሱሕብረተሰብ ውስጥ ስለሆነ ፍርደኛው ወደተፈረደበት ሃገር እንዲመለስ ሃገሮች ይጠይቃሉ። ይህን ጉዳይ የሚመራ ሕግ በአገራችን ያነበረ ሲሆን ከዚህ አንፃርም የዳበረው ልምድ እምብዛም ነው።

### 16.3.2. የወንጀል ክስን ወደ ሌላ ሃገር ማስተላለፍ

ይህ አሠራር በአንድ ሃገር እየታየ ያለን የወንጀል ክስ ወደ ሌላ ሃገር ማስተላለፍ ወይም በሌላ ሃገር እየታየ ያለውን ጉዳይ መውሰድን ያጠቃልላል። ይህ የሚደረገው በተለያዩ ምክንያቶች ቢሆንም በዋናነት የክሱን ሂደት ውጤታማ ለማድረግ ተብሎ የሚሠራ ነው። በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ ይህ አሠራር በብዛት የተቀመጠ ሲሆን እንደ UN Convention against Illicit Trafficking of Narcotic Drugs and Psychotropic substance Article (8) እና UN Convention on Transnational Organized Crime Art. 21) የመሰሉትን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። በሃገራችን የወንጀል ሕግም ሆነ በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጐች ውስጥ ይህ አሠራር ምን እንደሚመስል የሚያመለክት ሕግ በግልፅ እና በዝርዝር ባለመኖሩ የሃገራችን አሠራር ምን እንደሚመስል ለማወቅ ያስቸግራል።

### 16.3.3. ሌሎች የዓለም አቀፍ ትብብር ዓይነቶች

ከላይ የተጠቀሱት ዋና ዋና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት የዓለም አቀፍ ትብብር ዓይነቶችን መጥቀስ አስፈላጊ ነው። ከሙስና፣ ከኢኮኖሚ፣ ከፋይናንስና ከሕገ ወጥ ገንዘብ ዝውውር ወንጀሎች ጋር በተያያዘ የወንጀል ምርመራ ለማካሔድ ማስፈቀድ ወይም እንዲካሔድ መተባበር፣ የወንጀል ፍሬ የሆኑ ንብረቶችን ማገድ፣ መውረስ እና ማስወገድ፣ የወንጀል ምስክሮችና ሰለባዎችን መጠበቅና መንከባከብ፣ በሕግ አስፈፃሚ አካላት መካከል የሚኖሩ ልዩ ልዩ የሥራ ትብብሮች ለምሳሌ ለየት ያለ የምርመራ

ዘዴዎችን መጠቀም፣ እንደዚሁም የወንጀል መከላከል ሥራዎችን በጋራ መሥራት፣ በህግ ጉዳይ ላይ በጋራና በትብብር መስራትና ሌሎችን ሊካተቱ ይቻላል። ከላይ የተጠቀሱ ሥራዎች በዋናነት የዓለም አቀፍ ትብብር ሥራዎች ሲሆኑ በተለያዩ የዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የአገሮች ብሔራዊ ሕጐች ውስጥ ተዘርዝረው የሚገኙ ናቸው።

## 16.4 የዓለም አቀፍ ትብብርንና የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት

ብዙ ሃገሮች የዓለም አቀፍ ትብብርን አስመልክቶ ያሉ ጉዳዮችንና አሠራሮችን በወንጀል ሕጐቻቸው ውስጥ በዝርዝር ከማስቀመጥ በተጨማሪ አስፈላጊ የሆኑ ልዩ ሕጐችን ያወጣሉ። ለምሳሌ ካናዳን ብንመለከት አብዛኛው የዓለም አቀፍ ትብብር አሠራሮችን በወንጀል ሥነ ሥርዐት ሕግ ውስጥ በዝርዝር ከማካተቷም በተጨማሪ ለየት ያሉ እንደ "በወንጀል ጉዳይ ላይ የጋራ ትብብር ለማድረግ የሚያስችላት ሕግ" ያሉ ልዩ ሕጐች አሏት። የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዐት የወንጀል ጉዳዮችን አስመልክቶ የዓለም አቀፍ የትብብር ሥራዎችን ለመሥራት የሚያስችሉ በቂ ድንጋጌዎች የሉትም። ከዓለም አቀፍ ትብብር ሥራዎች ጋር ተያይዞ የአገራችን ሕችጎ በበቂ ሁኔታ ተሟልተው ባይገኙም በአንዳንድ የትብብር መስኮች (ለምሳሌ አሳልፎ መስጠትን እና የውጭ ውሳኔዎችን ማስፈፀም ወዘተ) ላይ የተወሰኑ ድንጋጌዎች አሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ ሕችጎ በቂና ግልፅ አይደሉም። በዓለም አቀፍ ትብብር ጉዳዮች ላይ የእያንዳንዱ የፍትሕ እና የሚመለከታቸው አካላት ተግባርበ ግልፅ ባለመታወቁ እና ሥራዎቹ በማን፣ እንዴት ወዘተ እንደሚሠሩ የሚደነግግ የሕግ ድንገጌዎች ባለመኖራቸው ሥራው ወጥ በሆነ መንገድ መሠራቱን ለመከታተል እና ለመቆጣጥር አልተቻለም። በመሆኑም በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ዘርፍ ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፍ ሕግጋት እና አሠራር ሥርዓት አንጻር ያሏትን መብቶች ለማስከበር እና የተጣሉባትን ግዴታዎች ለመወጣት የሚያስችል ጠንካራ የሕግ ማዕቀፍ ለመፍጠር ተችሏል ለማለት አይቻልም። የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዐት እነዚህን ችግሮች ከመፍታት አንጻር እጅግ ወሳኝ ሚና ያለው ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዐት ሕግ ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ግልጽ የሆነድ ንጋጌ የያዘ አይደለም።

ይህንን ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት የኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ ከወንጀል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የዓለም አቀፍ ትብብር የሚደረግባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች የተመሠረቱ የወንጀል ክሶችን፣ ዓለም አቀፍ ባሕርያት ባላቸው ወንጀሎች ላይ የሚደረጉ ምርመራዎችንና ለወንጀል ድርጊት ምስክሮችና ተጎጂዎች የሚደረጉ ጥበቃዎችን በተመለከተ የሚደረጉ ትብብሮች እንዲሁም ለፍርድ

ቤት ውሳኔዎች ዕውቅና መስጠትና ማስፈጸም፣ የወንጀል ጉዳዮችን ወደ ሌላ ሀገር ማስተላለፍ፣ አሳልፎ መስጠት፣ የጋራ የሕግ ድጋፍ እና የወንጀል ፍሬ የሆኑ ንብረትን ወይም ገንዘብን ማገድና መውረስን የሚመለከቱ እንደሆኑ እና በሕግ ጉዳዮች ዓለም ትብብር መስክ ያሉ ሕጎች ዓለም አቀፍ ትብብር የሚመራባቸው ዘመናዊ የአሰራሮችን፣ መርሆዎችን እና ሕጎችን በሚያካትቱ እና አፈጻጸማቸውን በሚያቀላጥፍ መልኩ ሊሻሻሉና አዳዲስ ድንጋጌዎችን እንዲያካትቱ ሊደረግ እንደሚገባ በግልጽ አመላክቷል፡፡ ይህን ኑተከትሎ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመፍታት እና የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲውን ለማስፈጸም ይህ የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዐት በወንጀል ጉዳዮች የአለም ዓቀፍ ትብብርን የሚመለከቱ ጠቅላላ ድንጋጌዎች፣ ልዩ ልዩ የትብብር ዓይነቶች የሚፈጸምበትን ሥነ ሥርዓት እና ስለ አሳልፎ መስጠት ዝርዝር ሥነ ሥርዓቶችን አካትቶ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡

በሕጉ ላይ በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ ትብብር ዓላማ ሀገሪቱ ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚኖሩ መብትና ጥቅሞችን ለማስከበር እና ግዴታዎችን በአግባቡ ለመወጣት ማስቻል እንደሆነ በግልጽ በመደንገግ በሕጉ የተካተቱ የዓለም አቀፍ ትብብር ድንጋጌዎች የሚተረጎሙት ከዚህ ዓላማ አንጻር መሆን እንዳለበት ለማስገንዘብ በግልጽ ተካትቷል፡፡ በመርህ ደረጃ ሕጉ በወንጀል ጉዳይ የሚደረግ ትብብር ኢትዮጵያ በምታደረገው ስምምነት መሠረት የሚፈፀም መሆን እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን የዚህ አይነት የሁለትዮሽ፤ ባለ ብዙ ሃገራት ወይንም አለም አቀፍ ስምምነት በሌለ ጊዜ ለሚቀርብ ማንኛውም የትብብር ጥያቄ በሕጉ የተካተቱት ዝርዝር ድንጋጌዎች ተፈጻሚ እንደሚሆኑ በስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ ተመልክቷል፡፡

በወንጀል ጉዳይ አለም አቀፍ ትብብር በስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ ውስጥ ሲካተት የራሱን መርህና አላማ ይዞ ነው፡፡ በዋነኛነት አላማውም የአገሪቷን ጥቅምና መብት ለለማስከበር ሲሆን በመርሕ ደረጃም ከስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ይልቅ አገራችን በምትፈርማቸው ስምምነቶች የሚመራ ነው፡፡ ለኢትዮጵያ የሚቀርብ የትብብር ጥያቄ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥትንና ሉዓላዊነት የሚያስከብር፣ የአገሪቱን ሕዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅ፣ በእንካ ለእንካ መርህ እና በጋራ ጥቅምና እኩልነት ላይ የተመሠረተ መሆን እንዳለበት በሕጉ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ትብብር በአገሪቱ ሕገ መንግስተ የተመለከቱ የሰብአዊ መብቶችን በሚጥስ ወይም የእኩልነት መብትን በሚጥስ መልክ ሊፈፀም እንደማይችል ይደነግጋል፡፡

በአሳልፎ መስጠት ጊዜም ከተቀመጡት ገደቦች መካከልም ኢትዮጵያዊ ዜጋን አሳልፎ መስጠት እንደማይቻል ተደነግጓል። ትብብር ሊደረግበው የሚችሉ ተግባራንም (ከወንጀል ምርመራ፣ ከማስረጃ፣ ከምስክር እና ጠቋሚ ጥበቃ፣ ከአሳልፎ መስጠት፣ ከወንጀል ንብረት ፍሬ ወይም ገንዘብ፣ ከተያዘ የተፈረደበት ሰው ልውውጥ፣ ከውሳኔ ማሰፈፀም፣ እና ከሌሎች በመንግስት ከሚፈቀዱ) ተጋባራት ጋር የሚገናኙ የትብብር መስኮች እንደሆነ ይደነግጋል። ከፍ ሲል የተገለጹትን ችግሮች ግምት ውስጥ በማስገባትም የትብብር መስመርና የማስፈጸም ሥልጣን (በዲፕሎማሲያዊ መስመር)፣ የትብብር ወጪ (በጠያቂው እንደሚሸፈን)፣ የትብብር ጥያቄ ማቅረብ ስለሚችሉ አካላት (በዋነኛት ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ቀጥሎ የፌዴራል አካላት)፣ የጥያቄ አቀራረብ (በዋነኛነት በፅሁፍ)፣ የትብብር ጥያቄ ይዘት፣ የጥያቄውን ተቀባነይት፣ አግባብነት ማረጋገጥ እና ውሳኔ መስጠት፣ ማረጋገጫ መስጠት፣ የትብብር ጥያቄ አፈጻጸም፣ የወንጀል ምርመራና ከምርመራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ትብብር፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለን ሰው በጊዜያዊነት የማስተላለፍ ትብብር፣ በውጭ አገር በቁጥጥር ሥር ያለን ሰው ለትብብር መጠየቅ፣ ለትብብር ወደ ኢትዮጵያ የገባ ሌላ ሰው፣ በጠያቂ አገር ማረፊያ ወይም ማረሚያ ቤት መቆየት ያለው ውጤት፣ መጥሪያና ሌሎች ሰነዶች የማድረስ ትብብር፣ ፍርደኛን ማስተላለፍ፣ የፍርድ ቤት ትእዛዝ፣ ፍርድ ወይም ውሳኔ ዕውቅና መስጠትና ማስፈጸምን፣ በኢትዮጵያ ግዛት እስረኛን ማስተላለፍ፣ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት፣ በወንጀል ተፈላጊን ሰው አሳልፎ መስጠትን የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች በሕጉ  ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል።

የማናቸውም የትብብር ጥያቄ አፈፃፀም የወንጀል ተጎጂን የካሳ ወይም ሌላ የመብት ጥያቄ በሚጎዳ አኳኃን መፈጸም እንደሌለበት ሕጉ የሚደነግግ ሲሆን ትብብር እንዲደረግ የተወሰነ እንደሆነ የሚፈጸመው በጠቅላይ አቃቤ ሕግ አማካኝነት በሚመለከተው የመንግስተ ተቋም አማካኝነት እንደሆነም ይደነግጋል። ሥለሆነም በወንል ተጎጂ አቤቱታ የተጀመረ ሌላ የወንጀል ጉዳይ ምርመራ ወይም የፍትሐብሔር ክርክር ካለ ጥያቄው ለተወሰነ ጊዜ ሊተላለፍ ይችላል ማለት ነው።

በአለም አቀፍ ትብብር ሂደት የፍርድ ቤት ሚናም በተመሳሳይ በሕጉ ውስጥ እንዲካተት ሆኗል። በዚህ መልኩ ከተቀመጡት ሃላፊነቶች ውስጥም አሳለፎ የሚሰጥን ሰው ለጊዜው በእስር እንዲቀይ ትእዛዝ የመስጠት፣ በአሳልፎ ይሰጥ ጥያቄ ላይ በአምስት ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት፣ ለኢትዮጵያ ተላልፎ የተሰጠን ሰው በእስር እንዲቆይ ወይም በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ መሰረት የተፈለገበት ጉዳይ እንዲፈፀም አሰፈላጊውን ትእዛዝ በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ መሰረት የመስጠት ተግባራት ይገኙበታል።

ይህ የፍርድ ቤት ተግባር መኖሩ ተቀባይነት ያለው አለም አቀፍ አሰራር በመሆኑ የትብብርን ፍላጎት ከፍ ያደርገዋል ተብሎ ይታሰባል።

## 17. ኪሳራና ወጪን በተመለከተ

በስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ውስጥ በመጨረሻው ክፍል ውስጥ ተካተተው በወንጀል ጉዳይ የሚወጣ ወጪን እና የሚደርስ ኪሳራን የሚመለከተው ጉዳይ ነው። አንደ የወንጀል ጉዳይ ተጀምሮ የመጨረሻ እልባት እስኪያገኝ ድረስ በከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ ምስክሮች፣ ፍርድ ቤት ላይ እና ሌሎች አካላት ላይ ወጪን የሚያስከትል በመሆኑ ይህንን ወጪ ማን ሊሸፍን እንደሚገባ መደንገግ ያለበት ነው። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ነባሩ ሕግ ተመሳሳይ ድንጋጌን የያዘ ሲሆን የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ በነባር ሕጉ ላይ ያስከተለው መሰረታዊ ለውጥ የለውም። በመሆኑም የወንጀል ጉዳይ በመሰረቱ የሕዝብና የመንግስት ጉዳይ በመሆኑ በየትኛውም ደረጃ ለሚደረግ ክርክር የሚሰፈልገው ወጪ በመንግስት የሚሸፈን ይሆናል። ይሕ ወጪ አስፈላጊ የሆነውን ወጪ ሁሉ የሚመለከት ሲሆን በተከሳሽ የተለየና ያልተገባ ምክንያት (ምሳሌ ከእስር በመጥፋቱ ፈልጎ በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚወጣ ወጪ) የሚወጣን ወጪ በፍርድ ቤት ውሳኔ ተከሳሹ እንዲሸፍን ሊወሰን ይቻላል። በርካታ ተከሳሾች የሆኑ እንደሆነም እንደሳፈላጊነቱ እየተጣራ በአንድነት እና በነጠላ ሊሸፍኑ ይችላሉ። በማናቸውም ምክንያነት ግን የተከላካይ ጠበቃ፣ የአስተርጓሚ እና መሰል ወጪዎች በመንግስት የሚሸፈን ነው።

በተመሳሳይ ምክንያት በግል አቤቱታ የሚቀርብን የወንጀል ፍርድ ሂደት ወጪ የግል ክስ አቅራቢ (በርካታ ከሆኑም በአንድነት ወይም በነጠላ) የሚሸፈን ነው። የዳኝነት ክፍያን በተመለከተ ጉዳዩ በዐቃቢ ህግ መቅረብ ሲኖርበት ቅድሚያ ስላልሰጠው ብቻ በግል በመቅረቡ የግል ከሳሽን ዳኝነት ማስከፈሉ ፍትሓዊ ስለማይሆን በዚህ ረገድ የቀድሞው ሕግ የጣለው ግዴታ ቀሪ ሆኗል። ይሁን እንጂ ከቅን ልቦና ውጪ በቀረበ ክስ ምክንያት ተከሳሽ ሲከራከር ቆይቶ በነፃ ከተሰናተም በዚህ ምክንያት ተከሳሹ ያወጣው ወጪ በከሳሹ እንዲሸፈን ፍርድ ቤቱ ሊወስን እንዲችል ሕጉ ድንጋጌን ይዟል።

በማናቸውም አግባብ በሚደረግ ክርክር አስፈላጊ የሆነውን የምስክር እና ሌሎች ማሰረጃ ማቅረቢያ ወጪዎች በተመለከተም ምስክሩ ወይም ማስረጃው እንዲቀርብለት የጠራው ወገን ወጪውን ይሸፍናል። ወጪው በመንግስት የሚሸፈን በሚሆንበት ጊዜም ስለወጪው መጠን በደንብ በሚወሰነው አግባብ ይከፈላል። ወጪውን ለመሸፈን አቅም የሌለው ተከሳሽ ካጋጠመም ሥነ ስርአት ሕጉ እውነትን

የማውጣትና ውጤታማ ፍትሕ አስተዳደር እንዲኖር የሚያልም በመሆኑ ይህንን አላማ ማሳካት ይቻል ዘንድ ምክንያታዊ የሆነው ወጪ ተለይቶ በፍርድ ቤት ውሳኔ በመንግስት እንዲሸፈንየሚያስችል ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲወጣ ሕጉይጠብቃል።

## 18. ደንብ፣ መመሪያ እና ቅፃ ቅፆችን ማውጣትእንዲሁም ሕጉን ስለማሻሻል

እንደሌሎች ሕጎች ሁሉ የስነ ስርአትና ማስረጃ ሕጉ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆን አስፈላጊ ከሆነት ነገሮች ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችና መመሪያዎች ሕጉ ስልጣን በሰጣቸው አካላት በአግባቡና በወቅቱ ሲወጡ ነው። በዚህ መሰረት በሚኒስተሮች ምክር ቤት ቢያንስ አምስት ያህል ደንቦች እንዲወጡ ይጠበቃል። በተመሳሳይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያንስ ስምንት ያህል መመሪያዎች፤ በፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ቢያንስ አስራ ሁለት ያህል መመሪያዎች እንዲሁም በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ቢያንስ ሶስት ያህል መመሪያዎች እንዲወጡ ይጠበቃል። ደንቦቹ እና መመሪያዎች በጊዜው ባለመውጣታቸው የህግ አፈፃፀም ክፍተት እንዳይፈጠርና በተግባር የሚስተዋሉ ችግሮች ሳይፈቱ እንደያቀሩ ለማድረግ ይህ ሕግ ከወጣ በኃላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ደንቦቹና መመሪያዎች በጥራት መውጣት ይገባቸዋል። በተመሳሳይ መልኩ እያንዳንዱ ተቋም ለስራው የሚያስፈልጉ ቅፃችን እንዲያወጣም ይጠበቃል። የቅፃ ቅፆች አስፈላጊነት ስራዎች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ፣ የተቀራረበና ከሕጉ ጋር የተናበበ አሰራር እንዲኖር፣ ስራዎች በቅልጥፍና እንዲከናወኑ፣ ለዘወትር ስራዎችም እንደ ቼክ ሊስት እንዲያገለግሉ በመሆኑ በተቻለ ፍጥነት ወጥተው እንዲተገበሩ ይጠበቃል። አሁን ያለውን የባለሙያ ብቃት ግምት ውስጥ በማስገባትም ቅጾችን እንደቀድሞው ሕግ በአስገዳጅነት የሕጉ አባሪ ማድረግ ግን አላስፈለገም።

የፍትሕ አካላቱ መመሪያ እና አስፈላጊ የሆኑ የሚያወጡ ከመሆናቸውም በላይ ይህንን የሥነ ስርአት ሕጉን በማሻሻል ረገድ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይጠበቃል። ማንኛውም የዚህ ሕግ ማሻሻያ በተሟላ እና በዝርዝር ጥናት ላይ የተመሰረተ መሆን ይገባዋል። የስነ ስርአቱ ሕጉን የማሻሻል ሂደት በሕገ መንግስቱ በተረጋገጠው አግባብ የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ ማሳተፍ ያለበት ከመሆኑም በላይ የፍትሕ አካላቱ በማሻሻያው አስፈላጊነት ላይ በጋራ መምከርና ተገቢነቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው። ይህንን አነስተኛ ሂደት ያጠናቀቀውን ማሻሻያ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀጥሎም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ በባለቤትነት እንዲያጸድቅ የሚያስችል ግልፅ ስልጣን በሕጉ ተሰጥቶታል። የሕጉ ማሻሻያም የዚህ ሕግ አካል ሆኖ ይወጣል።

## 19. ሰንጠረዥ

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ክፍፍል የሕጉ አካል ሆኖ በአባሪ በተያያዘው ሰንጠረዥ የተመለከተ ነው። ሰንጠረዡ በመሰረቱ የወንጀል አይነቶችንን ድልድል በደረጃቸው፣ የትኛውን ጉዳይ የትኛው ፍርድ ቤት ይመለከታል የሚለውን የሚያመለክት ከመሆኑም በላይ መነሻ ያደረገበት መርህም ለወደፊቱ ወንጀል አይነት እንደ መነሻ ሊያለግል ይችላል። ሰንጠረዡ ወንጀሎችን የፌዴራል እና የክልል በማለት የሚከፍላቸው በዚህ ህግ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን የስልጣን ድልድል መሰረት በማድረግ ነው። በሌላ በኩልም አንድ ወንጀል ጉዳይ በፌዴራል ስልጣን ስር ወይንም በክልል ስልጣን ስር የሚያርፍ እንደሆነ ለመለየት የሚያስችል መመዘኛ አልነበራቸውም። በስራ ላይ ያሉት ህጎች የወንጀሎቹን ዝርዝር በማስቀመጥ ከሚለዩት በስተቀር በመርህ ደረጃ ያሰቀመጡት መመሪያ የለም። በመሆኑም አንድን ጉዳይ በፌዴራል የወንጀል ስልጣን ስር ያርፋል ወይንስ የክልል ጉዳይ ይሆናል የሚለውን ለይቶ በስልጣን ድልድሉ ሰንጠረዥ ማስቀመጥ የሚያስፈልግ በመሆኑ "የፌዴራል የወንጀል ጉዳይ" የሚለው ምን ምን አይነት ጉዳዮችን ሊያካትት ይገባል የሚለው ከአገሪቱ ሕገ መንግስት አንጣር ታይቶ የስነ ስርአትና ማስረጃሕጉ የዳኝነት ስልጣን ሰንጠረዥን ለማዘጋጀት ጥቅም ውሏል። ይህ መርህ በሕጉ ላይ ለተመለከተው ሰንጠረዥ ክፍፍል ብቻ ሳይሆን ወደፊት የሚወጡ የወንጀል ሕጎች የዳኝነት ስልጣን ጥያቄ በተነሳም ቁጥር ለመፍትት/ለመደልደል የሚስችል ድንጋጌ ይሆናል ማለት ነው።

ወንጀሎቹን በፌፌዴራል ስልጣን ስር እንዲካተቱ የተደረገበት መስፈርትም ይኸው መስፈርት ነው። አንድ ወንጀል በፌዴራል ወይም በክልል የዳኝነት ስልጣን ስር እንደሚያርፍ ከተመለከተ በኋላ ተከታይ ስራው በየትኛው እርከን ላይ የሚገኘው ፍርድ ቤት ሊመለከተው ይገባል የሚለውን መለየት ነው። ለዚህ በመሰረታዊነት መለኪያ ሆኖ የተወሰደው ወንጀሎች በቀላል፣ በመካከለኛና በከባድ ደረጃ የተከፋፈሉ መሆናቸው ነው። በዚህ መለኪያ መሰረትም አበዛኛው የወንጀል ጉዳይ በስረኛው ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የሚታይ ሲሆን መካከለኛው ፍርድ ቤት በአብዛኛው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይሆናል ማለት ነው። በመሆኑም እስከ አስራ አምስት አመት ድረስ የሚያስቀጡ ወንጀሎች እንዳግባብነታቸው በፌዴራል ወይም በክልል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የሚታዩ ሲሆን ከአስራ አምስተ አመት በላይ የሚያስቀጡ ወንጀሎች በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሚታዩ ይሆናሉ። ይሁን እንጂ በአንድ ድንጋጌ ውስጥ ከፊሉ ከአስራ አምስት አመት በታች ከፊሉ ከአስራ አምስት አመት በላይ የሚያስቀጡ ድንጋጌዎች ሊገኙ ይችላሉ። በሌላም በኩል በተመሳሳይ ከፊሉ በፌዴራል ከፊሉ ደግሞ በክልል ፍርድ ቤት ስር የሚያስቀጣ ወንጀል

ሊያጋጥም ይችላል፡፡ በዚህ መልኩ አንድ ተከሳሽ በተለያዩ ወንጀሎች የመከሰስ እድል ቢገጥመው ስልጣን ያለውን ፍድ ቤት የመለየት ችግር እንዳይገጥም ክስን አጣምሮ የማየት መርህን በመተል ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤት ወይንም ከባዱን ጉዳይ ለማየት ስልጣን ለተሰጠው ፍር ቤት እንዲቴ በሚያስችል መልክ ድልድሉ በሰኘተረዡ ተሰርቷል፡፡